የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በዓለም መድረክ

አዘጋጅ፡-

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት
ሥርዓተ ትምህርት ክፍል መስከረም 2012 ዓ.ም.

ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

መግቢያ

የቤተክርስቲያን ታሪክ ትርጉም…… 2

የቤተክርስቲያን ታሪክ ምንጮች…….. 2

የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት …… 4

ምዕራፍ አንድ

1.1 የቤተ ክርስቲያን ትርጉም…….. 5

ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን …….. 5

የክርስቲኖች አንድነት……..…..8

እያንዳንዱ ክርስቲያን……...…..9

ምዕራፍ ሁለት

የቤተ ክርስቲያን ዕድሜ……...10

2.1 ማኅበረ መላእክት (ቤተክርስቲያን በዓለመ መላእክት)……10

2.2 ከአዳም እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ……...11

2.2.1 ዘመነ አበው……..……11

2.2.2 ዘመነ መሳፍንት……..…..19

2.2.3 ዘመነ ነገሥት……...24

2.2.4 ዘመነ ነቢያት ሥህናት/ ፀዋዌ…… ……...29

ምራፍ ሦስት

የአማናዊቷ ቤተክርስቲያን አመሠራረት……..…..31

3.1 የክርስቶስ መምጣት ተስፋና የእስራኤል ሕዝብ አምልኮ……..…31

ፈሪሳውያን ……32

ሰዱቃውያን……..…33

ኤሴውያን……...33

3.2 የኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ……...35

3.3 የሐዋርያት ጉዞ / ዘመነ ሐዋርያት / ከ34 ዓ.ም - 70 ዓ.ም/……37

3.3.1 በዓለ ጰራቅሊጦስ……..……38

3.3.2. የሐዋርያት አመራረጥ ታሪክ ፣ ገድልና ክብር……38

3.3.3 ቤተ ክርስቲያን በአይሁድና በአሕዛብ መካከል……..38

3.3.3.1 በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረ አለመግባባት……....59

3.3.3.2 የሐዋርያት ሲኖዶስ (50 ዓ.ም) ……..…..59

3.4 ዘመነ ሐዋርያውን አበው ከ70 ዓ.ም - 160 ዓ.ም ……..….60

3.5 ዘመነ ሰማዕታት ከ160-312……..…..60

ንጉሥ ዳክዮስ (249-251 ዓ.ም)……..61

ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ……..……61

ታላቁ ቆስጠንጢኖስ……..62

ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ለቤ/ክ የሰጣቸው መብቶች……..63

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ

ክፍል አንድ

መግቢያ

➢ የቤተክርስቲያን ታሪክ ትርጉም

ሰዎች ሠርተውት ያለፉትና ያከናወኑት ነገር እንዲሁም በቀደመው ዘመን የተፈጸመ ክንዋኔ ሁሉ ታሪክ ይባላል። የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ስንልም ቤተ-ክርስቲያን ያከናወነቻቸውንና ሠርታቸው ያለፈቻቸውን፣ በዘመናት ሁሉ የተፈጸመባትን ማንኛውም ነገር ማለታችን ነው። በተጨማሪም የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ማለት የክርስትና እምነት /ሃይማኖት/ ታሪክ ማለት ነው። የአምላክ መገለጥ በዘመን፣ በቦታ የተደረገ ስለሆነ መቼ የት ለምን እንዴት እንደሆነ የምናውቅበት ክፍል ነው። የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ስንል በሀገር ወይም በአህጉር ያልተወሰነ አጠቃላይ በዓለም ሁሉ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ያላትን ታሪክ የሠራችውን ሥራ፣ አስተምህሮቷን፣ እናትነቷን ወዘተ... ለመግለጽ ነው።

የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ተማሪ

- ቤተ-ክርስቲያን ከተመሠረተች ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ ያለውን ታሪኳን፣
- እንዴት እንደተመሠረተች፣
- እንዴት የዓለም ሕዝብ እንደተቀበላት፤
- በየጊዜው ከአባላቷና ከተቃዋሚዎች የተሰነዘሩባትን የኑፋቄ ትምህርቶች የጸና ሃይማኖትን እንደምን እንዳሳለፈቻቸው ይህንን እና የመሳሰለውን ያጠናል።
- በዚህ የጥናት ጊዜው ያለፈውን ያውቃል፣ ያለበትን ሁኔታ ያስተውላል።

የቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት እግዚአብሔር ግዕዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያደረገው/የሚያደርገውን/ ግንኙነት የሚገልጥ የረኸርም ዘመን ሒደትም የሚያትት ክፍል ነው።

➢ የቤተክርስቲያን ታሪክ ምንጮች

ለቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት በምንጭነት የሚከተሉት የሚጠቀሱ ሲሆን የታሪክ ተማሪዎች እነዚሁን ተዛማጅ መጻሕፍትና ምንጮች በሚገባ መዳሰስ ይገባቸዋል።

1. ቅዱሳት መጻሕፍት
   - መጽሐፍ ቅዱስ /የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት/
   - አዋልድ መጻሕፍት
2. አባቶቻችን የጻፏቸው የታሪክ መጻሕፍት ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታና ጊዜ ተገኝተው የቤተ-ክርስቲያንና የዘመኑን ታሪክ የጻፉ ጸሐፊዎች /ሩፊኖስ፣ ሶቅራጥስ፣ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን፣ አውሳብዮስ ወዘተ...../ የጻፏቸው መጻሕፍት።
3. በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጉባኤዎችና ውሳኔዎች
   - ጉባኤ ኒቂያ፣ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፣ ጉባኤ ኤፌሶን
4. ጥንታዊ ቅርሶች /በየጊዜው የክርስቲያን መቃብራት፣ መቅደሶች፣ ሥዕሎች፣ ገንዘቦች፣ የድንጋይ ላይና የብራና ጽሑፎች፣ የአርኪዮሎጂ /የጥንታዊ ነገሮች ምርመራ/ ጥናት ግኝቶች ወዘተ... /
4. ጥንታዊ ቅርሶች
5. መንፈሳውያንም ሆኑ ዓለማውያን ነገሥታት በቤተክርስቲያን ላይ የደነገጓቸው ልዩ ልዩ ህግጋት ወዘተ ታሪኮቿ ናቸው።

የቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ዓላማና ጥቅም

- የቤተክርስቲያናችንን ከፍተኛነትና ጠቃሚነትን ለመገንዘብና ራስንም በእምነት ለማጽናት፣
- ባለፉት ዘመናት የተከሰቱ ችግሮችን ለማወቅና በድጋሚ እንዳይከሰቱ የመፍትሔ ሃሳብ ለመስጠት፣
- ቅዱሳን አባቶች በመከራና በፈተና ያሳዩትን የሃይማኖት ፅናት በማየት እነርሱን ለመምሰልና እኛም የድርሻችንን ለመወጣት እና
- በመንፈሳዊ ጉዞአችን መንፈሳዊ ጥበብና ብልሃትን ገንዘብ እንድናደርግ ይጠቅመናል።

የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት

አንድ ነገር የራሱ የሆነ ጠባይ፣ የራሱ የሆነ መገለጫ፣ የራሱ የሆነ መታወቂያና መጠሪያ እንዳለው ሁሉ የቤተ-ክርስቲያን ባሕርያት ስንል ቤተ-ክርስቲያን ቤተ-ክርስቲያን የምትታወቅበት የራስዋ የሆነ ማንነት፣ የራስዋ የሆነ ጠባይ፣ የራስዋ የሆነ መገለጫ አላት። ቤተ-ክርስቲያን የማትመረመር የእግዚአብሔር መለኮታዊ የምሥጢር ግምጃ ቤት ናት። ቤተክርስቲያን ከሌሎች አካላት የምትለይባቸው (የምትታወቅባቸው) በርካታ ባሕርያት ቢኖሩም በዚህ ክፍል አራቱን እንመለከታለን፡-

1. ቤተ-ክርስቲያን አንዲት ናት

ቤተ-ክርስቲያን አንዲት ናት ስንል የአንድነቷ መሠረት ሃይማኖት፣ የምታምነው እምነት ይዘት ነው። መገለጫውም ምሥጢራት ናቸው። ምእመናን አንድ ልብ አንድ ኅሳብ ሆነው በውስጥ የሚደረገውን ሥርዓትና ክብር ይካፈሉበታልና ስለዚህም የሚሠራባት ሥርዓት የሚፈጸምባት ጸሎት አንድ በመሆኑ ቤተክርስቲያን አንዲት ናት። (ገላ 4÷5) እግዚአብሔር ሲሠራት (ሲመሠርታትም) አንዲት ናት። በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ሰዎች በከተማ፣ በገጠር፣ በወርቅ፣ በአፈር፣ በሣር፣ በእንጨት፣ በቆርቆሮ፣ በድንጋይ፣ በብሎኬት፣ በእምነ በረድ፣ በወርቅ፣ በዕንቊ፣ በአልማዝ የተሠሩ ሥርዓቷን የጠበቁ የተለያዩ የሕንፃ አሠራሮች ሁኔታ ቢኖርም ክብሯ አንድ ነው።

ቤተ-ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት። ራሷ፣ መሠረቷ፣ ጉልላቷ፣ ጌታዋና መሪዋ አንድ ስለሆነ ሙሽራዋ ክርስቶስ የሆነላት ሙሽሪት ቤተክርስቲያን አንዲት ናት። ጌታችን የእኛን በደል በእርሱ ላይ ያኖረ መሆኑን ለማሳየት ወደ ባሕርይ አባቱ በጸለየ ጊዜ "እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው" (ዮሐ. 17፥11) በማለት ቤተክርስቲያን አንዲት እንደሆነች ገልጿል። (ኤፌ. 4፥4-6) (ሮሜ. 12፥4-5፣ ዮሐ.15፥5-6)

2. ቤተ-ክርስቲያን ቅድስት ናት

ቤተ ክርስቲያን ቅድስና የባሕርይው የሆነው ጌታችን በደሙ የመሠረታት፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ባስተማሩት መሠረት ቤተ-ክርስቲያን የተቀደሰ ሥራ የሚሠራባት፣ በውስጧም የሚገቡትና የሚኖሩት ሁሉ በየጊዜው ራሳቸውን የሚቀድሱባት ቤት ናት። (ሐዋ 20÷28፣1ኛጴሮ.1፥15-16፣ዘሌ.19፥2) በቤተ ክርስቲያን ኃጢአትና ርኩሰት አይፈጸምባትም። በኃጢአትና በክህደት ረክሰው የነበሩ በእምነት በንስሐ ወደ እርሷ ገብተው ይቀደሳሉና ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት። መዝ 45÷4 ቤተ-ክርስቲያን ቅድስት ናት ስንል ለእግዚአብሔር የተለዩች ክብርትና ንጽሕት ናት ማለታችን ነው። ክርስቶስ ለራሱ ትሆን ዘንድ የለያት፣ ነፍሱን ስለእርሷ አሳልፎ እስከሞት ድረስ በመስጠት የወደዳት፣ በደሙ የዋጃትና በቃሉ ያነጻት የክርስቶስ ሙሽራ ቅድስት ናት ማለት ነው። (ኤፌ. 5፥25-27)

3. ቤተ-ክርስቲያን የሁሉና በሁሉ ያለች (ኩላዊት) ናት

ቤተ ክርስቲያን በዘር፣ በጎሳ በቋንቋ ተከፍላ የእገሌ ናት የምትባል ሳትሆን የሁሉና በሁሉ ያለች ናት። ጌታችን በመስቀል ላይ የተሰቀለው ለሁሉም እንጂ ለተወሰኑት ብቻ አይደለም። ማቴ 28÷19 ‹‹እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።›› በማለት ያዘዘው ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ሁሉ የተገባች በመሆኗ ነው። (ገላ 3÷23)

ቤተ-ክርስቲያን አንዲት ብትሆንም መንፈሳዊት ናትና በሁሉ ያለች የሁሉ ናት። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ግእዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነት ናትና በአንድ አካባቢ ልትወሰን አትችልም። (ኤፌ. 1፥23) ስለዚህ በሁሉ ያለች፣ አምኖ ተጠምቆ በበሯ የሚገባውን ሁሉ ተቀብላ አካሏ የምታደርግ የሁሉ ናት እንጂ፣ የተጀመረችባት የፍልስጤም ምድር፣ የተስፋፋችበት የሮም ወይንም የሌላ አካባቢና የአንድ ነገድ ብቻ አይደለችም። ክርስቶስ ለሚያምኑበት ሁሉ ጌታ እንደሆነ ቤተ ክርስቲያንም የሁሉ ናት።ስለዚህም ስለ ቤተ ክርስቲያን ስናነሣ ቤተ ክርስቲያን በሰማይም በምድርም ያሉትን በማጠቃለል በሁሉ ሥፍራ የምትገኝ ሁሉን የያዘች የእግዚአብሔር ሙላቱ ናት ማለት ነው።

4. ቤተ-ክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት

ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት ታስተምራለች። እንደ ሐዋርያት ምሥጢራትን ትፈጽማለች። ሐዋርያት ከጌታ የተቀበሉትንና የእነርሱ የሆነውን ቅዱስ ትውፊት ተቀብላ ትሠራበታለች እንጂ አዲስ ነገር ፈጥራ ራሷን ከግንዱ የምትለይ ቅርንጫፍ አትሆንም። (ኤፌ. 2፥20-22) እንደ ሐዋርያት

የምታስተምር፣ እንደ እነርሱም የተለየ (ቅዱስ) ስብስባ (ሲኖዶስ) ያላት፣ በዚህም ሥርዓት የምትመራ በእነርሱ የሥርዓት መሠረት ላይ የታነጸች ስለሆነችና የሐዋርያትን ገድል ይዛ በመገኘት ዕረፍታቸውን እየቆጠረች ስለምታስባቸው ሐዋርያዊት ናት። (ይሁ.1÷3)። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት አንሥቶ ሳይቋረጥ በቅብብሎሽ የመጣ አስተምህሮ፣ ሕይወት፣ የክህነት ክትትል፣ ምሥጢራት ያላት ናት። ቀዳሚ ተልእኮዋም ወንጌልን ለሁሉም መስበክ ነው። (ማቴ. 28፥19) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ጋር እንደነበረ፣ ትላንትም ዛሬም ነገም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ነው። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት የተቀበለችውን ትውፊት፣ ሥርዓት በልጆቿ እያስቀጠለች ሥርዓቷ ሳይጓደል አስተምህሮዋ ሳይበረዝና ሳይከለስ እስከ ዳግም ምጽአት ጠብቃ የምታቆይ ሐዋርያዊት ናትና ነው።

ምዕራፍ አንድ

1.1 ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው ?

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የግእዝ ቋንቋ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ በተጻፈበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ‹‹ካሃል›› (Qahal) እና ‹‹ኤዳህ›› (Edah) ተብሎ ይተረጎማል። ሐዲስ ኪዳን በተጻፈበትና ሰብኣ ሊቃናት (Septuagint) ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ በተረጎሙበት ትርጉም አቅሌስያ (akklesia) በሚል ቃል ተጽፏል። ወደ ግእዝ ሲተረጎምም ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ተተርጉሟል።

ቤተክርስቲያን የሚለው ከሁለት ቃላት በጥምረት የተገኘ ሲሆን ቤተ ማለት በግእዝ አደረ ክርስቲያን ደግሞ የክርስቶስ ማለት ነው። በዚህም ቤተክርስቲያን የሚለው በቁሙ ሲፈታ የክርስቶስ ማደሪያ፣ የክርስቶስ ሕዝብ፣ የክርስቶስ ተከታይ ማለትን ያስገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹ቤተ›› የሚለው ቃል ወገንን፣ ነገድን ያመለክታል። ይህም ቤተ ያዕቆብ፣ ቤተ እስራኤል፣ ቤተ አሮን የሚለው ቃል የእስራኤል ሕዝብ፣ የእስራኤል ወገን የሚያመለክት እንደሆነ ሁሉ ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› የሚለውንም ቃል እግዚአብሔር በክርስቶስ የጠራውና ለእግዚአብሔር የተለየ አካል፣ ለእግዚአብሔር የተለየ አካል፣ ለእግዚአብሔር የተለየ አካል፣ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ እና ለእግዚአብሔር አምልኮ የተለየ ቦታ የሚል ትርጉም አለው። ቤተክርስቲያን በዘይቤ /በሰዋሰው አፈታት/፡- ቤተክርስቲያን ሦስት ትርጉም ያለው በዘርፍና በባለቤትነት የተቀመጠ ስም ነው።

፩. ሕንፃ ቤተክርስቲያን

በብፁአን አባቶች ቡራኬ ተባርኮ በሜሮን የከበረ የድኅነትና የክብር ምሥጢራት የሚፈጸምበት፣ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ሕንፃ ቤተመቅደስ (ቤተ-ክርስቲያን) ይባላል። ቤተመቅደስ ልዩ፤ ቅዱስ፣ ንጹሕ፣ ክቡር የሆነ የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንበት፣ የሚቀደስበት፣ የሚከበርበት ከሌሎች ቦታዎች ሁሉ የተለየ የክብር፣ የምሕረትና የይቅርታ አምላክ የእግዚአብሔር የጸጋው መገኛ ነው። ለእግዚአብሔር ስግደትና ሥርዓተ አምልኮ የሚከናወንበት የምስጋና የጸሎት ቤት ነውና ስለዚህ ቅዱስ፣ ንጹሕ፣ ልዩ መባል ይገባቸዋል። (ዘፍ. 28፥18-22) ቤተ ክርስቲያን ስንል የክርስቲያኖች መገናኛ መሰብሰቢያ በዓት ማለት ነው። ይህም ክርስቲያኖች በአንድነት የሚጸልዩበት፣ የሚሰግዱበት፣ ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉበት፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቦታና የጸሎት ቤት ማለት ነው። (ኢሳ 56÷7፤ ኤር 7÷10-11፤ ማር 11÷17፤ ሉቃ 19÷46) ቤተ መቅደስ (ቤ/ክ) በአጭሩ እግዚአብሔርና ሕዝቡ የሚገናኙበት እግዚአብሔር አምላክነቱ የሚገለጥበት ሕዝቡም ለአምላኩ የምስጋናም ሆነ የስግደት ሌላም ዓይነት መሥዋዕት የሚያቀርብበት የተቀደሰ ሥፍራ ነው።

ለጊዜው በሙሴ መሪነት ሕዝበ እስራኤል ከፈጣሪያቸው እግዚአብሔር ጋር የተገናኙበት ቃል ለቃልም ይነጋገሩበት ከነበረው ደብተራ (ድንኳን) ጀምሮ ሰሎሞን ከሠራው ቤተ መቅደስ ጀምሮ እስከ አሁን ያለው እግዚአብሔር ራሱ በፈቃዱ ባርኮ የሰጠን ቤተ መቅደስ ይባላል። ይህም የእግዚአብሔር አዳኝነት

የሚነገርበት፣ ወንጌል የሚሰበክበት፣ በመስቀል ላይ ለቤዛነት የተሰጠንና ዘላለማዊ ሕይወት የሚወረስበት ቅዱስ ቁርባን (ሥጋውና ደሙ) የሚዘጋጁበትና ለምእመናን የሚሰጥበት፣በአጠቃላይ የእግዚአብሔር የጸጋው መገኛ በዘመነ ሐዲስ ቤተ-ክርስቲያን የተባለው ሕንፃ ነው። ይህ በሰው እጅ የተሠራው ቤተ መቅደስ ነው።

ይህ ሰዎች የሠሩት ቤት (ሕንፃ) ቅዱስ ስሙ እንዲጠራበት፣ ቤተመቅደስ እንዲባል፣ የእግዚአብሔር ማደሪያም እንዲሆን የወደደና የፈቀደ እግዚአብሔር ነው። (ዘጸ. 25፥8-10)፤ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ባለቤቱ ራሱ መቅደስ ብሎ የጠራው የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን ተሠራ። ከዚህ በኋላም የእግዚአብሔር ልጆች እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሁሉ በዚህ ድንኳን ደጀፍ እየሰገዱ አምልኮታቸውን ይፈጽሙ ነበር። (ዘዳ. 33፥9-11)። በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ በድንኳኑ ደጃፍና ዙሪያ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ ለስሙ የምስጋና መሥዋዕት እያቀረቡ ሰሎሞን በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ እስከ ሠራው ቤተ መቅደስ ድረስ ቆይተዋል።

ቤተ መቅደስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው የዳዊት ልጅ ንጉሥ ሰሎሞን ነው። (2ኛነገ. 25፥8-17) ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም፤ የአባቱን የዳዊትን የኑዛዜ ቃል በማክበር በብዙ ወጭና ድካም፣ ውስጥና ውጪውን በኪሩቤል (መላእክት) ሥዕል (1ኛነገ. 6፥29)፣ በውስጥ ያለውንና በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀውን መጋረጃም በመላእክት ሥዕል አስጊጦ የሠራው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ የተሠራው በኢየሩሳሌም አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕት በአቀረበበትና ዳዊት በገዛው ቦታ ነው። ዘፍ. 22፥2፣ 2ኛዜና 3፥1)። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን የሠራበት ዘመን በ4500 ዓ.ዓ እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቧል። ቤተ መቅደሱ የተሠራበት ምክንያትም እስራኤል በምድረ በዳ ሲጓዙ ሥርዓተ አምልኮታቸውን ሁሉ የሚፈጽሙት በመካከላቸው ባለው ሙሴ ባሠራው ደብተራ ኦሪት (የምስክር ድንኳን) ነበር። ነገር ግን አገራቸው ሲገቡ ንጉሡ ዳዊት እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ ሕዝበ እስራኤል ሥርዓተ አምልኮታቸውን የሚፈጽሙበት ድንኳን እንጂ ቤት ስለሌለ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመሥራት ፈለገ፤ አስፈላጊውንም ቁሳቁስ ሰበሰበ። ልጁንም ሰሎምንን ጠርቶ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ስም ቤት ይሠራ ዘንድ አዘዘው።(1ኛዜና. 22፥1-ፍጻሜ)። ሰሎሞንም አባቱ ዳዊት ባዘዘው መሠረት ቤተ መቅደሱን እጅግ ውብ አድርጎ ሠራ። (1ኛነገ. 7) በቤተመቅደሱ ግራና ቀኝ ሁለት አዕማድ ቆመው ነበር። (2ኛዜና 3፥4-15) በመጨረሻም በምስጋና በጸሎትና በመሥዋዕት በእስራኤል ማኅበር ፊት ቤቱን ቀደሰ/ቅዳሴ ቤቱን አከበረ። (1ኛነገ. 8)። ይህ ሰሎሞን የሠራው ቤተ መቅደስ ከተፈጸመ በኋላ አንዳንድ ሰዎች ያኔም ሆነ ዛሬ ቤቱ የእግዚአብ ሐር ነው መባሉ እግዚአብሔርን ይዋስነዋል እንዳይሉ እንዲህ በማለት የተነገረ እናገኛለን። ‹‹በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ›› (1ኛነገ. 8፥27) እግዚአብሔር በባሕርዩ መወሰን የሌለበት በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ ሲሆን የሰዎችን አምልኮ ለመባረክ፣ የሰዎችን ልመናና አስብቁዖት ለመቀበል፣ ለሰዎችም ጸጋውን ለማደል (ለመስጠት)፤ ሕዝቡ ከእርሱ ጋር እርሱም ከሕዝቡ ጋር እንዲገናኙ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥሩልኝ አለ እንጂ ተለክታ በተሠራች ቤት ቀርቶ ዓለም ሁሉ ሊወስነው የማይችል መሆኑ የታወቀ ነው። (1ኛነገ. 8፥12-13) ይህንንም ቤተ መቅደስ ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢሩሳሌምን በወረረ ጊዜ ቤተ መቅደሱን አቃጠለው። ፡- **"የእግዚአብሔርን ቤትና የንጉሡን ቤት አቃጠለ። የኢየሩሳሌምን ቤቶች ሁሉ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ዙሪያዋን ሁሉ በእሳት አቃጠለ።"** (ኤር. 52፥13) እንዲል። የእስራኤል ሕዝብ ድል ሆነው ወደ ባቢሎን ከተማረኩ ከሰባ ዓመት በኋላ በፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ፈቃድ በነፃነት በሥጋዊ መሪያቸው በዘሩባቤል በመንፈሳዊ መሪያቸው ኢያሱ አማካኝነት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። በዘሩባቤልም መሪነት የፈረሰውን ቤተ መቅደስ እንደገና ሠሩ። (ዕዝ.3፥6፣ ዘካ.1፥16፣ 6፥9፣ 8፥10) በዚህን ጊዜ አንዳንድ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ቀድሞ ቃል የገባበት ቤተመቅደስ በመፍረሱ ለማቅለል ቢሞክሩም እግዚአብሔር የኋለኛው ከፊተኛው የበለጠ የከበረ መሆኑን በሐጌ. 2፥7-10 ተናገረ። በዚህም መሠረት ቤተ መቅደሱ በእግዚአብሔር የተቀደሰ ሆኖ እንደተከበረ አስፈላጊውም የአስራኤል ሥርዓተ አምልኮ እየተፈጸመበት እስከ ክርስቶስ ዘመን ቆይቷል። ከክ.ል.በፊት በ19 ዓመት ሄሮድስ ቤተ መቅደሱን እንደገና አስፋፍቶ አሠራው። ድንግል ማርያም በሦስት ዓመቷ ገብታ 12 ዓመት የተቀመጠችበት እዚህ ነው።

እንደገና ይህ ቤተ መቅደስ ለካህናት፣ ለአይሁድ ወንዶችና ሴቶች፣ ለአሕዛብም የሚሆኑ አራት አደባባዮች ነበሩ፡፡ የቤተ መቅደሱ አደባባይ በክርስቶስ ጊዜ 500 በ300 ሜትር ያህል ነበረ፡፡

ቤተ መቅደሱ ከእስራኤል ውጭ በዓለም ሁሉ እንዲታነጽና ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን አሕዛቡም አምልኮታቸውን በቤተ መቅደሱ እንዲገልጡ የወደደና የፈቀደ መሆኑንም ጌታችን ራሱ **‹‹ቤቴ (ለአሕዛብ ሁሉ) የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ የተጻፈ አይደለምን እናንተ ግን የወንዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት››** በማለት ከተናገረው ቃል ለማረጋገጥ እንችላለን፡፡ (ማር. 11፥15-19፣ ዮሐ. 2፥13-18፣ መዝ. 68፥9)) አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያርግ ሐዋርያት የአምላካቸውን ቡራኬ ተቀብለው ወደ ኢሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ የተሰጣቸውን ተስፋ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እስከ ተቀበሉ ድረስ ዘወትር በማመስገንና በመጸለይ በቤተ መቅደሱ ቀይተዋል፡፡ (ሉቃ. 24፥50-53) ይህ ደጅ ጽናት ያስገኘው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለሐዋርያት ከታደላቸው በኋላ እንኳ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች (ማኅበረ እስጢፋኖስ) ሳያቋርጡ በየቀኑ በቤተ መቅደስ አገልግሎትና በጸሎት ተግተው ይኖሩ እንደነበር ለማረጋገጥ እንችላለን፡፡ (ሐዋ. 2፥46) ከዚህ በመነሣት ሐዋርያት ዘወትር በዘጠኝ ሰዓት ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ይገሰግሱ እንደነበር ተጽፏል፡፡ (ሐዋ. 3፥1-3) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እየተመሰጠ ከሚመጣበት ፈተና ያመልጥ የነበረው በቤተ መቅደስ እየተገኘ በመጸለይ ነበር፡፡ (ሐዋ. 22፥17)፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ቅዱሳን ሐዋርያትና የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በተወሰነ ቦታ የጸሎት ቤት እንደሌላቸውና እንዳለሠሩ አላደረጉም፤ ነገር ግን ወደ አይሁድ ቤተመቅደስ በመሄድ ይጸልዩ እንደ ነበር ነው፡፡ እንዲሁም እነዚህ ክርስቲያኖች በግል የክርስቲያን ቤቶች በተለያዩ ክፍሎች እየተገናኙ ይጸልዩ ቅዱስ ቁርባንን ያዘጋጁ ነበር፡፡ ምእመናንም በቤተ ክርስቲያን ሆነው በሚጸልዩ ሰዓት በሌላ ቦታ ሆነው ከሚጸልዩት ጸሎት ይልቅ የተለየ ነውና ልመናቸውን እግዚአብሔር ይሰማል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ጸሎት ማድረግ፣ እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ቃለ እግዚአብሔርን መስማት፣ ከሌላ ቦታ በተለየ ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኛልና፡፡

ክርስትና እየተስፋፋና እየታወቀ ከሄደ በኋላ ቤተ ክርስቲያንም በፊልጵስዩስ ለመጀመሪያ ጊዜ በጌታችን ፈቃድ ከተሠራ በኋላ ክርስቲያኖች ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉት በቤተ ክርስቲያን ብቻ መሆን ጀመረ፡፡ ከዚያ በፊት የነበሩ ምኩራብና መቅደስም አገልግሎታቸውን ለቤተክርስቲያን አስረከቡ፡፡የዚህ የቤተ መቅደስ ነገር በምድር ብቻ ተወስቶ የሚበቃ ብቻ ሳይሆን ይህ በምድር ያለው ምድራዊው ኃላፊ ሆኖ የማያልፈው ሰማያዊው ቤተ-ክርስቲያን በሰማይ ደግሞ መኖሩን እግዚአብሔር አምላክ በመጻሕፍት አማካኝነት ገልጦታል፡፡ (ራዕ. 11፥19)

የቀድሞው ቤተ መቅደስ በሐዲስ ኪዳን ከቶ አያስፈልግም የሚሉ የሚያነሡትን ጥቅስ እንመልከት፡፡ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ውጭ ያሉት ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል ለራሳቸው ሰውነት ብቻ በመስጠት ሕንጻ ቤተ መቅደስን ሲነቅፉ ይደመጣሉ፡፡ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ጥልቅ የሆነ መለኮታዊ ምሥጢር የተሸከመች፣ እጅግ የሚደንቅ ባሕርያት ያላት፣ በእጅ ከመዳሰስና በዐይን ከመታየትም ያለፈ የረቀቀ እግዚአብሔር የምሥጢር ግምጃ ቤት ናት፡፡ እነዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ፡-

፩. **ኢሳ 66፥1-2**፡- "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሰማይ ዙፋኔ ነው፣ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድነው? እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር...."

ይህን የተናገረበት ምክንያት፡- ቀዳሚውንና ተከታዩን ምዕራፍ ብንመለከት እስራኤል ጣዖት እያመለኩ፣ኃጢአት እየሠሩ፣ የንስሐንም ጥቅም እየተዉ፣ ሕጉንና ትእዛዙን እያቃለሉ ቤተ መቅደስ እንሠራለን የሚሉትንና የራሳቸውን ሕይወት ሳያስተካክሉና ሳይመረምሩ ቤተ መቅደስ በማነጽ የሚድኑ የሚመስቸውን ኃጢአት እየሠሩ ወደ ቤተ መቅደስ መምጣትም የማያድን መሆኑን ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ ነው፡፡ከዚህም ሌላ ለመንግሥቱ ሽረት ለግዛቱ ወሰን የሌለውን በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ አምላክ እግዚአብሔርን በቤተ መቅደስ ብቻ ተወስኖ የሚኖር ነው፤ እንዳይሉና የሃይማኖት ሕፀፅ እንዳያመጡ ለማስገንዘብ፡፡

፪. **‹‹ልዑል አምላክ በሰው እጅ በሠራው ቤተ መቅደስ አይኖርም››** (ሐዋ. 7፥48-50)

--›› ቀደም ብሎ የቤተ መቅደሳችንን ሥርዓት አቃለለ ብለው አይሁድ ክርስቶስን ሰቅለውታል፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስንም ደግመው ሥርዓተ ቤተ መቅደሳችንን በመንቀፉ የሰቀልነው የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ

መዝሙር ነውና በድንጋይ ቀጥቅጠን እንግደለው ብለው ሁሉም ድንጋይ ባነሡበት ጊዜ የቤተ መቅደስ መሠረት የሆነውን ክርስቶስን ሰቅላችሁ ገደላችሁት ተከታዮቹ የሆኑ ክርስቲያኖችንም ከገጸ ምድር ለማጥፋት የተዘጋጃችሁ በመሆኑ ከዚህ ክፉ ተግባራችሁ ጋር ቤተመቅደሳችን ነው ብላችሁ በምትመኩበት በሕንፃው እግዚአብሔር አይኖርበትም ለማለት ነው።

ቤተ መቅደስ በሐዲስ ኪዳን ባያስፈልህግ ኖሮ

- እግዚአብሔር ለሰሎሞን ‹‹ጸሎትህን ሰምቻለው ለዘላለም ስሜ በዚ ያድር ዘንድ ... ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ ናለለው ነበር።›› ባላለው ነበር። (1ኛነገ 812-13፣ 9፥3) [9]
- በማቴ. 5፥23-24፡- ላይ ‹‹*መሠዊያው*›› ላይ ብሎ የሚል አገላለጽ ባልተጠቀመ ነበር።
- ዮሐንስ አቡቀለምሲስና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሰማያዊ ቤተመቅደስ ባልጻፈም ነበር። (ራዕ.11፥1-2 ፣11፥19፣ 14፥17፣ ዕብ 9፥11-12) (ሐምሌ/ነሐሴ 1993)
- 1ኛጢሞ.3፥15 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቤት ‹‹የእውነት ዓምድ›› ባላለው ነበር። (‹‹በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንዴት መኖር እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ›› ሲል ሕንፃ ቤተ መቅደሱን ያሳያል። -- ሐመር የካቲት 2010 ዓ.ም)
- በተጨማሪም ዘጸ. 25፥8-9፣ ዘጸ. 40፣ ይመልከቱ። በ1ኛ ሳሙ 3፥3 ‹‹የእግዚአብሔር መቅደስ››፣ በ2ኛነገ. 24፥13 ‹‹የእግዚአብሔር ቤት›› በዘፍ. 28፥17-28 ‹‹ቤተል-የእግዚአብሔር ቤት›› ማለቱን ልብ ይበሉ።

፪. የክርስቲያኖች አንድነት (አክሌስያ)

የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ለመሆን የተቀደሱ የክርስቲያኖች አንድነት ቤተ ክርስቲያን ይባላል። የክርስቲያኖች አንድነት ስንል ጳጳሳትን፣ ካህናትን፣ ዲያቆናትን፣ ምእመናንን፣ ማለት ነው። በዚህም መሠረት ቤተ-ክርስቲያን ማለት አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸምና ተልእኮዋን በአግባቡ ለመወጣት የዘረጋችውን አስተዳደራዊ መዋቅርና ሥርዓት ሁሉ ያጠቃልላል። ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጌታ በአንድ እምነት እና በአንድ ጥምቀት አምነው የተጠመቁ፣ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ፣ በዚህ ምድር በአንድ ጎሳብ እና ተስፋ የሚኖሩ፣ በመጪው ዓለምም በእግዚአብሔር መንግሥት በዘለዓለማዊ አንድነት የሚኖሩ ክርስቲያኖችን የሚያመለክት ነው። በመሆኑም ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› ማለት የክርስቲኖች ማኅበር ወይም የምእመናን አንድነት ጉባኤ ማለት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ጌታችንም በወንጌል የእያንዳንዱ ምእመን (ክርስቲያን) አካል ስብስብ (አንድነት) ቤተ ክርስቲያን እንደሆነና እርሱ እንዲያድርበት ሲገልጽ **‹‹ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚመሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለው››** (ማቴ. 18፥20) በማለት ተናግሯል።

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› የሚለው ቃል ተደጋግሞ ተጽፎ ይገኛል። በአብዛኛውም የሚያመለክተው የክርስቲያኖችን ማኅበር ነው። (ማቴ. 18፥15-17፣ 2ኛጴጥ. 5፥13) በሐዋርያት ሥራ ላይም በብዙ ቦታ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የተጠቀሰው በየቦታው የነበሩትን የክርስቲያኖች ጎባረት የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደሚለው ማለት ነው።

በግእዙ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የተተረጎመው በጽርዑ ኤክሌስያ ከሚለው ቃል ጋር አንድነት አለው። ፍቺውም ‹‹የተጠሩ ወይም የምርጦች ሸንጎ›› ማለት ሲሆን የጎሩያነ እግዚአብሔር ጉባኤ ማለት ነው። ስለዚህ የጉባኤውን አባላት ያመለክታል። በ284 ቅ.ድ.ክ ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ የተረጎሙት ሰብአ ሊቃናት ሙሴ ካሃል (Qahal) በማለት የጻፈውን ኤክሌስያ እያሉ ተርጉመውታል። በእግዚአብሔር የተመረጠ የእስራኤል ጉባኤ ማለት ነው። ይህም ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ 96 ጊዜ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የሚለው (ወይም የዚሁ ተመሳሳይ ትርጉም ያለው) ቃል 114 ጊዜ ተጠቅሷል። [12] ጌታችን አብዛኛውን ጊዜ የቤተ-ክርስቲያን ምሳሌ በሆኑ ቃላት መንግሥተ ሰማያት፣ መንግሥተ እግዚአብሔር በማለት ያስተምር ነበር እንጂ ቤተክርስቲያን የሚለውን ቃል የተናገረው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። (ማቴ 16÷18፤ ማቴ 18÷17።)

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደ እድርና እንደ ዕቅብ ሰዎች ተስማምተው በራሳቸው ፈቃድ በመሰባሰብና በመደራጀት ያቋቋማት ማኅበር ወይም የመሠረቷት ድርጅት አይደለችም። ነገር ግን ቤ/ክ ማለት መንፈስ ቅዱስ ያደረባት በእግዚአብሔር የተመረጡና የተጠሩ የቅዱሳን አበው አንድነት ማለት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር ሕዝቡን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደጠራና የተጠሩትም የልጁን መልክ እንዲመስሉና ለክብር እንደሆነ በሮሜ 8፥29 ላይ ገልጿል። ቤተ-ክርስቲን በምድር ላይ ከተመሠረቱ ማኅበራት ሁሉ አምሳያ የሌላት በእግዙአብሔር ፈቃድ ለእግዚአብሔር ዓላማ በእግዚአብሔር የተመረጡና የተጠሩ ሰዎች ጉባኤ ናት። እግዚአብሔር ሕዝቡን በማኅበር (በጉባኤ) የጠራበት የራሱ ዓላማ አለው። 13 የአማኞች (የክርስቲያኖች) ኅብረት ለምስጋናም ሆነ ለጸሎት ከግል ይልቅ በኅብረት ማድረሱ ጥቅሙ የጎላ ነው። ምክንያቱም በግሉ የደከመ ክርስቲያን በማኅበር ሲታቀፍ ይበረታል። የበረቱትን እያየ ጥንካሬው እየጨመረ ይሔዳል። በበረቱት እኅቶቹና ወንድሞቹ ጸሎት ይታገዛል። በብዙ ደካሞች መካከል አንድ ጠንካራ ክርስቲያን ቢገኝ በጸሎቱና በምክሩ ያግዛቸዋል።(ያዕ. 5፥16፣ ዕብ. 10፥25)።

ቤተ ክርስቲያን የብሉይና የሐዲስ ምእመናንን ታካትታለች። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም በመልእክቱ በሐዲስ ኪዳን የሚገኙ ምእመናን በምድር ላይ የተሰባሰቡባት ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) ሕዝበ እግዚአብሔር እንደ ደመና የከበቧት ሩጫቸውን በድል ያጠናቀቁ ምስክሮች እንዳሉ ያስገነዝበናል (ዕብ. 12፥1)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምርጥ ዕቃ ብሎ የጠራው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው ምስክሮች የተባሉት በብሉይ ኪዳን የነበሩ ከሩቅ ሆነው በእምነት መነጽርነት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከተውና ተስፋ አድርገው ተጋድሏቸውን በድል አጠናቀው ዐረፍተ ዘመን ገቷአቸው የሞቱት አባቶች ናቸው። ከቀደሙት አባቶች አንዱ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ነው። (ዕብ 11፥25) ይህም ቤተ-ክርስቲያንን የብዙ አባቶች ምስክርነት እንደከበባት ያስረዳል። ከእነዚህም አባቶች መካከል ጥቂቶቹ አቤል፣ ሄኖክ፣ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ሙሴ፣ ጌድዮን፣ ባርቅ፣ ሳምሶን፣ ዮፍታሔ፣ ዳዊት፣ ሳሙኤል.. ናቸው። (ዕብ 11፥4) እነዚህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን እንደደመና የከበቧት ሩጫቸውን በድል ያጠናቀቁ አባቶች ናቸውና የቤተ ክርስቲያን አባል ናቸው። በሐዲስ ኪዳንም ቤተ ክርስቲያን ስንል ከነገድና ከቋንቋ፣ ከአሕዛብና ከአይሁድ፣ በክርስቶስ ደም ፈርሶ አንድ ሕዝብ የሆኑትን ሕዝቦች ሁሉ ያጠቃልላል።

፫. እያንዳንዱ ክርስቲያን

በሦስተኛው ትርጉም ቤተክርስቲያን ስንል እያንዳንዱን ምእመን ማለታችን ነው። የሰው እጅ ያልሠራው የእግዚአብሔር ቤት በእግዚአብሔር ምሕንድስና የተሠራው የሰው ልጅ ሰውነት ነው። ይህ ቤተ መቅደስ ተንቃሳቃሽ፣ በክርስቶስ ደም የተገዛና የተመሠረተ፣ አምላኩን እግዚአብሔርን በፍቅር ዝቅ ብሎ ሰው በመሆን እስከሞትና መቃብር ያደረሰ በክርስቶስ ትንሣኤ ለዘለዓለም ሕይወት የትንሣኤ ተስፋ የተሰጠው፣ ቢቆሽሽ በንስሐ የሚታጠብና የሚታደስ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን የተመረጠ የክርስቲያኖች ሰውነት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ‹‹የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፣ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን›› በማለት የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠብቁ ሁሉ ለእርሱ መኖሪያ አብያተ መቅደስ መሆናቸውን አስታውቋል። (ዮሐ. 14፥23)።

የሰው ልጅ ዳግም ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ሲወለድ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ይሆናል። መንፈስ ቅዱስም ስለሚያድርበት የእግዚአብሔር ማደሪያ፣ ለእግዚአብሔር የተለየ ዙፋን፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይባላል። በዘመነ አበውም ሆነ በዘመነ ኦሪት ራሳቸውን ከርኩሰትና ከኃጢአት ለይተው ለእግዚአብሔር ክብር ከተለዩ ምእመናን ጋር እግዚአብሔር በረድኤት ነበረ። በሐዲስ ኪዳን ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ በዋጀውና በቀደሰው ሰው ላይ ማደርን መረጠ። ስለዚህ የእያንዳንዱ ምእመን (ክርስቲያን) አካል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ (ቤተ ክርስቲያን) ነው። ሮሜ. 8፥9-11

የምእመናን (የክርስቲያን) አካል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ፣ የመንፈስ ቅዱስ ቤት፣ የመንፈስ ቅዱስ ዙፋን ነው። ይህንን አካል በንጽሕና በቅድስና መያዝ የሚያድርበትን እግዚአብሔርን ማክበር ነው። እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነውና ያድርበት ዘንድ ንጹሕ ነገርን ይወዳል። በኃጢአትና በበደል በተጎሳቆለ

አካል ላይ እግዚአብሔር አያድርም፡፡ የእርሱ ማደርያ ለመሆን በኃጢአት ያደፈውን ማንነት በንስሐ ማጠብና ማንጻት ያስፈልጋል፡፡ (1ኛቆሮ. 6፥18፣ 1ኛቆሮ. 3፥16፣1ኛቆሮ 6÷19)፡፡

ሰዎች ሀሉ እንግዲህ እግዚአብሔር አንዖ፣ ለጠላትም ተሰጥቶ የነበረውን የእኛን ሰውነት በመስቀል ላይ በተከፈለ ቤዛነት በደሙ መፍሰስና በሥጋው መቆረስ በመሞቱ ለእኛ ካስረከበን እንዴት ይዘነው ይሆን? የእግዚአብሔር ቤት የሆነው ሰውነታችንን በሃይማኖት መሥርተን በምግባር አንጸን በእርግጥም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለሥጋውና ለደሙ ማደሪያ ካለበቃነው ስላአፈርስነው የእግዚአብሐየር ቤት መጠያቃችን የማይቀር ነውና ክርስቲያኖች ‹‹የቤትህ ቅናት አቃጠለኝ›› የተባለውን ቃል መዘንጋት የለብንም፡፡

ምዕራፍ ሁለት
የቤተ ክርስቲያን ዕድሜ

ቤተክርስቲያን ማለት እግዚአብሔር ግዕዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነትም ነው፡፡ በዚህም መነሻነት የቤተክርስቲያንን ታሪክ የሚያጠኑ ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያንን ዕድሜ በሦስት የተለያዩ ዘመናት ይከፍሉታል፡፡ ይኸውም ፡-

2.1. ማኅበረ መላእክት (ቤተክርስቲያን በዓለመ መላእክት)
2.2. ከአዳም እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው የደጋግ አባቶች አንድነት
2.3. ከክርስቶስ አሁን እስካለንበት ዘመን የሚደርሰው አንደነትን ያጠቃለለ ነው፡፡
የመጨረሻው የታሪክ ክፍል ሰፊ በመሆኑና አብዛኛውን የትምህርት ክፍል የሚሸፍን በመሆኑ ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ የሚታይ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ክፍሎች ግን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታቸዋልን፡፡

2.1 ማኅበረ መላእክት (ቤተክርስቲያን በዓለመ መላእክት)

እግዚአብሔር አምላክ በዕለተ እሁድ በመጀመሪያው ቀን ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል መላእክት ይገኙበታል፡፡ እግዚአብሔር መላእክትን ሲፈጥራቸው ከነ እውቀታቸው ነው፡፡ መላእክትን እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር በኃልዮ ሲፈጥራቸው በአገልግሎታቸው እንደ ንፋስ ፈጣኖች እንደ እሳት ረቂቃን አድርጎ ነው፡፡
እግዚአብሔር መላእክትን በጨለማ ከፈጠረ በኃላ ተሰወራቸው፡፡ እነርሱም ከእውቀት ጋር ስለተፈጠሩ ማነው የፈጠረን ብለው መጠየቅ ጀመሩ፡፡ በዚህን ጊዜ ከነሱ ላቅ በሎ ይገኝ የነበረው ሳጥናኤል እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ በማለት ክርክር ተነስቶ መላእክት ለሦስት ተከፈሉ፡፡

1. ከነሱ በቦታ ስለበለጠ ፈጥሮናል ያሉ፣
2. ነው ወይም አይደለም እያሉ መጠራጠር የጀመሩ፣
3. አምላካችን ራሱን እስኪገልፅልን ድረስ በያለነበት ጸንተን እንቁም ያሉ ነበሩ፡፡

ቅዱስ ገብርኤል አምላካችንን እስክናገኝ ድረስ ጸንተን እንቁም ብሎ ዓለመ መላእክትን አረጋጋ፡፡ ሳጥናኤልንም በቦታ ከላይ ስላለክ የታችኞቹን ፈጠርኩ ካልክ እኛም የታቾቻችንን ፈጠርና ማለት ሊሆን ነው፡፡ ይሄ ሊሆን ደግሞ አይችልም፡፡ ፈጣሪ ከሆንክ ፈጥረክ አሳየን በማለት መላእክቱ ለጠየቁት ምላሽ ሳጥናኤል መፍጠር አቅቶታል፡፡ በዚህም የተነሳ በመላእክቱ መካከል ጦርነት ሆነ፡፡ ሳጥናኤልን ተከትለው በተገኙ መላእክት እና በቅዱሳኑ መላእክት መካከል፡፡ በዚህን ወቅት እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ መላእክት ከወደ ምስራቅ በኩል በወረደ የብርሃን መስቀል ኃይላቸውንና ዕውቀታቸውን በማደስ ብርታትን ሰጣቸው፡፡ በኃላ በዘመን ሥጋዌ በመስቀል ዲያብሎስን ድል እንደሚያደርግ ሲያሳያቸው መስቀል ሰጣቸው፡፡ በብርሃነ መስቀሉ ብርታት ሳጥናኤልን አሸነፉ፤ ዲያቢሎስም ወደቀ፤ ክብሩንም አጣ፡፡ በመላእኩ ቅዱስ ገብርኤል ንግግር በመጽናት እግዚአብሔርን ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑ ቅዱሳን መላእክት ህብረት ስብስብ ቤተክርስቲያን ይባላል፡፡

2.2. ከአዳም እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ

ከአዳም እስከ አዲስ ኪዳን መመስረት ወቅት ያለው በአራት የተከፈለ ዘመን ነው። እነዚህም፡-

1. ዘመነ አበው
2. ዘመነ መሳፍንት
3. ዘመን ነገሥት
4. ዘመነ ነብያት/ካህናት/ሲባሉ እያንዳንዱን በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

⌗ 2.2.1 ዘመነ አበው

ዘመነ አበው የሚባለው ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ዘመን ነው። ዘመኑንም ሊቃውንት ከሁለት ከፍለው ያሳያሉ። ከአዳም እስከ ጥፋት ውኃ 2256 ዓ.ዓ እንዲሁም ከኖኅ እስከ ሙሴ 1588 ዓ.ዓ በጥቅሉ 3844 ዓመታትን ያስቆጠረ ዘመን ነው። በአጠቃላይ 22 የሆኑት አባቶች አርዕስተ አበው በመባልም ይታወቃሉ። አርእስተ አበው የሃረገ ትውልድ እና የመልካም ሥራ መነሻ በመሆን ያሳዩት የእምነትና የምግባር ፅኑነት በታሪካቸው ውስጥ ጉልህ ድርሻ ይዞ ይኖራል።

በዘመነ አበው አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ከፍታ ወደ አለው ተራራ በመውጣት መስዋዕትን ያቀርቡ ነበር። በዘመኑ ሰዎች ይመሩ የነበረው በሕገ ልቦና ነው። ይህ ዘመን ሕገ ልቦና የተባለው መጽሐፍ ሳይፃፍላቸው በልቦናቸው ባስቀመጠላቸው ሕግ ይመሩና ያምኑ ከነበረው አበው ጋር እግዚአብሔር የነበረው መንፈሳዊ ግንኙነት ስለሆነ ነው።
አርእስተ አበው በመባል የሚታወቁት 22 አባቶች የሚከተሉት ናቸው።

1.አዳም	2/ሴት	3/ሄኖስ	4/ቃይናን	5/መላልኤል	6/ያሬድ
7.ሄኖክ	8.ማቱሳላ	9.ላሜሕ	10.ኖኅ	11.ሴም	12.አርፋክስድ
13.ሳላ	14.ዔቦር	15.ፋሌቅ	16.ራግው	17.ሴሮሕ	18.ናኮር
19.ታራ	20.አብርሃም	21.ይስሐቅ	22.ያዕቆብ		

በዘመነ አበው ከነበሩ አባቶች መካከል የተወሰኑትን ታሪክና ከአንዳንዶቹም የምንማራቸውን ቁምነገሮች ጨምሮ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- አዳም

አዳም ማለት ከመሬት የተፈጠረ ያማረ፣ መልከ መልካም ማለት ነው። የሥነ ፍጥረት መካተቻ በሆነች በዕለተ ዓርብ በምድር መካከል በምትገኝ ኤልዳ በተባለች ስፍራ በነግህ የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ በእግዚአብሔር አርአያና መልክ ተፈጠረ። ዘፍ 1÷27፤ ኩፋሌ 5÷6
እግዚአብሔር አምላክ 'ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት' አለ። ዘፍ 2÷18። አዳም ለእንስሳት፣ ለሰማይ ወፎች እና ለምድር አራዊት ሁሉ ተባዕትና አንስት ሆነው ሲመጡ ስም ያወጣላቸው ነበር። ነገር ግን ለአዳም እንደ እራሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር። እግዚአብሔር በአዳም ላይ እንቅልፍ አምጥቶበት ፈፅሞ ሳይተኛ ፈፅሞም ሳይነቃ ከጎኑ አንድ አጥንት ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። ከአዳም የወሰዳትን አጥንት የአስራ አምስት ዓመት ሴት አድርጎ ፈጠራት። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር የባሕርይ ደግነት የተነሳ እርሱን ለማመስገንና ክብሩን ለመውረስ ተፈጠሩ። ኩፋሌ 4÷3-5። እግዚአብሔር ለአዳም ረዳት የፈጠረለት ስለ ሦስት ነገሮች ሲል ነው፡- ዘርን ለማብዛት፣ ከዝሙት እንዲጠበቅ እና ረዳት እንድትሆነው።

- እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም ሰባት ሀብታትን የሰጠው ሲሆን እነዚህም፡-
  1. ሀብተ መንግሥት፡- (የማስተዳደር)
  2. ሀብተ ክህነት፡- (የመቀደስ፣ የመባረክ፣ መስዋዕት የማቅረብ)
  3. ሀብተ ትንቢት፡- (የሚመጣውን የመናገር)

4. ሀብተ መዊዕ፡- (የማሸነፍ)
5. ሀብተ ኃይል፡- (የጥንካሬ)
6. ሀብተ ፈውስ፡- (የማዳን፣የመፈወስ)
7. ሀብተ ዝምሬ፡- (የመዝሙር)

እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ከፈጠራቸው በኃላ አዳምን በ40ኛው ቀን ሔዋንን ደግሞ በ80ኛው ቀን ይገሏትና ይጠብቋት ዘንድ ወደ ገነት አስገባቸው። በገነት ውስጥ ሶስት ዓይነት ዛፎች ነበሩ፡-

1.ዕፀ መብል፡- እንዲበሉት የተፈቀደላቸው ምግብ ነው፡

2.ዕፀ በለስ፡- እንዳይበሉት የታዘዙት ነው።

3.ዕፀ ሕይወት፡- እንደ እግዚአብሔር ፈቃደ ቢመገቡት የዘላለም ሕይወት የሚሠጥ ምግብ ነው።

ዕፀ በለስን እንዳይበሉ የታዘዙበት ሕግ አዳም ፈጣሪ እንዳለው የሚያውቅበት፣ ለፈጣሪ ያለውን ፍቅር የሚገልፅበትና ተገዥነቱን የሚያሳይበት ነው። አዳምና ሔዋን ይህን ሕግ በማክበር በገነት ውስጥ ለሰባት ዓመት ከሁለት ወር ከአስራ ሰባት ቀን ኖሩ። ከዚያ በኃላ ሰይጣን በእባብ አድሮ አሳሳታቸው። አትብሉ የተባሉትን ዕፀ በለስን በሉ፤ ሕጉን አፈረሱ፤ ከገነትም ተባረሩ። ዘፍ 3÷1፤ ዘፍ 3÷22-24። ከገነት ከተባረሩ በኃላ በደብር ቅዱስ ይኖሩ ነበር። አዳምና ሔዋን በሰሩት ኃጢአት በመፀፀታቸውና በንስሐ በመመለሳቸው እግዚአብሔር አምላክ 5500 ዘመን ሲፈፀም ሰው ሆኖ በመወለድ እንደሚያድናቸው ቃልኪዳን ገባላቸው። ዘፍ 3÷15-22። አዳምና ሔዋን በምድር ላይ ዘርን ተክተዋል። አዳም በተፈጠረ በ930 ዓመቱ አረፈ።

- አቤል

አቤል ማለት የዋህ ማለት ሲሆን የአዳምና የሔዋን ሁለተኛ ልጅ ነው። ከሰው ልጅ ፍጥረት የመጀመሪያ ልጅ የሆነ ቃየል የሚባል ታላቅ ወንድም ነበረው። ዘፍ 4÷1-2። ሔዋን ከቃየልና አቤል ጋር መንትያ የሆኑ ሴቶችን የወለደች ሲሆን የአቤል መንትያ አቅሌማ ስትባል የቃየል መንትያ ደግሞ ሉድ ትባላለች። አቤል በግ ጠባቂ ሲሆን ቃየል ደግሞ ገበሬ ነበር። አዳም ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት በተባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ዘር አራርቆ ለማጋበት ወሰነ። በዚህም መሰረት ከቃየል ጋር የተወለደችውን መንትያ ለአቤል፣ ከአቤል ጋር የተወለደችውን ደግሞ ለቃየል ሰጠ። ቃየል ለሱ የተሰጠችው አቅሌማ እንደ ሉድ መልከ መልካም ባለመሆኗ በውሳኔው ተናደደ። ስለዚህም አዳም መስዋዕት ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡና የአምላክን ፈቃድ እንዲጠይቁ አዘዛቸው። አቤል እግዚአብሔር በባሕሪው ንፁሕ ስለሆነ ንፁሕ ልብ ንፁሕ መስዋዕት ይወዳል ብሎ ከበጎቹ በኩር እና ስብ የሆነ መስዋዕት አቀረበ። ቃየል ግን እግዚአብሔር የሚቀርብለትን መስዋዕት አይበላም በሚል ትዕቢት ንፁሕ ያልሆነ መስዋዕት አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና መስዋዕቱ ተመለከተ። እግዚአብሔር ወደ ቃየልና ወደ መስዋዕቱ ባለመመልከት ውሳኔ አስተላለፈ። በዚህም ቃየል እጅግ ተናደደ፤ ፊቱም ጠቆረ። ዘፍ 5÷3-5፤ ዕብ 11÷4። ከዚህ በኃላ ቃየል ወንድሙን 'ና ወደ ሜዳ እንሂድ' አለው። ውሃ ለመጠጣትም ወደ ወንዝ ወረዱ። አቤል ውሃ ለመጠጣት ጎንበስ ባለበት ቃየል ገድርኤል የተባለው ሰይጣን እንዳስተማረው አቤልን በድንጋይ መትቶ ገደለው። በአቤልም ሞት ተጀመረ። ዘፍ 4÷8፤ ኩፋሌ 5÷9፤ ሄኖክ 19÷19

ቃየል አቤልን በመግደሉ የሚከተሉት ጉዳቶች ደርሰውበታል።

1. ኩብላይና ተቅበዝባዥ ሆነ፤
2. ምድር ፍሬዋን እንዳትሰጠው ተረገመ፤
3. በደጋግ አባቶች የዘር ሐረግ እንዳይቆጠር ሆነ።

- ሴት

ሴት ማለት ምትክ ማለት ነው። የአዳምን የሔዋን ልጅ ነው። አዳም በአቤል መሞት ያዝን ነበር። እግዚአብሔርም የአዳምን ሐዘን ተመለከተ። አዳም ሔዋንን በግብር አወቃት። ወንድ ልጅንም ወለደችለት። ስሙንም ሴት አለችው። የሴት ልጆች በጎበረት፣ በቅድስና፣ በንፅሕና ልክ እንደ መላእክት በመኖራቸው የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠሩ ነበር። ዘፍ 4÷25-26፤ ዘፍ 5÷3። ቃየልም ወንድሙን ከገደለ በኃላ ከዔደን በስተምስራቅ በምትገኝ በኖድ ምድር ተቀመጦ ልጆችን ወለደ። የቃየል ልጆች አካሔዳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ስላልነበር የሰው ልጆች የሚል ስያሜ ተሰጣቸው። ዘፍ 4÷16። ሴትም በ912 ዓመቱ አረፈ።

◈ ሄኖስ

‘ለሴት ደግሞ ወንድ ልጅ ተወለደለት ስሙንም ሄኖስ አለው።’ ዘፍ 4÷26 ሄኖስ ራሱን ከቃየል ልጆች ዐመፃ ጠብቆ እግዚአብሔርን በማመን ለእርሱም ለመገዛት የተዘጋጀ ልብን ገንዘብ ያደረገ ነብይ ነበር። ሄኖስ በደብር ቅዱስ /ኤልዳ/ ሆኖ የአባት የአያቱንና የሚች አጎቱን የአቤልን ሥርዓት በማፅናት የተወደደ መሥዋዕት ለፈጣሪ ሲያቀርብ የነበረ፣ ከሌሎች ወንድሞቹ በጥበብ ለየት ብሎ የታየ፣ በመንፈስ እግዚአብሔር የተቃኘ፣ ለፍጥረታት የሚራራ አባት ነበር። ሄኖስ ለስመ እግዚአብሔር ክብር ቀናዒ ስለነበር በፍጡሩ በአቤል ደም ይቀርብ የነበረው መሃላ እግዚአብሔርን ስለማክበር በፈጣሪ ስም እንዲሆን መንገድ ያሳየ ነበር። ኩፋሌ 5÷18። እግዚአብሔርም ስሙን ሊያከብር ልቡን ላተጋው ለሄኖስ መስሎ፣ አመስጥሮ፣ ተጠቦ እንዲያከብረው ፍላጎቱ ነበርና 22ቱን አሌፋት በጸፍጸፈ ሰማይ ገልጾለታል። ሄኖስ እግዚአብሔርን የመወደድና የማክበር ፍላጎቱ ስሙን ለስመ መጠሪያ በማድረግ፣ ስሙን በመሃላ በመዘከር ታውቋልና ስሙን የበለጠ በማከበር ክብርን እንዲያገኝ ለሄኖስ ይህን ጥበብ ገለጸለት። ሄኖስ በ905 ዓመቱ አረፈ። ዘፍ 5÷11።

◈ ያሬድ

ያሬድ ከአዳም ጀምሮ 6ኛ ትውልድ ሲሆን የስሙ ትርጓሜም ርደት /መውረድ/ ማለት ነው። ስያሜውንም ያገኘው በዘመኑ በደብር ቅዱስ ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው በጸሎትና በስግደት በመዓልትና በሌሊት አጥብቀው ከመትጋታቸው የተነሳ ትጉሃን ሰማይ /የሰማይ መላዕክት/ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው የሴት ልጆች የቃየል ወደሚሆኑት በአመንዝራነት ተስበው በመውረዳቸው ነው። ከዚህ ጊዜ በኃላ የሴት ልጆችና የቃየል ልጆች በኃጢአት አንድ አካል ሆነዋል። ከነርሱም እጅግ የባሱ ኃጥአንን በመውለድ ዓለምን ለጥፋት አዘጋጅተዋል። እግዚአብሔርም ሰውን በመፍጠሩ የተጸጸተበት ዘመን ነው። ያሬድ በ962 ዓመቱ አረፈ። ዘፍ 5÷20።

◈ ነብዩ ሄኖክ

ሄኖክ ማለት ተሐድሶ (አዲስ) ማለት ነው። አባቱ ያሬድ እናቱ ባረካ ይባላሉ። ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ ትውልድ ነው። ዘፍ 5÷18፤ ኩፋሌ 5÷22፤ ይሁዳ 1፣14። ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ በዘመኑ ከምግብ ተከልክሎ በጾም በጸሎትና በአምልኮት ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት የሚመስለው ሰው አልነበረም። በእምነቱና በቅንነቱ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ የተመሰከረለት አባት ነው። በ4014 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በስሙ የሚጠራውን መፅሐፍ ጽፏል። ዘፍ 5÷24፤ ኩፋሌ 5÷22-26፤ ዕብ 11÷5። ሄኖክ በእግዚአብሔር ያመነና እንደ ፈቃዱ የኖረ ሰው በመሆኑ በሥጋ ሞትን ሳያይ ለስድስት ዓመት በእግረ ገነት ቆይቶ በሰባተኛው ዓመት በ365 ዓመቱ ተሰወረ። በሕይወት እንዳለ እግዚአብሔር ወደ ራሱ ወሰደው። ሄኖክ ሁለቱ ወይራዎች ተብለው ከተገለፁ ቅዱሳን አንዱ ነው።
ስለዚህም በአቤል ሞት እንደታወቀው በሄኖክም ዘለዓለማዊ ሕይወት የተረዳ ሆነ። ሄኖክ በብሕትውና በመኖሩ በኩረ ባሕታውያን ይባላል። ኩፋሌ 5÷30፤ ሲራክ 44÷6፤ ራዕይ 11÷4።

◈ ኖኅ

ኖኅ ማለት ዕረፍት ማለት ነው። ዘፍ 5÷29። አባቱ ላሜህ እናቱ ቤቴናስ ይባላሉ። የአዳም 10ኛ ትውልድ የሆነው ኖኅ በትውልዱ ጻድቅ ፍፁምም ሰው ነበር። በእርሱ ዘመን የነበሩ ሕዝቦች ግን በኃጢአትን በክፋት የተጠመዱ ነበሩ። ዘፍ 6÷9፤ ኩፋሌ 6÷1።
ኖኅ አምስት መቶ ዓመት ከሆነው በኃላ ከሚስቱ አምዛራ ሴምን፣ ካምንና ያፌትን ወለደ። ዘፍ 6÷11፤ ኩፋሌ 6÷7-8። ምድር በሰዎች ኃጢአትና ክፋት በተሞላች ጊዜ እግዚአብሔር ለኖኅ የጥፋትን ውኃ እንደሚያመጣ አስጠነቀቀው። ኖኅ ቤተሰቡ እንዲሁም ሕያው ነፍስ ካላቸው ተባዕትና አንስት ፍጥረታት ከሚበሉት ሰባት ሰባት ከማይበሉት ሰባት ሰባት የሚድኑበት መርከብ እንዲያዘጋጅ ታዘዘ። ኖኅ በእምነት የደመና ክፋይ በማይታይበት ደረቅ ዘመን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ታላቅ የሆነ መርከብ አዘጋጀ። በዘመኑ ለነበሩት ሁሉ ከጥፋት ይድኑ ዘንድ ጽድቅንም ያስተምር ነበር። ዘፍ 6÷13-22።
ኖኅ ስድስት መቶ ዓመት በሆነው ጊዜ የጥፋት ንፍር ውኃ (ማየ አይኅ) መጣ። ኖኅና ቤተሰቡ እንዲሁም ሕያው ነፍስ ያላቸው ፍጥረታት ወደ መርከቢቱ ገቡ። የጥፋት ውሃ አርባ ቀንና ሌሊት ዘነበ። ውኃውም ወደ ላይ አስራ አምስት ክንድ ከፍ ከፍ አለ፤ መቶ ሃምሳ ቀን በምድር ላይ ሞላ። ከኖኅ ጋር ወደ መርከቢቱ ከገቡት በስተቀር የዳነ ፍጥረት አልነበረም። እግዚአብሔር ስለኖኅ የጥፋትን ውኃ ከምድር

አደረቀ። መርከቢቱም በአራራት ተራሮች ላይ ተቀመጠች። ዘፍ 7÷8-። ኖኅም ከመርከቢቱ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ከአራራት ተራሮች አንዱ በሆነው በታቦር መስዋዕትን አቀረበ። ዘፍ 8÷20። እግዚአብሔርም ምድርን ዳግመኛ በውኃ ላያጠፋ ከኖኅ እና በኖኅ አማካይነት ከሰው ልጆች ጋር ቃልኪዳን አደረገ። ለዚህም ምልክት ይሆን ዘንድ ቀስተ ደመና ተገለጠ። እግዚአብሔርም ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት አላቸው። ዘፍ 9÷8-12።

ከጥፋት ውኃ በኃላ ኖኅ ገበሬ ሆኖ ወይን ተከለ። ከወይን ጠጁም ጠጥቶ ሰከረ። ካምም የአባቱን ነውር ገለጠ። በዚህም ልጁ ከነዓን ተረገመበት። የአባታቸውን ነውር ባለማጋለጥ የጠበቁት ሴምና ያፌት ተባረኩ። ዘፍ 9÷20-27። ኖኅ ለልጆቹ ምድርን አከፋፈላቸው። ኖኅ በ950 ዓመቱ አረፈ።

ኖኅ የሰራት መርከብ የቤተክርስቲያንና የእመቤታችን ምሳሌ ናት። የኖኅ መርከብ በውስጧ የነበሩትን ነፍሳት ሁሉ ከጥፋት ውኃ እንዳዳነች ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ አምነው ወደ እርሷ የገቡትን ከሞተ ነፍስ ከኃጢአት ታድናቸዋለች። ይህች አማናዊት በክርስቶስ የተመሰረተች ቤተክርስቲያን ምሳሌዋ ከምትሆን ከኖኅ መርከብ ትበልጣለች። ምክንያቱም የኖኅ መርከብ ያዳነችው ከሞተ ሥጋ ነው። ቤተክርስቲያን ግን የምታድነው ከሞተ ነፍስም ነውና። በኖኅ መርከብ ውስጥ የነበሩት አውሬዎች ሲወጡ ባሕርያቸው አልተለወጠም። ወደ ቤተክርስቲያን የሚገቡ ግን ቀማኛው መጽዋች ዘማዊው እንደ ድንግል ይሆናሉ። በመርከብ ውስጥ ያሉት ሲድኑ ከውጭ የነበሩት ግን በጥፋት ውኃ ተደምስሰዋል። በክርስቶስ አምነው ወደ ቤተክርስቲያን የገቡ ከዘላለማዊው መቅሰፍት ይድናሉ። በክርስቶስ አምነው ወደ ቤተክርስቲያን ያልገቡት ግን የመዳን ተስፋ የላቸውም። በኖኅ የተሰራችው መርከብ ሦስት ክፍል ነበራት፤ በክርስቶስ የተመሰረተችው ቤተክርስቲያንም ሦስት ክፍሎች (መቅደስ፣ ቅድስት፣ ቅኔ ማኅሌት) አሏት።

- አብርሃም

አብርሃም ማለት የብዙዎች አባት ማለት ነው። አብርሃም ከመባሉ አስቀድሞ አብራም በሚል ስያሜ ይታወቃል። አባቱ ታራ ሲባል እናቱ ደግሞ ኤድና ትባላለች። አብራሃም አስቀድሞ ሦራ በኃላም ሣራ የብዙዎች እናት ተብላ የተጠራች ባለቤት ነበረችው። ዘፍ 11÷27። ከአዳም ጀምሮ ስንቆጥር አብርሃምን 20ኛ ትውልድ ላይ እናገኘዋለን። ታራ በፍላጎቱ ያይደል ጣኦት አምላኪ ነበር፤ አብርሃምም የአባቱን ጣኦት እያወጣ ይሸጥ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ጣኦት ለመሸጥ ወደ ገበያ ወጣ። በጉዞው ስለደከመው ከድካሙ ያበረታው ዘንድ የያዘውን ጣኦት ለመነ። ነገር ግን የያዘው ጣኦት ከድካም የሚያበረታ፣ ጥምን የሚቆርጥ፣ ረሐብን የሚያስታግስ ሆኖ አላገኘውም። በዚህም የተነሳ በገበያ መሃል ጣኦቱን እያቃለለ ቢዞር ሕዝቡ ለመግዛት ፈቃደኛኛ አልሆነም። አብርሃምም ዓይን እያለው የማያይ፣ ጆሮ እያለው የማይሰማ፣ አፍ እያለው የማይናገር... ብሎ ጣኦቱን ሰበረው። ከዚህ በኃላ የተያዩ ሥነ-ፍጥረታት አምላክ መሆን አለመቻላቸውን ለማወቅ ተመራመረ። በመጨረሻ እነዚህ ሥነ-ፍጥረታት አምላክ እንዳልሆኑ ሲገነዘብ የፀሐይ አምላክ ተናገረኝ ብሎ ለመነ። እግዚአብሔርም ተገለፀለት። አብርሃም በሥነ-ፍጥረት ተመራምሮ አምላኩን ስላወቀው ሥርወ ሃይማኖት ይባላል።

እግዚአብሔርም አብርሃምን 'ከአገርህ ከዘመዶችህ ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ...የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ' አለው። ዘፍ 12÷1-3። አብርሃም ከሚስቱ ሣራ እና ከወንድሙ ልጅ ሎጥ ጋር በመሆን ከካራን ወጥቶ ወደ ከነዓን ምድር ገባ። ዘፍ 12÷5። በዚያም ከተቀመጠ ከተወሰነ ጊዜያት በኃላ በምድር ላይ ረኃብ ስለሆነ አብርሃም ወደ ግብፅ ወረደ። ሣራ ውብ በመሆኗ ምክንያት የግብፅ ሰዎች ስለእርሷ ብለው እንዳይገድሉት በማሰብ አብርሃም እህቱ ናት አለ። የግብፅ ፈርዖን አለቆችም ሣራን ወደ ፈርዖን አገቧት። ፈርዖንም ለአብርሃም ስለ እርስዋ መልካም አደረገለት፤ ለእርሱ በጎችም በሬዎችም አህዮችም ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎችም ግመሎችም ነበሩት። እግዚአብሔርም በአብርሃም ሚስት ምክንያት ፈርዖንንና የቤቱን ሰዎች በታላቅ መቅሠፍት መታ። ፈርዖንም አብርሃምን ከግብፅ እንዲወጣ ከብቱን ሁሉ ሸኘለት።

አብርሃም ከግብፅ ከወጣ በኃላ እጅግ ሃብታም ሆነ። የወንድሙ ልጅም እንደዚሁ በለፀገ። በአንድነትም ይቀመጡ ዘንድ ምድር አልበቃቸውም። በዚህም የተነሳ አብርሃምና ሎጥ ተለያዩ። ሎጥም በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውን አገር ሁሉ መረጠ፤ እስከ ሰዶምም ድረስ ድንኳኑን አዘዋወረ። የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ። አብርሃም በከነዓን ምድር ተቀመጠ።

አሥራ ሁለት ዓመት ለኮሎዶጎምር ተገዝተው የነበሩ አራት ነገሥታት (ሰዶምን ጨምሮ) በአሥራ ሦስተኛውም ዓመት ዐመፁ። በአሥራ አራተኛውም ዓመት አምስቱ ነገሥት ኮሎዶጎምር አራቱ የዐመፁ ነገሥታትን ድል አደረጉ። ሎጥንና ከብቶቹንም ማረኩ። አብርሃምም ይህን በሰማ ጊዜ በቤቱ የሚገኙ ሦስት መቶ አስራ ስምንት ብላቴኖች አሰልፎ በመሔድ ነገሥት ኮሎዶጎምርን ድል መታ። ሎጥንና ከብቶቹን ሁሉ አስመለሰ። አብርሃም ጠላቶቹን አሸንፎ ሲመለስ ከሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ አኮቴት ጽዋዐ በረከት ተቀበለ። አስራትንም ለመልከ ጼዴቅ አወጣ። ዘፍ14÷12-18። ከዚህ ነገር በኃላ እግዚአብሔር ለአብርሃም በራዕይ ተገለጠለት። አበርሃምም 'አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ምንን ትሠጠኛለህ› እኔ ያለልጅ እሄዳለለሁና' አለ። እግዚአብሔርም ዘሩን እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ምድርም አሸዋ እንደሚያበዛለት ነገረው። ዘፍ15÷1-6 የአብርሃም ዘሮች በግብፅ ምድር ለአራት መቶ ዓመታት እንደሚኖሩና እግዚአብሔርም ከግብፃውያን እጅ እንደሚያድናቸው የተገለፀው በዚህ ጊዜ ነው። ዘፍ 15÷12-15።

የአብርሃም ሚስት ሣራ ልጅ አልወለደችም ነበር። እርሷም ስምዋ አጋር የተባለች ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት። ሣራ መካን መሆኗን ባወቀች ጊዜ አብርሃምን ወደ አጋር እንዲገባ አደረገች። አብርሃምም ወደ አጋር በመግባት እስማኤልን ወለደ። ዘፍ16÷1-6። እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ቃልኪዳንን አደረገ። የቃልኪዳኑ ምልክትም ግዝረት ነበር። አብርሃምም ልጁን እስማኤልን በቤቱም የተወለዱትን ወንዶች ሁሉ ገረዘ። እርሱም በ99 ዓመቱ በዚያኑ ቀን ተገረዘ። ዘፍ17÷9-14።

አብርሃም እንግዳ ተቀብሎ በማስተናገድ የታወቀ በመሆኑ ጥንተ ጠላታችን ዲያቢሎስ በዚህ ነገር ሊፈትነው ተነሳሳ። ዲያቢሎስ እራሱን በሰው አምሳል በመግለፅና ሰውነቱን በደም በመቀባባት ወደ አብርሃም ድንኳን በሚወስድ መስቀለኛ መንገድ ተቀመጠ። ከአብርሃም ዘንድ ለእንግድነት የሚሄዱ ሰዎችን #አብርሃም ፀባዩን ቀይሯል ለእንግድነት ብሄድ እንዲህ አድርጎ በመደብደብ መለሰኝ; በማለት ይመልሳቸው ጀመር። አብርሃም ያለእንግዳ ምግብ ስለማይቀምስ በረሃብ እንዲጎዳ አስቦ ነበር። አብርሃም በድንኳኑ ደጅ ተቀምጦ ሳለ ቅድስት ሥላሴ በመምህሬ የአድባር ዛፍ በአረጋውያን አምሳል ተገለጡለት። አብርሃምም በድንኳኑ ውስጥ አስተናገዳቸው። ቅድስት ሥላሴም በዓመቱ ከቃልኪዳን ሚስቱ ልጅ እንደሚወልድ ነገሩት። አብርሃምና ሣራ በእድሜያቸው ፈፅመው አርጅተው ነበር። ሣራም ልጅ የመውለዷን ብስራት በሰማች ጊዜ በሴቶች የሚሆነው ልማድ ቀርቷት ነበርና ሳቀች። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ባለመኖሩ በዓመቱ ይስሐቅ ተወለደ። የአብርሃምም ዘር በይስሐቅ ተጠራለት። ዘፍ 18÷1-15፤ ዘፍ 21÷1-7።

ይሄ የአብርሃም ድንኳን የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን በአብርሃም ድንኳን ሥላሴ ገብተውበታል፤ እመቤታችንም በፀነሰች ጊዜ ሦስቱም አድረውባታል። አብ ለማፅናት፤ ወልድ በተለየ አካሉ ለተዋሕዶ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ለማንጻት (ኃጥያት ኖሮባት ሳይሆን ወንድ ከማወቅ፣ ዘርን ከመቀበል፣ ድንግልናን ከማጣት ለጌታ እነዚህ ነገሮች አይስማሙትምና ከለከላት ለማለት ነው)።

የአብርሃም የወንድም ልጅ ሎጥ በሰዶም ከሚስቱና ከሁለት ሴት ልጆቹ ጋር ይኖር ነበር። ሰዶምም በከፍተኛ ኃጢአት የተሞላች ከተማ ነበረች። እግዚአብሔርም ሰዶምን የሚያጠፋበት ጊዜ መቃረቡን ለአብርሃም አማከረው። አብርሃምም በሰዶም ውስጥ ስለሚገኙ ጻድቃን ብሎ እግዚአብሔር ከተማይቱ እንዳያጠፋ ምልጃን አቀረበ። ነገር ግን በሰዶም ውስጥ ከሎጥ በስተቀር አንድም ጻድቅ አልተገኘም። ሰዶምና በውስጧ ያሉት በሙሉ ከመጥፋታቸው በፊት ሎጥ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር በመሆን በመላእክት መሪነት ከከተማይቱ ወጡ። የሎጥ ሚስትም መላእክቱ ከተማይቱን ዞራችሁ አትመልከቱ ያሉትን ቃል ባለማክበሯ የጨው ሃውልት ሆና ቀረች። ሰዶምና ገሞራም በእሳት ዲን ጠፉ። ዘፍ 18÷22፤ ዘፍ 19÷1። ሎጥ በሸመገለ ጊዜ ሴት ልጆቹ ወንድ ስለማናውቅ ዘር ላይቀርልን ስለሆነ ከአባታችን ዘር እናስቀር ብለው ተማከሩ። አባታቸውንም የወይን ጠጅ በማጠጣትና በማስከር ታላቂቱ ሴት ሞአብን ስትወልድ ታናሺቱ ሴት ደግሞ አሞንን ወለደች። ዘፍ 19÷30-38።

ይስሐቅም እያደገ ሄደ። ወላጆቹም ተደሰቱበት። እግዚአብሔርም አብርሃምን ፈተነ። በእርጅና የወለደውን ብቸኛ የተስፋ ልጁን መስዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብ ጥያቄ ቀረበለት። አብርሃም አንድ ልጁን ይስሐቅን በሞርያ ተራራ ለመስዋዕትነት በእምነት አቀረበ። ዕብ 11÷18-19። እግዚአብሔርም የአብርሃምን የእምነት ፅናትና ታዛዥነት ተመለከተ። አብርሃምም በልጁ ፈንታ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ ያገኘውን

አንድ በግ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጎ አቀረበ፡፡ አብርሃም በመልካም ሽምግልና በ175 ዓመቱ አረፈ፡፡

በዘመነ ሕገ ልቡና ለቤተክርስቲያን ምሳሌነት ከሚጠቀሱ መካከል ክህነተ መልኬ ጼደቅ ይገኝበታል፡፡ ካህኑ መልከ ጼዴቅ የሰያሜ ካህናት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ አብርሃም ያቀረበው ጎብስትና ወይንም ዛሬ ካህናት በቤተክርስቲያን ለሚያቀርቡት መስዋዕተ ሐዲስ /የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም/ ምሳሌ ነበር፡፡ መዝ 109÷1-4፡፡ አበ ብዙኃን አብርሃም የምዕመናን (የክርስቲያኖች) ምሳሌ ነው፡፡

- ይስሐቅ

የይስሐቅ የስሙ ትርጓሜ ይስቃል ማለት ነው፡፡ አብርሃምና ሣራ በእርጅና እድሜያቸው የወለዱት ልጅ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም 'ዘርህ ከአብራክህ በሚከፈለው በይስሐቅ ይጠራልሃል' ያለው የተስፋ ቃል ተፈፀመ፡፡ በዚህም ይስሐቅ የተስፋው ልጅ ተባለ፡፡ ዘፍ 21÷1-፡፡ ይስሐቅ በተወለደ በስምንተኛው ቀን የቃልኪዳን ምልክት የሆነውን ግዝረት ፈፀመ፡፡ ይስሐቅ ታዛዥ ሰው ስለነበር አብርሃም በሞርያ ተራራ ላይ ለመስዋዕትነት ባቀረበው ወቅት በፍፁም ትሕትና ፈቃደኝነቱን ገልፆ ነበር፡፡ ዘፍ 22÷1-8፡፡

አብርሃም በሸመገለ ጊዜ ልጁ ይስሐቅ ሚስት እንዲያገባ ፈለገ፡፡ ስለዚህም ኢያውብር የተባለውን ሎሌውን ጠርቶ 'ለልጄ ለይስሐቅ ከሃገሬና ከተወላጆቼ ሚስት እንድትወስድለት አምልሃለሁ' አለው፡፡ ሎሌውም ሚስት ትሆነው ዘንድ የባቱኤልን ልጅ ርብቃን አመጣለት፡፡ ይስሐቅም ርብቃን አገባ፡፡ ይስሐቅ እናቱ ሣራ በሞተች ጊዜ ከነበረው ሃዘን ርብቃን ካገባት በኃላ መፅናናትን አገኘ፡፡ ዘፍ 24፡፡

ርብቃ መካን ስለነበረች ለይስሐቅ ልጅ አልወለደችለትም ነበር፡፡ ይስሐቅም ስለሚስቱ ስለ ርብቃ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም ተለመነው፤ ፀሎቱንም ሰማ፡፡ ስለዚህም ርብቃ ፀነሰች፡፡ ይስሐቅም ከሚስቱ ኤሳውና ያዕቆብ የተባሉ መንታ ልጆችን ወለደ፡፡ እግዚአብሔርም የአብርሃምን ተስፋ በማፅናት ይስሐቅን ባረከለት፡፡ ዘፍ 25÷19-26፣ 26÷12-14፡፡ ይስሐቅም በመልካም ሽምግልና በ180 ዓመቱ በማረፍ ወደ አባቱ አብርሃም ተከማቸ፡፡ ዘፍ 35÷28፡፡

- ያዕቆብ

የያዕቆብ የስም ትርጓሜ ተረከዝን ያዥ፣ አሰናካይ ማለት ነው፡፡ ርብቃ ለይስሐቅ ከወለደችለት መንታዎች ታናሹና የታላቅ ወንድሙን ተረከዝ ይዞ የወጣ የአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባት የሆነ ነው፡፡ ሁለቱ መንታዎች ባደጉ ጊዜ ዔሳው አዳኝ ሲሆን ያዕቆብ ግን እናቱን በቤት የሚያገለግል ሆነ፡፡ ይስሐቅ ዔሳው ካደነው ይበላ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ዔሳውን ይወድ ነበር፡፡ ርብቃ ደግሞ በቤት የሚያገለግለውን ያዕቆብን ትወድ ነበር፡፡ ዘፍ 25÷19-26፡፡

ከዕለታት በአንድ ቀን ዔሳው ከአደን መልስ ርቦት ሲመጣ ያዕቆብን ቀይ የምስር ወጥ ሲያዘጋጅ ያገኘዋል፡፡ ዔሳውም ስለራበው ከምስር ወጡ ያበላው ዘንድ ያዕቆብን ጠየቀ፡፡ ያዕቆብ ከብኩርና የሚገኘውን በረከት እያወቀ ያደገ ስለነበረ ዔሳውን ብኩርናህን ከሸጥክልኝ እሰጥሀለሁ አለው፡፡ ዔሳውም እኔ በርኃብ ተይዤ ብኩርናዬ ምኔ ነው አለ፡፡ ያዕቆብ ዔሳው ያቃለላትን ብኩርና በምስር ወጥ ገዛ፡፡ ይህም ታሪክ ምሳሌነት ያለው ነው፡፡ ኤሳው የእስራኤል ያዕቆብ የአሕዛብ ብኩርና የሃይማኖት ምሳሌ ነው፡፡ ኤሳው ብኩርናውን በመብል እንደሸጠ አሕዛብ በወንጌል አምነው ክብር የማግኘታቸው ምሳሌ ነው፡፡

ይስሐቅም በስተእርጅናው ዓይኑ ደክሞ ሳለ ታላቅ ልጁን ለምርቃት በጠራ ጊዜ ያዕቆብ የወንድሙን በረከት አባቱን በማታለል ተቀበለ፡፡ በዚህ ምክንያት በልቡ ቂም ያዘበት፡፡ ዔሳውም ወንድሙን ሊገድል መፈለጉን የተረዳችው ርብቃ ያዕቆብ ሸሽቶ ወደ ወንድሟ ሀገር እንዲሄድ መከረችው፡፡ ስለሆነም የይስሐቅን ምርቃት በመቀበል ያዕቆብ ከዔሳው በመሸሸና በዚያውም ሚስት ለማግባት ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ሄደ፡፡ ዘፍ 25÷27-34፣27፤ ኩፋሌ19÷16፤ ኩፋሌ 19÷57፡፡

ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ተጓዘ፡፡ ሎዛ የምትባል ስፍራ በደረሰ ጊዜ ፀሐይ ጠልቃ ስለነበር በዚያ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፡፡ ሕልምም አለመ፤ እነሆም የወርቅ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ፣ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ፣ የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር፡፡ እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት የአብርሃምን ተስፋ ሰጠው፡፡ ያዕቆብም ማልዶ ተነሣ፤ ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፤ በላዩም ላይ ዘይትን አፈሰሰ፡፡ ያንንም ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው፡፡ ዘፍ 28÷10-22፡፡ በዚህ ታሪክ መሰላሉ የእመቤታችን ወርቁ የንጽሕናዋ የድንግልናዋ፣ ቀይ ጎልማሳ የተቀመጠበት ዙፋን የማህጸኗ፣ ቀይ ጎልማሳ የጌታ፣ የተንተራሰው ድንጋይ የትንቢተ ነብያት ምሳሌ ነው፡፡ መላእክት በመሰላሉ

መውጣት መውረዳቸው ጌታችንን በፀነሰች ጊዜ ማሕፀኗን ዓለም አድርገው መላዕክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው ሲያመሰግኑ የመስሚቷ። ከላይ ወደታች መውረዳቸው በትህትና ራሱን ዝቅ አድርጎ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው የመሆኑ ሚስጢር ሲሆን ከታች ወደ ላይ መውጣታቸው በተዋሕዶ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ነው። አንድም መላእክት ወደ ላይ ወደታች መወጣት መውረዳቸው የሰዎችን ልመና ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሕረት ከሰማይ ለሰው ወደ ምድር የማምጣታቸው (አማላጅነታቸው) ምሳሌ ነው። በአጠቃላይ እመቤታችን ነብያት በተናገሩት ትንቢት ፀንታ በንፅህና በድንግልና የመውለዷና ዛሬም በእርሷ አማላጅነት /መሰላልነት/ የሰው ሁሉ ልመና ወደ እግዚአብሔር የመድረሱ ምሳሌ ነው።

ያዕቆብ ተነሥቶ ወደ ምስራቅ ሰዎች ሀገር ሄደ። በዚያም በጎች ውኃ ወደሚጠጡበት ጉድጓድ ደረሰ። በጉድጓዱም አፍ ትልቅ ድንጋይ ነበር። ያዕቆብ ራሔል የአባቷን በጎች ይዛ ስትመጣ ተመለከተ። ብዙ እረኞች ተሰባስበው በጎቧን የሚያነሡትን ድንጋይ ያዕቆብ ብቻውን አነሣ። ራሔል ይዛቸው የመጣችውን የላባን በጎች አጠጣ። ይህ ጉድጓድ የያዕቆብ ጉድጓድ ተብሎ ይጠራል። ዘፍ 29÷1፤ ኩፋሌ 20÷12፤ ዮሐ 4÷6።

ያዕቆብም በአጎቱ ላባ ቤት መኖር ጀመረ። ላባ ሁለት ሴት ልጆች ነበሩት። ታላቂቱ ልያ ታናሺቱ ደግሞ ራሔል ይባላሉ። ያዕቆብም ራሔል መልከ መልካም ስለነበረች ይወዳት ነበር። ያዕቆብ ለሃያ አንድ ዓመታት አገልግሎ ልያንና ራሔልን ከአገልጋዮቻቸው ጋር የራሱ አደረገ። ያዕቆብ ከልያ ስድስት፣ ከራሔል ሁለት፣ ከልያ አገልጋይ ዘለፋ ሁለት፣ ከራሔል አገልጋይ ባላ ሁለት በአጠቃላይ አስራሁለት የእስራኤል ነገድ አለቆችን ሲወልድ ዲና የምትባል ሴት ልጅንም ከልያ አግኝቷል።

አስራ ሁለቱ የነገደ እስራኤል አለቆች

ከልያ የተወለዱ	ከራሔል የተወለዱ
1. ሮቤል	1.ብንያም
2. ስምዖን	ከዘለፋ የተወለዱ
3. ሌዊ	1.ጋድ
4. ይሁዳ	2.አሴር
5. ይሳኮር	ከባላ የተወለዱ
6. ዛብሎን	1.ዳን 2.ንፍታሌም

እግዚአብሔር ያዕቆብን ወደ አባትህ ምድር ወደ ዘመዶችህም ተመለስ፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ አለው። ያዕቆብም ሚስቱንና ልጆቹን እንዲሁም በላባ ዘንድ ያፈራቸውን ከብቶች ይዞ በስውር ወደ አባቱ ምድር ከነዓን ኮበለለ። ላባም የያዕቆብን መኮብለል በሰማ ጊዜ የሰባት ቀን መንገድ ተከተለው፤ በገለዓድ ተራራም ደረሰበት። እግዚአብሔርም ለላባ በሕልም ተገልጾለት በያዕቆብ ላይ ምንም ክፉ እንዳያደርግበት አስጠነቀቀው። ያዕቆብ እና ላባ በክፉ እንዳይፈላለጉ ተማምለው በሰላም ተለያዩ። ያዕቆብም ለመታሰቢያ እንዲሆን ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመ። ዘፍ 31።

ያዕቆብም የተወሰነ መንገድ ከሔደ በኃላ ዔሳው ካለበት ስፍራ ደረሰ። የወንድሙን የዔሳውን ልብ ለማራራት እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ በርካታ ከብቶችን በአገልጋዮቹ እጅ ላከ። ያዕቆብ ያለውን ሁሉ የያቦቅን ወንዝ አሻግሮ ካሳለፈ በኃላ እርሱ ግን ከወንዙ መልስ ብቻውን አደረ። በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ሲታገለው አደረ። ያዕቆብም ካልባረከኝ አለቅም በማለት አሸነፈ። ስለዚህም እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም እስራኤል ብሎ ሰየመው። ያዕቆብም የዚያን ስፍራ ስም ጵንኤል ብሎ ሰየመው። ዘፍ 32÷22-32። ከያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች የተገኙት 'ሕዝብ እስራኤል' ተብለው ይጠራሉ። ዔሳው ለዘመናት የተለየውን ወንድሙን በፍቅር ተቀበለው። ያዕቆብም አባቶቹ አብርሃምና ይስሐቅ በኖሩበት ምድር ተቀመጠ። ዘፍ 49÷28። ያዕቆብ በ147 ዓመቱ አረፈ። በአብርሃም መቃብር በኬብሮን ተቀበረ። ዘፍ 50÷13፤ ኩፋሌ 32÷6።

- ይሁዳ

ይሁዳ ማለት ማመስገን ማለት ነው። ልያ ለያዕቆብ የወለደችው አራተኛ ልጅ ነው። ዘፍ 29÷35። ይሁዳ ካደገ በኃላ የከነዓዊውን ሰው ሴት ልጅ ሴዎን አገባ። ከእርሷም ኤር፣ አውናን፣ እና ሴሎም የሚባሉ ልጆችን ወለደ።

ኤር የሚባለው የበኩር ልጁ ለአቅመ አዳም በደረሰ ጊዜ ከአሕዛብ ወገን የሆነችውን ትዕማር የምትባል ሴት አጋባው። ኤር ግን ትዕማር አሕዛብ ስለሆነች በንቀት የማይደርስባት ሆነ። እግዚአብሔርም በዚህ ትዕቢቱ ምክንያት ቀሰፈው። ይሁዳም ዘር እንዲቆም (እንዲተካ) ይፈልግ ስለነበር ትዕማርን ለሁለተኛ ልጁ አውናን አጋባት። አውናን ልጅ ብወልድ የሚጠሩት በወንድሜ ስም ነው ብሎ ዘሩን በአፍአ ያፈካ (በምድር ያፈስ) ነበር። በዚህም እግዚአብሔር ቀሰፈው። ይሁዳም ትዕማርን 'ታናሹ ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ በአባትሽ ቤት መበለት ሆነሽ ተቀመጪ' ብሎ አሰናበታት። ትዕማርም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እመቤታችን ከቤተ ይሁዳ እንደሚወለዱ የተነገረውን ተስፋ ትሰማ ስለነበር ከባለተስፋ ቤት ወጣሁ በማለት አዘነች። ዘፍ 38÷1-11። ከዚህ በኃላ የይሁዳ ሚስት ሞተች። አንድ ቀን ይሁዳ የበጎቹን ፀጉር ወደሚሸልቱት ሰዎች ወደ ተምና ሄደ። ትዕማርም የይሁዳን ወደ ተምና መምጣት በሰማች ጊዜ ልብሰ ዘማ ለብሳ ጠበቀችው። ይሁዳም ምራቱ ትዕማር መሆኗን ባለማወቁ ፈቃዱን እንድትፈፅምለት ጠየቃት። ትዕማርም ከይሁዳ የፍየል ጠቦት ለመቀበል ተስማምታ እስከዚያው ድረስ ግን ኮፍያውን በትሩን እና ቀለበቱን ለምልክት ተቀብላ ፈቃዱን ፈጸመችለት።

ከሶስት ወራት በኃላ ይሁዳ ምራቱ ከእርሱ መፀነሷን አወቀ። ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስ እና ዛራ የተባሉ መንታ ልጆችን ወለደ። ፋሬስ በጌታችን መድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ ተቆጥሯል። ዘፍ 38÷27-30፣ ማቴ 1÷3። አባቱ ያዕቆብ 'በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም' ብሎ የተናገረው ትንቢት ፍፃሜ አገኘ። ዘፍ 49÷1።

- ዮሴፍ

ዮሴፍ ማለት ይጨምር ማለት ሲሆን ያዕቆብ ከራሔል ከወለዳቸው ሁለት ልጆች የበኩር ልጅ ነው። ዮሴፍ የያዕቆብ አስራ አንደኛ ልጅ ነው።

ዮሴፍ ከህፃንነቱ ጀምሮ ህልም አላሚና ፈቺም ነበር። በአባቱ ዘንድ እጅግ ተወዳጅና ሥነምግባሩም ያማረ ነበር። አንድ ቀን የሴፍ ህልምን አለመ፤ ለወንድሞቹም 'እነሆ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ነበር፤ የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች፤ የእናንተ ነዶች በዙሪያ ከብበው ለእኔ ነዶ ሰገዱ።' ብሎ ሕልሙን ነገራቸው። ዘፍ 37÷5-7። እነርሱም በእኛ ላይ ሊነግሥ ነው ብለው በቅናት በመነሣሣት ስንቅ ይዞላቸው በሄደበት በአንዱ ቀን በዱላ መቱት፤ወደ ስምአን ቢጠጋ በጥፊ መታው፤ ሮቤል ተዉ ለምን ትመቱታላችሁ አለ፤ ሊያድነው ፈልጎ ጉድጓድ እንጣለው አለ። ሮቤል ይህን ያደረገው የአባቱን ዕቁባት ባላንን ደፍሮ ከአባቱ ተቀያይሞ ስለነበር ከሱ ለመታረቅ ፈልጎ ነው። ይሁዳ ግን አውጥተን እንሸጠው በማለት ወደ ግብፅ ለሚሄዱ እስማኤላውያን ነጋዴዎች በ20 ዲናር ሸጡት። ይህ ታሪክ ምሳሌነት ያለው ሲሆን ዮሴፍ በጌታ፣ ሮቤል በፀሐፍት ፈሪሳውያን ሲመሰሉ ስምዖን ዮሴፍን በጥፊ እንደመታ ፀሐፍት ፈሪሳውያን ማነው የመታህ እያሉ ጌታን በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው። አንድም የሴፍ የጌታ፣ ሮቤል የጴላጦስ ምሳሌ ነው። ሮቤል ዮሴፍን እንዳይገድል ግን ጉድጓድ ጣሉት እንዳለ ጴላጦስ ጌታን መረመርኩት ኃጢአት አላገኘውበትም ግን ቀጥቼ እተወዋለሁ የማለቱ ምሳሌ ነው። ሉቃ 23÷14። የዮሴፍን ልብስ ደም ቀብተው ለያዕቆብ አሳዩት። ያዕቆብም አለቀሰ። ዮሴፍ የመለኮቱ፣ ልብሱ የትስብእት /የሥጋ/ ምሳሌ ነው። ደሙ ከልብሱ እንጂ ከዮሴፍ እንዳልተገኘ ሁሉ ሕማም ሞቱ የተገኘው በትስብእት /በሥጋው/ እንጂ በመለኮት ያለመገኘቱ ምሳሌ ነው። አንድም ዮሴፍ ከልብሱ ተለይቶአል፤ ልብሱ የዮሴፍ ልብስ እንደተባለ እንዲሁ በሥጋው ሞተ የመባሉ ምሳሌ ነው። ወንድሞቹ በክነዓን ዮሴፍ ሞተ ብለው በግብፅ ግን ሕያው እንደሆነ ጌታም በሥጋው ሞቶ በመለኮት ሕያው የመሆኑ ምሳሌ ነው። ይሁዳ የአዲስ ኪዳኑ የአስቆሮቱ ይሁዳ ምሳሌ ነው። ዮሴፍን በ20 ዲናር ሸጠ። የክነዓን 20 ዲናር በግብፅ 30 ብር ነው። ይህም ጌታን በ30 ብር የመሸጡ ምሳሌ ነው።

ዮሴፍ በግብፅ ባሪያ ሆኖ ሳለ በጴጢፋራ ቤት ለአስተዳዳሪነት ተሾመ። የጴጢፋራ ሚስት በሃሰት ስለከሰሰችው በግዞት ታሰረ። እዚያም እግዚአብሔር ሞገስን ሰጥቶት ከግዞቱ ቤት አለቃ በታች ኃላፊ ሆነ። ዘፍ 41÷40። የግብፅ ፈርኦንን ህልም የሚፈታለት በታጣ ጊዜ በግዞት ከዮሴፍ ጋር በነበረ ሰው አስታዋሽነት ዮሴፍ ነፃ ወጥቶ የግብፅ ንጉሥ ፊት ቀረበ። የፈርኦንንም ህልም በሰባት ዓመት የጥጋብ ዘመንና በተከታዩ ሰባት ዓመት አስከፊ የረሐብ ዘመን በመግለጥ አሳወቀ። በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት እህልን በመሰብሰብ የረሃቡን ዘመን ለማለፍ እንዲረዳ ዮሴፍ በግብፅ ከፈርዖን በታች ሆኖ ተሾመ። በዚህም ዮሴፍ በርካታ ሰዎችንና ቤተሰቡን ከሞት አዳነ። ዘፍ 47÷13-26። ዮሴፍ ግብፃዊቷ አስናትን አግብቶ

ምናሴን እና ኤፍሬምን ወለደ። ዘፍ 41÷50-52 አባቱን እና ወንድሞቹን ወደ ግብፅ አስመጥቶ መገባቸው። ዘፍ 46÷1-6። አባቱን በከነዓን እንዲቀብሩት የእስራኤልን ልጆች በማማሉ እምነቱን ገለጠ። ዘፍ 50÷25 ከእስራኤል ነገዶች የሁለቱ አባት ሆነ። ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ምናሴን እና ኤፍሬም ባረካቸው። ዮሴፍ በ110 ዓመቱ ዓረፈ። ዘፍ 50÷26።

◈ 2.2.2. ዘመነ መሳፍንት

መስፍን ማለት ፈራጅ፣ አስተዳዳሪ፣ ገዥ ማለት ነው። መንግሥተ እግዚአብሔር ወይም ዘመነ መሳፍንት እየተባለ የሚጠራው ነገሥታት በእስራኤል ማስተዳደር ከመጀመራቸው በፊት ከመካከላቸው መስፍን ያስነሳላቸው የነበረበት ዘመን ነው። መሳፍንት እንደ ነገሥታት ሀገረ መስፍን አልነበራቸውም። ከማንኛውም ነገደ እስራኤል መስፍን ሊነሣ ይችል ነበር። በተለይም ኢያሱ ካረፈ በኃላ እግዚአብሔር ንጉሣቸው ሆኖ እንዲገዛቸው ፈቃዱ ስለነበር የኢያሱ ተከታይ የሆነ አንድ ጠቅላይ መሪ አልተሾመባቸውም። ለሰልፍ ሲወጡ ይሁዳ የተሰፋው ቃል ጨራሽ ስለሆነ እርሱ መሪ ሆኖ ከሌሎች በፊት እንዲሄድ እግዚአብሔር ይገልጥላቸው ነበር።

በመጀመሪያ የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን ሕግ እያሰቡ ለእርሱ ብቻ ይታዘዙ ነበር። በኃላ ግን በሀገሩ የቀሩ ከነዓናውያን እንቅፋት ሆኑባቸውና ወደ ጣኦት ማምለክ እንዲያዘነብሉ አደረጓቸው። አምላካቸውንም ትተው ለሌሎች አማልክት ሲገዙ እግዚአብሔርም ተዋቸው። በጠላቶቻቸውም እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። መሳ 1÷1-2። በጠላቶቻቸው ተቸግረውና በኃጢአታቸው ተፀፅተው ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ እርሱም በምህረት ኅብኝቷቸው መሳፍንትን በማስነሳት ከጠላቶቻቸው እጅ ያድናቸው ነበር። ዘመነ መሳፍንት 450 ዓመታት ያህል የቆየ ሲሆን በዚህ ወቅት ሙሴ በተቀበለው ታቦት አማካኝነት በመገናኛው ድንኳን እግዚአብሔር ይገለጥላቸው ነበር። በእስራኤል በአጠቃላይ 17 መሳፍንት በየተራ ህዝበ እስራኤልን መርተዋል። እነዚህም በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው።

1. ሙሴ	5. ሰሜጋር	9. ቶላ	13. ዓብዶን
2. ኢያሱ	6. ዲቦራና ባርቅ	10. ዮፍታሔ	14. ሶምሶን
3. ኀቶኒያል	7. ጌዲዎን	11. ኢብጻን	15. ዔሊ
4. ናያድ	8. አቤሜሌክ	12. ኤሎም	16. ሳሙኤል

- ከነዚህ መሳፍንት ዋነኞች የሆኑት የጥቂቱን ታሪክ በሚከተለው መልኩ በአጭሩ እናቀርባለን።

◈ ሙሴ

ሙሴ ማለት የስሙ ትርጓሜ ከውሃ የተገኘ ሲሆን አባቱ እንበረም እናቱ ደግሞ ዮካብድ ይባላሉ። ሙሴ የተወለደው የጨካኙ ፈርዖን ሕግ ወንዶች ልጆች እንዳይወልዱ በከለከለ ጊዜ ነው። ዘጸ 2÷2። ይሁን እንጂ እናቱ ከወለደችው በኃላ ሦስት ወር ደበቀችው። ከዚያ በላይ ስላልተቻላት በደንገል አድርጋ ከወንዝ ዳር ባለ ቁጤማ ውስጥ አስቀመጠችው። እግዚአብሔርም ይህን የሚያምር ህፃን ለትልቅ ስራ ስለመረጠው አዳነው። የፈርዖን ልጅ ልትታጠብ ከደንገጡሮችዋ ጋር ወደ ወንዝ በወረደች ወቅት ከቁጤማ ውስጥ ያለውን ሙሴን አገኘችው። በህፃኑ ላይ ያለውን ልዩ ፀጋ በተመለከተች ጊዜ ወሰደችውና ልጇ አድርጋ ተቀበለችው። ጡት የሚያጠባው በተፈለገ ጊዜም እናቱ ስለተገኘች ሙሴ የእናቱን ጡት እየጠባ ነገር ግን የፈርዖን የልጅ ልጅ እየተባለ አደገ።

ሙሴ በፈርዖን ቤት በነበረበት ወቅት የእስራኤል ልጆች በከባድ ስራ ይጨነቁ ነበር። እንደ ንጉሥ ስለአደገ የግብፅ ጥበብን ሁሉ ተምሮ በአሕዛብ ትምህርት ቢታነፅም በእነርሱ ዘንድ ክብር የተባሉት ነገሮችን አልወደደም፤ ይልቁንም ወደ ወንድሞቹ አዘነበለ። ሙሴ በአንድ ወቅት በግብፃዊና በእስራኤላዊ መካከል ፀብ በሆነ ጊዜ ለእስራኤላዊው አድልቶ ግብፃዊውን ገደለው። ዘፀ 2÷11-14። በነጋታውም ወደዚያ ስፍራ በመጣ ጊዜ ሁለት ዕብራውያን ሲጣሉ ተመለከተ፤ ሊያስታርቃቸውና ሊመክራቸው ፈለገ። እነርሱ ግን ገላጋያቸው ሙሴን ሊቀበሉት አልወደዱም። ይልቁንም አንደኛው ዕብራዊ ትላንት እንደገደልከው ግብፃዊ ልትገድለኝ ትፈልጋለህ ያለውን በሰማ ጊዜ ሙሴ የሰራው ስራ ይፋ መሆኑን አወቀ። በዚህም

ፈርዖን ሊገድለው እንደሚችል ሰለተገነዘበ መኮብለል የግድ ሆነበት፡፡ ከፈርዖን ቤትና ከግብፅ ሀገር ጠፍቶ 40 ዓመት የሚያህል ጊዜ ከምድያማውያን ዘንድ በአንድ ካህን ቤት ተቀመጠ፡፡ ምድያማዊው ካህን ዮቶርም የሙሴን መልካምነት ተመልክቶ ሴት ልጁ ሲፓራን ለሚስትነት ሰጠው፤ ባለሙሉ መብት አድርጎም እንደፈቃዱ ይኖር ዘንደ አሰለጠነው፡፡ ሙሴም ከሚስቱ ከሲፓራ ልጆችን ወለደ፡፡ አንዱን በሌላ ምድር መጻተኛ ነኝ ሲል ጌርሳም አለው፡፡ ሌላኛውን የአባቴ ፈጣሪ እረዳቴ ነው ሲል አልዓዛር ብሎ ጠራው፡፡ ዘጸ 2÷15-22፡፡

ሙሴ በአንድ ወቅት ወደ እግዚአብሔር ተራራ ኮሬብ ሲመጣ በእኩለ ቀን ከፀሐይ ይልቅ ደማቅ የሆነ ብርሃን ዓይኑን ሳበው፡፡ እንግዳ በሆነው ነገር ተደንቆ ወደ ተራራው ሲመለከት የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ነበልባል በቁጥቋጦው መካከል ታየው፤ እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ቢነድም ሳይቃጠል አየው፡፡ ሙሴም ልሂድና ቁጥቋጦው ስለምን እንዳልተቃጠለ የሚታየውን ታላቅ ራዕይ ልይ አለ፡፡ ሙሴ ይመለከት ዘንድ በመጣ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ሕይወት አልባ ጫማዎችን አድርጎ እንዳይቀርብ ከለከለው፤ ጫማውንም ከእግሩ አወለቀ፡፡ አምላካዊ ብርሃን በሚበራበት መሬት ላይ በባዶ እግሩ ቆመ፡፡

እግዚብሔርም በሙሴ ውስጥ ያስቀመጠውን ልዩ ፀጋ በሚገባ ይረዳ ዘንድ በእጁ በያዘው በትር ምልክትን አሳየው፡፡ ዘጸ 3÷1፤ ዘጸ 4÷1፡፡ እስራኤልን ነፃ እንዲያወጣ ሙሴ በእግዚአብሔር ታዞ ወደ ፈርዖን ተላከ፡፡ወንድሙም አሮን እንዲናገርለት ተፈቀደ፡፡ ፈርዖንም ህዝቡን አለቅም ባለ ጊዜ እግዚአብሔር በሙሴ እጅ አሥር መቅሰፍት በግብፅ ላይ አወረደ፡፡ ዘጸ 5÷11፡፡

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን ህዝቡ ሁሉ በየቤታቸው አንዳንድ ጠቦት ከበጎች ወይም ከፍየሎች ወስደው አርደውም የእግዚአብሔርን በዓል ፋሲካ እንዲያደርጉ አዘዘ፡፡ ዘጸ 12÷3-13፡፡ በበጉ ደምም እንደሚድኑ ተስፋ ተሰጣቸው፡፡ የእስራኤልም ልጆች ሁሉ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዘ አደረጉ፡፡ በዚያም ቀን እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከሠራዊታቸው ጋር ከግብፅ ምድር አወጣቸው፡፡ እግዚአብሔርም የግብፅን ንጉሥ ልብ አፀና፤ እርሱም እስራኤልን አሳደደ፡፡ እግዚአብሔርም የሙሴን ድምፅ ሰምቶ የኤርትራን ባሕር በመክፈል ሕዝቡን አዳነ፡፡ ዘፀ 14÷1-15፡፡

ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ከኤርትራ ባሕር አውጥቶ ወደ ሱር ምድር ወሰዳቸው፡፡ በማራና በኤሎምም ሰፈሩ፡፡ ከኤሎምም ተነስተው ወደ ሲና ምድረ በዳ ደረሱ፡፡ በዚያ ሳሉ ረሐብ መጣባቸው፡፡ እግዚአብሔር ችግራቸውን አይቶ ሥጋንና እንጀራን ሰጣቸው፡፡ ዘፀ 16÷12፡፡ በራፊዲም በሰፈሩ ጊዜ ውሃ ተጠመ፤ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጮኸና ከኮሬብ ድንጋይ ውኃ ሰጣቸው፡፡ ዘፀ 17÷1፡፡ አማሌቃውያንም መጥተው ከእስራኤላውያን ጋር በራፊዲም ተዋጉ፡፡ ሙሴ በተራራ ላይ ቆሞ ስለጸለየላቸው እስራኤላውያን ድል ነሱ፡፡ ዘፀ 17÷8፡፡ ከራፊዲም ተነስተው ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ፤ ከዚያም እስራኤላውያን በተራራው ፊት ለፊት ሰፈሩ፡፡ አንደ ዓመትም በሲና ሰፍረው ሳሉ በሙሴ አማካኝነት ህግን ተቀበሉ፡፡ እግዚአብሔርም እንዳዘዘው ሙሴ መሠዊያን አዘጋጀ፡፡ መሥዋዕትንም አቅርቦ የመሥዋዕቱን ደም በመሠዊያውና በሕዝቡ ላይ ረጭቶ ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑለት ከእግዚአብሔር ጋር ቃልኪዳን ገቡ፡፡ ዘፀ 24÷1-12፡፡

ሙሴም 40 ቀን በሲና ተራራ ላይ በመቆየቱ ሕዝቡ ሁሉ በአሮን ላይ አምፀው ለወርቅ ጥጃ ሰገዱ፡፡ ዘፀ 32÷6፡፡ ሙሴም ከተራራ በወረደ ጊዜ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ሲበድሉ አገኛቸው፡፡ የሙሴም ቁጣ ተቃጠለ፡፡ እነዚያንም ሁለቱን ጽላት ከእጁ ጥሎ ከተራራው በታች ሰበራቸው፡፡ የሰሩትንም ጥጃ ወስዶ እንዲሁ አደረገው፤ ለሕዝቡም ጸለየ፡፡ ዘፀ 32÷7-35፡፡ ሙሴም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የፊተኛውን አስመስሎ ጽላት ቀረፀ፡፡ ዘፀ 34÷1፤ ዘዳ 10÷1-5፡፡ በሲና ተራራ ላይ እንደገና 40 ቀን ቆየ፡፡ እግዚአብሔርም ይቅር ብሎ እንደገና ቃልኪዳኑን በድጋሚ አጸና፤ በጽላቱም ላይ በሥሩ የቃልኪዳን ቃሎች ጻፈባቸው፡፡ ዘፀ 10÷4፡፡ ሙሴም የመገናኛውን ድንኳን አሰርቶ ተከለ፡፡ ዘፀ 35÷40፡፡ ስለ መሥዋዕት፣ ስለ ክህነት፣ እንዲሁም ስለሚያደርጉት ጉባዔ ሁሉ ትዕዛዞችን ተቀበለ፡፡ ህዝቡን ቆጠረ፤ በየነገዳቸውም በመቅደስ ዙሪያ አደረጋቸው፤ ለጉዞም አዘጋጃቸው፡፡ ዘኁ 1÷2፡፡ ወደ ከንዓን ዳርቻ በደረሱ ጊዜ 12 ከነገዱ የሚሆኑ ሰዎችን እንዲሰልሉ ላከ፡፡ ሰልለውም በመጡ ጊዜ አስሩ ሰዎች በሕዝቡ ላይ ጥርጥርን ፈጠሩ፡፡ ባለማመንም የተነሳ አንወጣም ባሉ ጊዜ አርባ ዓመት በምድረ በዳ እንዲመላለሱ ተፈረደባቸው፡፡ ዘኁ 13÷1፡፡ ዘዳ 1÷14፡፡ ዘኁ 14÷20፡፡ ዘዳ 1÷34፡፡ የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ 40 ዓመት በተመላለሱበትም ወቅት ቢሆን እግዚአብሔር አልተለያቸውም፡፡ በተቸገሩ ሁሉ ጊዜ ረዳቸው፡፡ ዘኁ 20÷2-12፡፡ መናንም በየጊዜው ከመስጠት አልተቆጠበም፡፡

ሙሴ የኤዶምያስን ንጉሥ እስራኤላውያን በሃገሩ እንዲያልፉ መልዕክት ላከ። የኤዶምያስ ንጉሥ ግን በሃገሩ እንዲያልፉ አልፈቀደም። ዘኁ 20÷19። እስራኤላውያንም እግዚአብሔርንና ሙሴን አሙ፤ በዚህም እግዚአብሔር የሚገድሉ እባቦች ሰደደባቸው፤ ሕዝቡንም ነደፉ። በሙሴ ምልጃም ከቁጣው መቅሰፍት ዳኑ። ዘኁ 27፤4-9። የአሞራውያን ነገሥታትን በማሸነፍ በዮርዳኖስ በስተምስራቅ ወዳለው ሰፊ ምድር አገባቸው። የሞአብ ንጉሥ ባላቅም እስራኤልን እንዲረግም በለዓምን ግድ አለው። ነገር ግን በለዓም እግዚአብሔር ከልቡ ያነቃውን ነገር በምሳሌ ተናገረ። ዘኁ 21÷32። በመጨረሻ ሙሴ አዲሱን ትውልድ ለማሳወቅ፣ ለማስተማርና ለማጠንከር ሕዝቡን ሰብስቦ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ እና የሰጣቸውን ሕግ አጥብቆ አሳሰባቸው። በረከት እንዲሆንላቸው ለእግዚአብሔር ብቻ መታዘዝና በእርሱ ብቻ ማመን አስፈላጊ መሆኑን ገለጠላቸው። ሙሴም በራሱ ምትክ ኢያሱን በሕዝቡ ላይ መሪ እንዲሆን ሹሞ የእስራኤል ነገዶችን ባረከ።

ሙሴ እጅግ ትሁት ነበር፤ ግብፃዊውን በንዴት የገደለው ሙሴ የእስራኤልን መቃወምና ማጉረምረም ታገሰ። እራሱንም ለእነርሱ አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን በጸሎቱ በመግለፅ እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው ለመነ። እስራኤላውያን በምድረ በዳ በሚንከራተቱባቸው ዓመታት አንድ ጊዜ ሙሴ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ስም አላከበረምና ምድረ ከነዓንን አሻግሮ እንደሚያያት እንጂ እንደማይገባባት አግዚአብሔር ተናገረው። ዘፀ 17÷1-7። ዘኁ 20÷1-12። በዚህም ምክንያት ሙሴ ከሞአብ ሜዳ በኢያሪኮ ፊት ለፊት ወዳለው ወደ ናባው ተራራ ራስ ወጣ፤ በዚያም ከነዓን ካየ በኃላ በመቶ ሃያ ዓመቱ ዐረፈ። ዘዳ 34÷1። መላዕክትም እስራኤላውያን ለሙሴ ሥጋ ሰግደው እንዳይሳሳቱ በማሰብ ደብቀው ቀብሩት።

- ኢያሱ

ኢያሱ ማለት አዳኝ መድኃኒት ማለት ነው። ኢያሱ ከመባሉ አስቀድሞ አውሴን ተብሎ ተጠርቷል። ኢያሱ ሙሴ ከሞተ በኃላ እስራኤላውያንን እየመራ ከነዓን ያስገባ ነው። ኢያሱ ምድሪቱን ይሰልሉ ዘንድ ሰሎሞንን እና ካሌብን ለከ። እነርሱም ሊይዟቸው ከሚፈልጉ ሰዎች ያመልጡ ዘንድ ስለረዳቻቸው ዘማዊቷን ራኬብን /ርዓብ/ አዳኗት። ባሕረ ዮርዳኖስም በፊታቸው በሆነ ጊዜ ኢያሱ ታቦት የሚይዙትን ካህናት በመጥራት ታቦቱን እንደተሸከሙ እግራቸውን ውኃ ውስጥ እንዲያቆሙ አደረገ። በዚህም ባህሩ ደርቆ እስራኤል በደረቅ ተሻገሩ። ከዮርዳኖስ ባሻገር የምትገኘው የኢያሪኮ ከተማ ታላቅና ብርቱ ነበረች። እግዚአብሔር ግን ከተማይቱን ከነገስታቱ ጋር አሳልፎ እንደሚሰጠው ለኢያሱ ተናገረው። በአምላክም ትዕዛዝ ካሕናቱ ታቦቱን ይዘው ከተማይቱን ሰባቱ ዙሩና ከህዝቡ ጋር በመሆን ከፍተኛ ድምፅ ያለው ጩኸት አወጡ። በዚህ ጊዜ የኢያሪኮ ቅፅር ፈረሰ። በዚያም ሠላሳ አንድ ነገሥታትን እስኪያሸንፉ ድረስ እግዚኢአብሔር ኢያሱን ረዳው። በአይሎን ሜዳ (ገባኦን) እስራኤል ከአሞራውያን ጋር በተዋጉ ጊዜ ኢያሱ በቃሉ ፀሐይንና ጨረቃን አቆመ። እግዚአብሔርም አሞራውያንን በመብረቅና በበረዶ አጠፋቸው። ኢያሱም ከሌዊ ነገድ በስተቀር ለሌሎቹ ነገዶች ርስትን አከፋፈለ። የታቦቱንም ድንኳን በሴሎን ተከለ። ኢያሱ 110 ዓመት ሲሆነው አረፈ። በተራራማው በኤፍሬም አገር ተቀበረ።

- ጌዲዎን

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፋትን ሰሩ፤ እግዚአብሔርም በምድያም እጅ ሰባት ዓመት አሳልፎ ሰጣቸው። ምድያማውያን በየጊዜው ወደ እስራኤል እየዘመቱ የእርሻቸውን ፍሬ ያጠፉ ነበር። በዚህም ምክንያት እስራኤላውያን ምድያምን በመፍራት በተራራዎች ላይ ምሽግና ዋሻ አበጁ። በንስሐ ተመልሰው እግዚአብሔርን ያድናቸው ዘንድ ለመኑት። መሳ 6÷1-6።

የእግዚአብሔር መልአክ በዚያን ወቅት ለምናሴ ነገድ ለሆነ ለኢዮአስ በሆነችው ዛፍ ስር ተቀመጠ፤ የኢዮአስም ልጅ ጌዲዎን ከምድያማውያን በመሸሽ በወይን መጥመቂያ ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር። እግዚአብሔርም በመልአኩ አድሮ ጌዲዎንን የእስራኤል ጠላቶች የሆኑትን ምድያማውያንን እንደሚያጠፋ ነገረው። ጌዲዎን ግን # ጌታ ሆይ እስራኤልን በምን አድናለሁ? ወገኔ ከምናሴ ነገድ ይልቅ የተጠቃ ነው፤ እኔም በአባቴ ቤት የሁሉ ታናሽ ነኝ አለው። እግዚአብሔርም #በእርግጥ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ምድያምንም እንደ አንድ ሰው ትመታለህ; አለው። ጌዲዎንም ሄዶ ለእግዚአብሔር መልአክ ቁርባንን አመጣ፤ የእግዚአብሔር መልአክ #በዚህ ድንጋይ ላይ አኑር; አለና እጁን ዘርግቶ በያዘው በትር ጫፍ ቁርባኑን አስነካ፣ እሳትም ከድንጋይ ውስጥ ወጥቶ ቁርባኑን በላ። የእግዚአብሔር መልአክ ተሰወረ።

በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ጌዲዎንን #የአባትህ የሆነውን የበዓልን መሰዊያ አፍርስ፤ በዚያም ኮረብታ ላይ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር መሠዊያን አሳምረህ ሥራ፤ የአባትህ የሆነውን ሁለኛውን የሰባት ዓመት በሬ ውሰድና የሚቃጠል መስዋዕት አድርገህ ሰዋ; አለው። ጌዲዎንም የአባቱን ቤተሰቦችና የከተማውን ሰዎች ስለፈራ ይህን በቀን ማድረግ አልቻለም። ነገር ግን በሌሊት አደረገው። አባቱም የበዓልን መሰዊያ ስላፈረሰ ጌዲዎንን ይሩበዓል ብሎ ጠራው። መሳ 6÷25-32።

ምድያማውያን፣ አማሌቃውያን እና የምስራቅ ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው በኢይዝራኤል ሸለቆ ሰፈሩ። ጌዲዎንም እግዚአብሔር በዘረጋለት ፀምር (የተባዘተ የበግ ፀጉር) ላይ የድል ምልክት እንዲገልጥለት ጠየቀ። እግዚአብሔር ጌዲዎን በዘረጋው ፀምር ላይ ብቻ ጠል አወረደ፤ ከፀምሩ ውጭ ባለው ምድር ላይ ግን ጠል አልወረደም። ዳግመኛም ጌዲዎን እግዚአብሔርን ጠል በዙሪያው ባለው ምድር ላይ እንዲወርድ በፀምሩ ላይ ግን ፈፅሞ እንዳይወርድ ለመነ። እግዚአብሔርም የጌዲዎንን ልመና ፈጸመለት። የዚህ ምልክት ምሳሌነት ለጊዜው፡- ፀምሩ የእስራኤል፣ ጠል የረዲኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ጠል በፀምሩ ላይ መውረዱ በምድር ላይ ግን አለመውረዱ ረድኤተ እግዚአብሔር ለእስራኤል መገለጡን በዙሪያቸው ላሉ አሕዛብ ደግሞ አለመገለጡን የሚያሳይ ነው። ፍፃሜው ግን፡- ፀምሩ የእመቤታችን፣ ጠሉ የጌታችን ምሳሌ ነው። ጠል በፀምሩ ላይ መውረዱ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልደ ከሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በማኅፀኗ የማደሩ ምሳሌ ነው። ጠል በምድር ላይ አለመውረዱ ደግሞ ሌሎች ሴቶች ለዚህ ክብር አለመመረጣቸውን የሚያሳይ ነው። ደግሞም በሁለተኛው ምልክት ፀምር የእስራኤል፣ ጠል የመቅሰፍተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። የሁለተኛ ምልክት ምሳሌነት ለጊዜው ጠል በፀምሩ ላይ አለመውረዱ በምድር ላይ ግን መውረዱ እስራኤል ከመቅሰፍት የመዳናቸው አሕዛብ ግን በመቅሰፍት የመጥፋታቸው ምሳሌ ነው። ለፍፃሜው ግን ጠል የዘርዓ ብእሲ፣ ፀምር የእመቤታችን ምሳሌ ነው። በዚህ ግዜ በፀምሯ ላይ ሳይወርድ ከምድር ላይ መታየቱ እመቤታችን ያለዘርዓ ብእሲ ለመውለዷ ሌሎች ሴቶች ግን በዘርዓ ብእሲ ለመውለዳቸው ምሳሌ ነው።

ጌዲዎን ሠላሳ ሁለት ሺህ ጦር አሰለፈ። እግዚአብሔር ግን #እስራኤል እጄ አዳነኝ ብሎ እንዳይታበይ ሠራዊትህን ቀንስ; አለው። ስለሆነም ጌዲዎን የፈራ የደነገጠ ተነስቶ ይመለስ በሎ በማወጁ ከሕዝቡ ሃያ ሁለት ሺህው ተመለሱ። እግዚአብሔር አስር ሺሁም ብዙ ነውና ወደ ውኃ አውርዳቸውና እፈትናቸዋለሁ ብሎ ጌዲዎንን አዘዘ። ጌዲዎንም ወደ ውኃ ወሰዳቸው። በዚያም ውሻ እንደሚጠጣ እየተንበረከኩ በምላሳቸው የጠጡት በርካቶች ሲሆኑ ሶስት መቶ የሚሆኑት ግን በእጃቸው እየጨለፉ ጠጡ። እግዚአብሔርም ጌዲዎንን ሦስት መቶዎቹን ብቻ እንዲያሰልፍ በነገረው መሰረት አሰለፈ። በጦርነቱም ወቅት እግዚአብሔር ምድያማውያንን በጌዲዎን እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። ጌዲዎንም ምድያምን አጠፋ። መሳ 8÷22።

እስራኤላውያን ጌዲዎንን #ከምድያም እጅ አድነኸናልና አንተ፣ ልጅህም የልጅ ልጅህም ግዙን; አሉት። ጌዲዎን #እኔ አልገዛችሁም፣ ልጄም አይገዛችሁም፤ እግዚአብሔር ይገዛችኋል እንጂ; አላቸው። ጌዲዎን በእስራኤል ላይ አርባ ዓመት ፈራጅ ሆነ። በጌዲዎን እድሜ ምድሪቱ አርባ ዓመት አረፈች። መሳ 8÷22-28። ጌዲዎን በመልካም ሽምግልና ዐረፈ። በአባቱም መቃብር ተቀበረ። መሳ 8÷32።

ዮፍታሔ

ከእስራኤል መሳፍንት አንዱ ነው። አባቱ ገልዓድ ሕጋዊ ካልሆነች ሴት የወለደው ልጅ ነው። የእንጀራ እናቱ ልጆች ባደጉ ጊዜ ወገናችን አይደለህምና በአባታችን ቤት አትወርስም ብለው አሳደዱት። ዮፍታሔም ሸሽቶ በጦብ ምድር ተቀመጠ፤ በዚያም ተከታዮችን ሰብስቦ መሪ ሆነ። መሳ 11÷1-3።

በዘያ ዘመን አሞናውያን ከእስራኤላውያን ጋር ይዋጉ ነበር። አሞናውያን ድንበር ተሻግረው ሊያጠቋቸው በተነሱ ጊዜ በፊታቸው የሚመራቸውን ያጡ እስራኤላውያን ዮፍታሔን በመለመን የጦር አለቃ አድርገው ሾሙት። ዮፍታሔ በቅድሚያ የሰላም ስምምነት ለማድረግ መልዕክተኞችን ወደ አሞናውያኑ ንጉሥ ላከ። የአሞናውያን ንጉሥ ግን በእርቁ ስምምነት ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆነም። መሳ 11÷12። የፍታሔም ለጦርነት ተሰለፈ። ለእግዚአብሔርም #ጠላቶቼን ድል ነስቼ በሰላም ከተመለስኩ በመጀመሪያ ከቤቴ ደጅ ወጥቶ የሚቀበለኝን ማንኛውንም አሰዋለሁ; በማለት ስዕለትን ተሳለ። እግዚአብሔርም አሞናውያንን በእጁ አሳልፎ ሰጠው። ዮፍታሔ በእግዚአብሔር መንፈስና ኃይል መትቶ አሸነፋቸው።

ከጦርነት መልስ ወደ ቤቱ ሲመለስ ሴት ልጁ ከበሮ ይዛ እየዘፈነች ልትቀበለው ወጣች። ለእርሱም ብቸኛ ልጁ ነበረች። ዮፍታሔም እርሷን ባየ ጊዜ ልብሱን ቀዶ #ለእግዚአብሔር ተስያለሁና ከዚያውም ልመለስ አልችልምና በጣም አስጨነቅሽኝ; አላት። እርሷም ለእግዚአብሔር የተናገርከውን ቃል ፈፅም፤ እኔም ስለድንግልናዬ ሁለት ወር እንዳለቅስ አሰናብተኝ አለችው። ሁለት ወር ከተፈፀመ በኃላ ወደ አባትዋ ተመለሰች። የፍታሔም የተሳለውን ስእለት ይፈፅም ዘንድ የሚወዳትን ሴት ልጁን መስዋእት አድርጎ አቀረበ። የኤፍሬምም ሰዎች በድልህ ጊዜ እኛን አልጠራሕንም በሚል ምክንያት ተነሱበት። ነገር ግን ዮፍታሔ ድል ነሳቸው። ዮፍታሔ በእስራኤል ላይ ስድስት ዓመት ፈረደ። ዮፍታሔ ሲያርፍ በሃገሩ በገልዓድ ተቀበረ። መሳ 12÷7።

- ሶምሶን

አባቱ የዳን ነገድ የሆነው ማኑሄ ሲሆን እናቱ መካን ነበረች። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስራ በመስራታቸው ለአርባ ዓመታት በፍልስጥኤማውያን እጅ አሳልፎ ሰጥቷቸው ነበር። በተለይም በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር መልአክ ለሴቲቱ ተገልጾ #ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ የወይን ጠጅን የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ፤ ርኩስም ነገር አትብይ። ልጁም ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናል። በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፤ እርሱም እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል; አላት። መሳ 13÷5-7። ወንድ ልጅም ወለደች፤ ስሙንም ሶምሶን ብላ ጠራችው። እርሱም አደገ፤ እግዚአብሔርም ባረከው፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በዳን ሰፍራ ያነቃቃው ጀመር። በዚያ ዘመን ፍልስጥኤማውያን አንዳንዶቹን የእስራኤል ከተሞች ወስደው ይገዙባቸው ነበር። እስራኤላውያን ግን ሊዋጓቸው አልደፈሩም። ሶምሶን ግን በአንዲት ፍልስጥኤማዊት ምክንያት ተጣልቶ 300 የሚሆኑ ቀበሮዎችን በመሰብሰብና ጭራቸውን አብሮ በማቆላለፍን በእሳት በመሰካት የፍልስጤማውያኑን ደርሶ የነበረ ሰብል ደመሰሰ። ይህን ካደረገ በኃላ ግን ፍልስጤማውያኑን ፈርቶ በዋሻ ውስጥ ተሸሸገ ተቀመጠ። መሳ 15÷7። የይሁዳ ሰዎች ፍልስጥኤማውያንን ፈርተው ሶምሶንን አሳልፈው ሰጡት። በዚያን ወቅትም ሶምሶን በአህያ መንጋጋ ብቻ አንድ ሺህ ፍልስጤማውያን ገደለ። መሳ 15÷9-19። ለሃያ ዓመታትም በእስራኤል ላይ ፈራጅ ሆነ።

ሶምሶን ኃይሉ የበረታ በመሆኑ ጠላቶቹ በጋዛ ከተማ ሊይዙት ሲጠባበቁ የከተማይቱን በር መዝጊያ ነቅሎ በመውሰድ ያመለጠ እስራኤላዊ መስፍን ነው። መሳ 16÷1-3። ከዚህ በኃላ ሶምሶን ደሊላ የምትባል ሴትን ወደደ። ከእርሷም ዘንድ መግባቱን የተመለከቱት ፍልስጤማውያን ደሊላን የሶምሶን የኃይል ሚስጢር ምን እንደሆነ በማጣራት እንድትነግራቸው አስገደዷት። ደሊላም ሶምሶንን ናዝራዊነቱን እስኪገልጥላት ድረስ ነዘነዘችው። ሶምሶንም #ለእግዚአብሔር የተለየሁ ነኝና በራሴ ላይ ምላጭ አልደረሰም; ብሎ የልቡን ገለፀላት። እርሷም የራሱን ፀጉር አስላጭታው ኃይሉ በደከመ ጊዜ ለፍልስጤማውያን መኪንንት አሳልፋ ሰጠችው። መሳ 16÷20። እነርሱም ዓይኑን አሳውረው በጋዛ አሰሩት። አምላካቸው ዳጎንን ሊያመሰግኑ በተሰበሰቡበት ወቅት ሶምሶንን አስመጥተው ተዘባበቱበት። የሶምሶን ፀጉር ማደግ ጀምሮ ነበር። እርሱም ወደ እግዚአብሔር ፀልዮ የቤቱን ምሶሶዎች ገፋ፤ ቤቱም ሲወድቅ በውስጥ የነበሩት መኪንንት እና ከፍልስጤማውያን በርካቶች አለቁ፤ ሶምሶንም አብሮአቸው አረፈ። ሶምሶን በሕይወት ዘመኑ ከገደላቸው ይልቅ በሞቱ የገደላቸው በዙ። መሳ 16÷23-31።

- ዔሊ

ከአሮን ቤተሰብ የሆነ በሊቀ ክህነትና በፈራጅነት በእስራኤል ያገለገለ ነው። በዘመኑ የእግዚአብሔር የመቅደስ ድንኳን በሴሎ ተተክሎ ነበር። ዔሊ አፍኒን እና ፊንሐስ የሚባሉ በክህነት የሚያገለግሉ ሁለት ልጆች ነበሩት። ልጆቹ ግን በእግዚአብሔር ፊት በቀና የማይጓዙ ምናምንቴዎች ነበሩ። እነዚህ ልጆች ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መስዋዕት ለራሳቸው ከመውሰድ ጀምሮ በመገናኛው ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር እስከማመንዘር የደረሱ ነበሩ። ዔሊም ካህንና ፈራጅ ሲሆን ልጆቹን በሚገባ አልገሰፀም ነበር። በዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ለብላቴናው ሳሙኤል ተገልጦለት በዔሊ ቤተሰብ ላይ የሚያደርሰውን ከባድ ቅጣት ነገረው።

ዔሊ በእስራኤል ላይ አርባ ዓመት ከፈረደ በኃላ እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሊዋጉ ወጡ። ነገር ግን በፍልስጤማውያን ተመቱ። ሁለቱ የዔሊ ልጆችም አፍኒንና ፊንሐስ በጦርነቱ ሞቱ።

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦትም ተማረከች። ዔሊም ስለልጆቹ እና ስለ እግዚአብሔር ታቦት በሰማ ጊዜ ከወንበር ወድቆ ሞተ። 1ኛ ሳሙ 4።

- ሳሙኤል

በኤፍሬም ሃገር የሚኖር ሕልቃና የተባለ ሌዋዊ ነበር። ሐና እና ፍናና የሚባሉ ሁለት ሚስቶች ነበሩት። ፍናና የተባለችው ሚስቱ የልጆች እናት ስትሆን ሐና ግና መካን ነበረች። ሐናም በእግዚአብሔር ፊት ልትፀልይ ወደ መቅደስ ሄደች። ልጅ እንዲሠጣትም ለእግዚአብሔር ስዕለት ተሳለች። እግዚአብሔርም ሐናን አሰባት፤ ወንድ ልጅም ወለደች። #ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ; ስትልም ሳሙኤል ብላ ጠራችው። 1ኛ ሳሙ 1÷27። ሳሙኤል ጡት በተወ ጊዜ ሐና ለመስዋዕት ወይፈንን ይዛ ወደ እግዚአብሔር ቤት አቀረበች። ሕልቃናና ሐናም ሕፃኑን ወደ ዔሊ አቀረቡት። ሳሙኤልም ገና ብላቴና ሳለ በእግዚአብሔር ፊት እያገለገለ አደገ። 1ኛ ሳሙ 3÷1-14።

በወቅቱ ዘመኑ መልካም ስላልነበር የእግዚአብሔር ቃል ክቡር ነበር፤ ራዕይም አይገለጥም ነበር። ይሁንና ሳሙኤል ካደገ በኃላ የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ በኩል ይተላለፍ ነበር። ዔሊ ካረፈ በኃላ ነቢየ እግዚአብሔር ሳሙኤል በእስራኤል ፈራጅ ሆነ። ዕድሜውን ሙሉ በእስራኤል ላይ ፈረደ። በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን ፈራጆች አደረጋቸው። እነርሱ ግን በአባታቸው መንገድ አልሄዱም። የእስራኤል ሽማግሌዎችም ወደ ሳሙኤል ተሰብስበው #እንደ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ንጉሥ አንግሥልን; አሉት። ሳሙኤልም በመጀመሪያ ሳኦልን ቀጥሎም ዳዊትን ቀብቶ አነገሠላቸው። ሳሙኤል በአገሩ በአርማቴም ዐረፈ። 1ኛ ሳሙ 25÷1።

⌗ 2.2.3 ዘመነ ነገሥት

ሳኦል የእስራኤል ንጉሥ እስከሆነበት ዘመን ድረስ እግዚአብሔር ለእስራኤላውን እንደ ሙሴ ኢያሱ ያሉ መሳፍንትን ያስነሣላቸው ነበር። ከእነርሱም በመጨረሻ የተነሣው ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን በእስራኤል ፈራጅ አድርጎ ሾማቸው። የሳሙኤል የበኩር ልጅ ኢዩኤል ሲባል ሁለተኛው ደግሞ አቢያ ነበር። እነርሱም በቤርሳቤህ ፈራጆች ነበሩ። ልጆቹም በቀና መንገድ አልተጓዙም፤ ነገር ግን ረብ ለማግኘት ፈቀቅ አሉ። መማለጃ በሉ፤ ፍርድንም አጓደሉ። በዚህ የተነሣ የእስራኤል ሕዝብ ወደ ሳሙኤል መጡ። ልጆችህ በአንተ መንገድ አልሄዱም። ልጆችህ በአንተ መንገድ አልሄዱም። ስለሆነም እንደሌሎች አሕዛብ የሚፈርድልን አንግሥልን፤ የሚፈርድልን ንጉሥ ስጠን አሉት። ሳሙኤል ነገሩ አስከፍቶት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም ለሳሙኤል 'በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን ናቁኝ እንጂ አንተን አልናቁምና የሚልሁን ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ።' አለው። ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ እና የንጉሥን ስርዓት ለሕዝቡ ነገራቸው።1ኛ ሳሙ 8÷11-12።

- ሳኦል

ሳኦል ማለት ከእግዚአብሔር የተለመነ ማለት ነው። ከብንያም ወገን የሚሆን ቂስ የተባለ ጽኑህ ኃያል ሰው ነበር። ቂስ ሳኦል የሚባል የተመረጠ መልካም ልጅ ነበረው። ሳኦል በአንድ ወቅት የአባቱ የሆኑና የጠፉ አህዮችን ፍለጋ በመጣ ጊዜ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ጠቋሚነት ተመርቶ በመቀባት አነገሠው። ሳኦል ወደገባያን ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ እግዚአብሔር ልባቸውን የነካው ኃያላንም ከሳኦል ጋር ሄዱ። ክፉዎች ሰዎች ግን ያድነን ዘንድ ይህ ሰው ማነው ብለው ጥቂት እንኳን እጅ መንሻ አላመጡለትም። ሳኦል ከነገሠ ከአንድ ወር በኃላ አሞናውያንን ጦርነት ገጥሞ ድል ሲነሳ እስራኤላውያን ሳሙኤልን አንግሥልን አሉት። ሳሙኤልም የሳኦልን ንግሥና በጌልጌላ አፀናለት። ከዚህም በኃላ ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ መሰነባበቻ ንግግር እና ምክርን አደረገ።

ሳኦል በነገሠ በሁለተኛ ዓመት ሦስት ሺህ ሰዎችን ከእስራኤል መረጠ። እነዚህንም ሳኦል ከልጁ ከዮናታን ጋር በመሆን ተካፈሉ። ፍልስጤማውያንም ከእስራኤላውያን ጋር ለመዋጋት ተሰባሰቡ። ከእነርሱም ጋር ሠላሳ ሺህ ሰረገሎች ስድስት ሺህም ፈረሰኞች በጣም ብዙ ሕዝብም ነበር። እስራኤላውያንም የፍልስጤማውያንን ብዛት አይተው ፈሩ፤ ተበተኑም። ሳኦልም ሳሙኤልን ሳይጠብቀና በድፍረት የሚቃጠል መስዋዕትንና የድኅንነት መስዋዕትን አቀረበ። ሳሙኤልም ይህን ባወቀ ጊዜ ገሰፀው፤ መንግሥቱ እንደማይፀናለትና እግዚአብሔር እንደልቡ የሆነ ሰው መምረጡን ነገረው።

ሳኦልና የተቀረው ሕዝብ ሠልፈኞችን ሊገናኙ ወደ ብንያም ገባያን (ጊብዓ) ሄዱ። በዚህ ወቅት ቁጥራቸው 600 ያህል ነበሩ። በዚህም ሳኦል፣ ልጁ ዮናታንና ሕዝቡም በብንያም ገባያን (ጊብዓ) ተቀምጠው አለቀሱ። በእስራኤል ዘንድ ከሳኦልና ዮናታን በስተቀር ሰይፍና ጦር የያዘ አልነበረም። የሳኦል ልጅ ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው ወደ ፍልስጤማውያን ሰፈር ለማለፍ ተማከሩ፤ ሄዱም። ሕዝቡ ግን መሄዳቸውን አላወቀም ነበር። ዮናታን ጋሻ ጃግሬውን እንዲህ አለው 'ፍልስጤማውያኑ በተመለከቱን ጊዜ ርቃችሁ ቆዩ ቢሉን ርቀን እንቆማለን፤ ወደ እኛ ውጡ ካሉን ግን እግዚአብሔር በእጃችን አሳልፎ እንደሰጣቸው ምልክት ይሁነን' አለው። ይህን ተባብለው ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር በገቡ ጊዜ ፍልስጥኤማውያኑ ዮናታንና ጋሻጃግሬውን ወደ እኛ ውጡ የምንነግራችሁ ነገር አለን አሏቸው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ፍልስጤማውያንን በእጃቸው አሳልፎ እንደሰጣቸው አወቁ። በመሆኑም ዮናታንና ጋሻጃግሬው ፍልስጤማውያን ላይ ወደቁባቸው። በእግዚአብሔር አጋችነትም በአንድ እርሻ መካከል ብቻ ሃያ ሰው ገደሉ። በሰፈሩም በእርሻውና በሕዝቡም ሁሉ መካከል ሽብር ነበረ፤ በሰፈሩ የተቀመጡና ለምርኮ የወጡት ተሸበሩ፤ ምድሪቱም ተናወጠች፤ ከእግዚአብሔርም ዘንድ ታላቅ ሽብር ተለቀቀባቸው። በብንያም ጊብዓ ያሉ የሳኦል ዘበኞችም ተመለከቱ፤ እነሆም የፍልስጤማውያን ሠራዊቱ ወዲህና ወዲያ እየተራወጠ ተበታተኑ። ሳኦልም ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሕዝብ እስኪ ተቋጠሩ፥ ከእኛ ዘንድ የሄደ ማን እንደሆነ ተመልከቱ አላቸው። ቆጠራ በተካሄደ ጊዜ እነሆ÷ ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው በዚያ አልነበሩም። በፍልስጥኤማውያን ሰፈር ግርግርታ እየበዛና እየጠነከረ ሄደ፤ ሳኦልና ከእርሱም ጋር የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተሰብስበው ወደ ውጊያው መጡ፤ እነሆም፥ በአሕዛቡ ወገን የእያንዳንዱ ሰው ሰይፍ በባልንጀራው ላይ ነበረ፥ እጅግም ታላቅ ድንጋጤ ሆነ። ቀድሞ ከፍልስጥኤማውያን ጋር የነበሩት ከእነርሱም ጋር ከሰፈሩ ዙሪያ የወጡት ዕብራውያን ደግሞ ከሳኦልና ከዮናታን ጋር ወደ ነበሩት እስራኤላውያን ለመሆን ዞሩ። ከእስራኤልም ሰዎች በተራራማው በኤፍሬም አገር የተሸሸጉት ሁሉ ፍልስጥኤማውያን እንደ ኰበለሉ በሰሙ ጊዜ እነርሱ ደግሞ ሊዋጉአቸው ተከትለው ገሠገሡ። እግዚአብሔርም በዚያ ቀን እስራኤልን አዳነ።

ሳኦልም መንግሥቱን በእስራኤል ላይ አጸና፤ በዙሪያውም ካሉት ከጠላቶቹ ሁሉ ጋር÷ ከሞዓብም፥ ከአሞንም ልጆች፥ ከኤዶምያስም፥ ከሱባም ነገሥታት፥ ከፍልስጥኤማውያንም ጋር ይዋጋ ነበር፤ በየሄደበትም ሁሉ ድል ይነሣ ነበር። እርሱም ጀግና ነበረ÷ አማሌቃውያንንም መታ÷ እስራኤልንም ከዘራፊዎቹ እጅ አዳነ። የሳኦልም ወንዶች ልጆች ዮናታን÷ የሱዊ÷ ሜልኪሳ ነበሩ፤ የሁለቱም ሴቶች ልጆቹ ስም ይህ ነበረ፤ የታላቂቱ ስም ሜሮብ÷ የታናሺቱም ስም ሜልኮል ነበረ። የሳኦልም ሚስት ስም የአኪማአስ ልጅ አኪናሆም ነበረ፤ የሠራዊቱም አለቃ ስም የሳኦል አጎት የኔር ልጅ አበኔር ነበረ። በሳኦልም ዕድሜ ሁሉ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጽኑ ውጊያ ነበረ፤ ሳኦልም ጽኑ ወይም ኃያል ሰው ባየ ጊዜ ወደ እርሱ ይሰበስብ ነበር። በአንደኛ ሳሙኤል ምዕራፍ ሰላሳ አንድ ከቁጥር አንድ ላይ እንደሚገኘው ፍልስጥኤማውያንም ከእስራኤል ጋር ተዋጉ፤ የእስራኤልም ሰዎች ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ÷ ተወግተውም በጊልቦዓ ተራራ ላይ ወደቁ። ፍልስጥኤማውያንም ሳኦልንና ልጆቹን በእግር በእግራቸው ተከትለው አባረሩአቸው፤ ፍልስጥኤማውያንም የሳኦልን ልጆች ዮናታንንና አሚናዳብን ሜልኪሳንም ገደሉ። ሰልፍም በሳኦል ላይ ጠነከረ÷ቀስተኞችም አገኙት፤ እርሱም ከቀስተኞቹ የተነሣ እጅግ ተጨነቀ። ሳኦልም ጋሻ ጃግሬውን እነዚህ ቈላፋን መጥተው እንዳይወጉኝና እንዳይሳለቁብኝ ሰይፍህን መዝዘህ ውጋኝ አለው። ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ነበርና እንቢ አለ። ሳኦልም ሰይፉን ወስዶ በላዩ ወደቀ። ጋሻ ጃግሬውም ሳኦል እንደ ሞተ ባየ ጊዜ እርሱ ደግሞ በሰይፉ ላይ ወደቀ÷ ከእርሱም ጋር ሞተ። በዚያም ቀን ሳኦል ሦስቱም ልጆቹ ጋሻ ጃግሬውም ሰዎቹም ሁሉ በአንድ ላይ ሞቱ።

◈ ዳዊት

ከዘመነ አብርሃም ሺህ ዓመት ያህል በኃላ በእስራኤል አገር ቤተልሔም በተባለች ከተማ ነገዱ ከይሁዳ የሆነው እሴይ ይኖር ነበር። እሴይ ስምንት ወንድ ልጆች ነበሩት። የመጨረሻው ልጅ ስም ዳዊት ይባላል። ዳዊት ማለት ልበ አምላክ ማለት ነው። ዳዊት ገና ብላቴና ሳለ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር። በዚያም በጎቹን ከሚነጥቁበት አንበሶችና ሌሎችም አራዊቶች መንጋጋ በጎቹን በማላቀቅ የሚጠብቅበት ከፍተኛ ኃይለ መንፈስ ቅዱስ ተጎናፅፎ ነበር። በወቅቱ በእስራኤል ነግሦ የነበረው ሳኦል ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምክንያት ከደረሰበት ክፉ መንፈስ እንዲርቅ ዳዊት በገና ይደረድርለት ነበር። የሳኦል ንግሥና

ባለመፅናቱ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነውን የእሴይ ልጅ ዳዊትን በወንድሞቹ መካከል ቀባው። እግዚአብሔርም ሰባት ሃብታትን ሰጠው።

እስራኤልና ፍልስጥኤም ይዋጉ በነበረበት በአንድ ወቅት ከፍልስጤማውያን ወገን የሆነ ስሙ ጎልያድ የተባለ ግዙፍ ሰው ተነሣ። ከጎልያድ ትልቅነት የተነሳ እስራኤላውያን ማሸነፍ አቅቷቸውና ፈርተው በሸሹ ጊዜ ዳዊት ለወንድሞቹ ስንቅ ለማድረስ በጦር ሜዳው ደረሰ። የሆነውንም ሁሉ ተመልክቶ በእስራኤል አምላክ ላይ በሚገዳደረው ጎልያድ አዘነ። ዳዊት ንጉሡ ሳኦል ጎልያድን እንዲዋጋ እድል እንዲሰጠው በማስፈቀድ በእግዚአብሔር አምላክ ስም በወንጭፍ ግንባሩን መቶ በመጣል ገደለው።

ዳዊትም ጎልያድን ከማሸነፉ በተጨማሪ በጦር ሜዳ በሚያሳየው ጀግንነት የተማረከው ንጉሡ ሳኦል በጦረኞች ላይ ሾመው። የሳኦል ልጅ ዮናታን ዳዊትን ስለወደደው የወንድማማችነት ቃልኪዳን አደረጉ።

የእስራኤል ህዝብ ሁሉ ዳዊትን በመውደዱ ክብሩን የሚያሳንስበት ስለመሰለው ሳኦል ቀናበት። ከዚህም በላይ ሳኦል ዳዊትን ሊገድለውም ሞከረ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር በመሆኑ ሊድን ቻለ። ዳዊትን በቤተዘመድነት ለመያዝ በማሰብ ሳኦል ታናሽ ልጁን ሜልኮልን ዳረለት። ይሁን እንጂ ዳዊት አማቱ ሳኦል ካልገደለው በቀር እንደማያርፍ ተረድቶ ወደ ኖብ ቀጥሎም ወደ ጌት ከተማ ኮበለለ። ከጌት ከተማም ዓዶላም ወደ ተባለ ዋሻ ሒዶ ተሸሸገ። ተጨንቀው ወደ እርሱ የሚመጡ ሰዎች በመብዛታቸው ዳዊት የእነርሱ አለቃ ሆነ። ሳኦል ዳዊት የተሸሸገበትን ስፍራ በማወቅ ወደዚያ ሄዶ ሰፈረ። በመሸ ጊዜ ዳዊት የሳኦልን መጎናፀፊያ በቀስታ ቆርጦ ወሰደ። ሳኦል ከድንኳኑ በወጣ ጊዜ ዳዊት የመጎናፀፊያውን ዘርፍ ቁራጭ እንደወሰደ አሳየው። በዳዊት እጅ ተላልፎለት ሳለ ስላልገደለውና ምሕረትን ስላደረገለት ሳኦል በስራው እጅግ ተፀፀተ።

ዳዊት የመላው እስራኤል ነገሥ ከመሆኑ አስቀድሞ የይሁዳ ሰዎች ከተማ በሆነችው ኬብሮን ለሰባት ዓመት ተኩል ያህል ዘመን ነገሠ። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥም በዳዊትና በሳኦል ቤተሰብ መካከል ጦርነት ይካሄድ ነበር። የተቀሩትን የእስራኤል ነገድ ይመራ የነበረው የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ ሲሞት ዳዊት መላውን እስራኤል በመጠቅለል ለሠላሳ ሶስተ ዓመታት በንግሥና መርቷል።

ዳዊት የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ታቦት ማደሪያ ይሆን ዘንድ ቤተመቅደስ ይሠራ ዘንድ ወደደ። ስለሆነም ታቦተ ፅዮንን ከአሚናዳብ ቤት አመጣ። በታቦተ ፅዮን መምጣጥ ዳዊት የንግሥና ልብሱን አውልቆና በደስታ ተውጦ በመዝለል ሲዘምር የተመለከተችው ሜልኮል በልቧ ናቀችው፤ በዚህም እስክትሞት ድረስ አልወለደችም። ዳዊት ለታቦተ ፅዮን ድንኳን ተከለ፤ በዚያም መሥዋዕቱን በእግዚአብሔር ፊት አሳረገ። እግዚአብሔር ለዳዊት በነብዩ ናታን በኩል እርሱ ቤተ መቅደሱን እንደማይሰራ ነገር ግን ዘሮቹ ግንባታውን እንደሚያከናውኑት የተስፋ ቃል ተነገረው።

ዳዊት የአሞንን ከተማ ረባትን እንዲወጉ ሰራዊቱን በአለቃቸው በኢዮአብ መሪነት ልኮ እርሱ ግን በኢየሩሳሌም ቀረ። በዚያም ሆኖ ሳለ በአንዳቸው ቀን በሰገነቱ ላይ ሲመላለስ የኦርዮን ሚስት ስትታጠብ ተመለከተ። በሐፀ ዝሙትም ተነደፈ። ልኮም የኦርዮን ሚስት የሆነችውን ቤርሳቤህን አስመጣ። ከእርሷም ጋር በመተኛቱ ፀነሰች። ዳዊትም መፅነሷን ከስድስት ወር በኃላ እንደሰማ ኦርዮንን ከጦር ሜዳ አስጠራው። ከሚስቱም ከቤርሳቤህ ጋር እንዲተኛ ሁለት ጊዜ ቢሞክርም ኦርዮን ወንድሞቹ ለጦርነት ተሰልፈው ሳሉ እኔ ቤት ገብቼ በምቾት አላድርም በማለቱ አልተሳካለትም። በመጨረሻም ለሰራዊቱ አለቃ ለኢዮአብ ጦርነቱ በተፋፋመበት ቦታ ኦርዮንን አሰልፈው እንዲሸሹ የሚገልፅ ደብዳቤ በራሱ በኦርዮን እጅ ልኮ አስገደለው። ቤርሳቤህንም ለራሱ አደረገ። በዚህም እግዚአብሔር ገሰፀው። የተወለደውም ልጅ ሞተ። ሆኖም በኃላ ላይ ከቤርሳቤህ ሌላ ወንድ ልጅ ወለደ፤ ስሙንም ሰሎሞን ብሎ ጠራው።

የዳዊት የመጀመሪያ ልጅ አምኖን አህቱ ትዕማርን አስገድዶ ቢያስነውራትም ዳዊት ምንም እርምጃ ባለመውሰዱ አቤሴሎም ተናደደ። ጊዜም ጠብቆ በአባቱ ዳዊት ላይ አመፀ። ህዝቡ ሁላ ከአቤሴሎም ጋር መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ ዳዊት ሸሸ። በዳዊት እና በአቤሴሎም ሰራዊት መካከል በተደረገ ጦርነት አቤሴሎም እንደሞተ ዳዊት በሰማ ጊዜ አዘነ። አምርሮም አለቀሰ። ወደ ኢየሩሳሌምም ተመለሰ። አንድ ነገዱ ከብንያም የሆነ ሳቡዔ የተባለ ሰው በዳዊት ላይ አመፀበት። ዳዊትም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም የሳኦል ቤት ደም ስላለበት የሳኦል ዘሮችን እንዲያጠፋ በነገረው መሰረት ዳዊት ይህንኑ አደረገ። ዳዊት በአጠቃላይ ህዝበ እስራኤልን ለአርባ ዓመት በንግሥና ከመራ በኃላ በሽምግልናው ጊዜ በእርሱ ፋንታ ሰሎሞን እንዲነግሥ ፈቀደ። ዳዊትም በመልካም ሽምግልና ዐረፈ።

◈ ሰሎሞን

ልበ አምላክ ዳዊት በሸመገለ ጊዜ ልጁ አዶንያስ ንጉሥ ሊሆን አሴረበት፡፡ ይሁንና ዳዊት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር እንደማልኩ ሰሎሞን ይነግሣል በማለት ሰሎሞንን አነገሠው፡፡ ሰሎሞን ማለት ሰላማዊ ሲሆን እስራኤልን በአንድነት ከመሩት ነገሥታት ሦስተኛውና የመጨረሻው ነው፡፡ የነገሠውም ገና ብላቴና ሳለ ነበር፡፡ እንደነገሠም የመገናኛው ድንኳን ወዳለበት ገባኦን ሄዶ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ፡፡ እግዚአብሔርም በራዕይ ተገልጦለት ምን እንደሚሻ ጠየቀው፡፡ ሰሎሞንም በእስራኤል ህዝብ ሁሉ ላይ መልካም እንዲፈርድ ጥበብና ማስተዋልን ይሠጠው ዘነድ ለመነ፡፡ እግዚአብሔር ለሰሎሞን የለመነውን ሁሉ ሰጠው፡፡

ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ካሳረገ በኃላ ታላቅ የሆነ ግብግን አደረገ፡፡ በዚያም ለሁለት አመንዝራ ሴቶች ጥበባዊ ፍርድን ፈረደ፡፡ ይህ ፍርድ ጥበብ የተሞላ በመሆኑ በእስራኤል ሁላ የሰሎሞን ዝና ተሰማ፡፡ ህዝቡም የእግዚአብሔር ጥበብ እንዳለበት አይተው ንጉሡን ተቀበሉ፡፡ ከኤፍራጠስ ጀምሮ እስከ ግብፅ ዳርቻ በመንግሥታት ላይ ሁሉ ነገሠ፡፡ ስለ ጥበቡ የሰሙ ነገሥታት ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡ ንግስተ ሳባም በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ ሄዳለች፡፡
ሰሎሞን በእግዚአብሔር ስም ቤት ለመስራት አስቦ የአባቱ ወዳጅ ወደነበረው ወደ ጢሮሱ ኪራም እንጨትና ባለሙያ እንዲልክለት መልዕክትን ላከ፡፡ ኪራምም የፈለገውን ሁሉ አደረገለት፡፡ በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤት መስራት ጀመረ፡፡ የእግዚአብሔርም ቃል ሰሎሞን በትዕዛዙና በሥርዓቱ ከተጓዘ ለዳዊት የገባለትን ቃል ኪዳን እንደሚያፀናለት ነገረው፡፡ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ስራ በሰባት ዓመታት ጨረሰ፡፡ ዳዊት የቀደሰውን የብርና የወርቅ ዕቃ ሁሉ አገባ፡፡ ቤቱንም በወርቅ አስለብጦ በፅንቁ አስጌጠው፡፡ የቃልኪዳኑን ታቦት ለፅዮን አስመጥቶ በቤተመቅደሱ አስገባ፡፡ እስራኤላውያንም በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ቀን በዓል አደረጉ፡፡

ሰሎሞን በመጨረሻ ዘመኑ ከእምነቱ ውጪ ከሆኑ ሴቶች ጋር ግኑኝነት በመፈፀሙና ለጣኦታቸው ማምለኪያ የሚሆን ቤትን በመስራቱ እግዚአብሔር ገስፆታል፡፡ በዚህም ምክንያት መንግሥቱ ለሁለት ተከፈለ፡፡ ይሁንና እግዚአብሔር ለአባቱ ለዳዊት ሲል ክፍፍሉን በሰሎሞን ዘመን አላደረገውም፡፡ ይሁን እንጂ በሰሎሞን ልጅ በሮብዓም ዘመነ መንግሥት እስራኤላውያን ለሁለት ተከፋፍለዋል፡፡ ሰሎሞን ከእርሱም በፊት ከነበሩት በአንፃራዊነት ሰላማዊ የሚባል የአስተዳደር ጊዜ የገጠመው ሲሆን በእስራኤል ላይ 40 ዘመን ነግሦ በዳዊት ከተማ ዐርፏል፡፡

◈ ሮብዓም

ሮብዓም የሰሎሞን ልጅ ሲሆን ከአባቱ በመቀጠል በትረ መንግሥቱን የተረከበ ነው፡፡ በወቅቱ እስራኤላውያን በጠቅላላ ወደ እርሱ ዘንድ ቀርበው #አባትህ ቀንበር ጭኖብናልና አንሳልን; የሚል ጥያቄ አቅርበውለት ነበር፡፡ ሮብዓምም ከጓደኞቹ የሰማውን ምክር መነሻ በማድረግ ቀንበሩን እንደሚያጠነክርባቸው በማስፈራራት ምላሽ ሰጣቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ኢዮርብዓም የተባለና በሰለሞን ዘመን ተሰዶ ወደ ግብፅ የሄደን ጎበዝ አለቃቸው አድርገው በማንገሥ 10 ነገድ ዋና ከተማቸውን ሴኬም በማድረግ ተገነጠሉ፡፡ ሮብዓምም የተቀረውን ሁለት ነገድ (የይሁዳንና የብንያምን) ብቻ በመያዝ ዋና ከተማቸውን ኢየሩሳሌም በማድረግ በዚያው ቀሩ፡፡ የሰሜኖቹ እስራኤል በሚል መጠሪያ እስከተማረኩበት ጊዜ ሲጠሩበት ደቡቦቹ ደግሞ ይሁዳ ተብለዋል፡፡ ለሁለት ከተከፈሉ በኃላ ለበርካታ ዘመናት እርስ በእርሳቸው ጦርነት ያደረጉ ሲሆን ይህም አዳክሟቸው ለጠላት ጦር አሳልፎ ሰጥቷቸዋል፡፡ ሰሜኖቹን እስራኤላውያን 19 ነገሥታት ደቡቦቹን 20 የይሁዳ ነገሥታት አስተዳድረዋቸዋል፡፡ በአጭሩ በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

- **አስራ ዘጠኙ የእስራኤል ነገሥታት**

ተ.ቁ	ንጉሥ	የነገሠበት ዘመን	መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ	መግለጫ
1.	ኢዮርብዓም	21	1ኛነገ 14÷20	የናባጥ ልጅና ቴቱልና መናገሻ ከተማው ደረገ
2.	ናዳብ	2	" " 15÷25	የኢዮርብዓም ልጅ
3.	ባአስ	23	" " 15÷33	ናዳብንና ቤተሰቡን ሁሉ ገድሎ የነገሠ

4.	ኤሳ	2	" " 16÷8	የባኦስ ልጅ
5.	ዘምሪ	7 ቀን	" " 16÷15	የባኦስን ቤተሰብ ከገደለ በኃላ ራሱን የገደለ
6.	ዘንበሪ	12	" " 16÷25	ሰማርያን ዋና ከተማው አደረገ
7.	አክዓብ	21	" " 16÷29	የዘምሪ ልጅና የጣኦት አምልኮን ከሚስቱ ከኤልዛቤል ጋር ያስፋፋ እና በነቢዩ ኤልያስ የተገሰፀ
8.	አካዝያስ	2	" " 22÷51	የአክዓብ ልጅና የቤተሰቡን መጥፎ አርዓያ የተከተለ
4.	ኤሳ	2	" " 16÷8	የባኦስ ልጅ
5.	ዘምሪ	7 ቀን	" " 16÷15	የባኦስን ቤተሰብ ከገደለ በኃላ ራሱን የገደለ
6.	ዘንበሪ	12	" " 16÷25	ሰማርያን ዋና ከተማው አደረገ
7.	አክዓብ	21	" " 16÷29	የዘምሪ ልጅና የጣኦት አምልኮን ከሚስቱ ከኤልዛቤል ጋር ያስፋፋ እና በነቢዩ ኤልያስ የተገሰጸ
8.	አካዝያስ	2	" " 22÷51	የአክዓብ ልጅና የቤተሰቡን መጥፎ አርዓያ የተከተለ
9.	ኢዮራም	7	2ኛ ነገስት 3÷1	በክፉ ስራው እግዚአብሔርን ያሳዘነ
10.	ኢዩ	28	" " 10÷36	የበዓልን ካህናት በዘዴ የፈጀ ቢሆንም ኢዮርብዓም ላቆማቸው ጣዖታት የሰገደ
11.	ኢዮአካዝ	17	" " 13÷1	ሃጥያት በመስራት እግዚአብሔርን ያሳዘነ
12.	ዮአስ	16	" " 13÷10	እግዚአብሔርን በማሳዘን ጀምሮ በንስሐ የጨረሰ
13.	ኢዮርብዓም	41	" " 14÷23	በእግዚአብሔር ፊት ክፉት ያደረገና በሶርያ ነገስታት የተማረከውን ሀገር ያስመለሰ
14.	ዘካርያ	6ወር	" " 15÷8	በክፉ መንገድ የተጓዘ
15.	ሰሎም	1ወር	" " 15÷13	ዘካርያን ገድሎ በሰማርያ የነገሠ
16.	ምናሔም	10	" " 15÷27	ክፉም አደረገ፤ እስራኤልንም ለአሶር ንጉሥ ግብር እንዲከፍሉ አደረገ።
17.	ፋቁሲያስ	2	" " 15÷23	ክፉም ሥራ ሠራ። ፋቁሔም ገደለው
18.	ፋቁሔ	8	" " 15÷27	የአሦር ንጉሥ ሕዝቡን ማርኮ የወሰደበት ሥርዓተ ንግሥና
19.	ሆሴዕ	2	" " 17÷1	በዘመኑ ሰማርያ ወደቀች

- **ሃያው የይሁዳ ነገሥታት**

ተ.ቁ	ንጉሥ	የነገሠበት ዘመን	መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ	መግለጫ
1.	ሮብዓም	17	2ኛዜና. 12÷13	የሰሎሞን የመጀመሪያው ልጅ ጣዖትን በማምለኩ እግዚአብሔር የቀጣው
2.	አብያ	3	" " 13÷2	በምግባር አባቱን ሮብዓምን የመሰለ
3.	አሳ	41	" " 16÷13	ደግና የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈፃሚ
4.	ኢዮሳፍጥ	25	" " 20÷31	የአባቱን የአሳን አርአያ የተከተለ ደግ ንጉሥ
5.	ኢዮራም	7	" " 21÷20	የኢዮሳፍጥ ልጅና የአክአብን ልጅ በማግባትና ወንድሞቹን ሁሉ በመግደል በክፋት የቆመ
6.	አካዝያስ	1	" " 22÷2	የኢዮራም ልጅና በኃጢአት እግዚአብሔርን ያሳዘነ
7.	ጎቶልያ	6	" " 22÷1	የአካዝያስ እናቱ የነገሥታት ዘሮችን ሁሉ ከኢዮአስ በስተቀር የገደለች

8.	ኢዮአስ	40	〃 〃 24÷1	ጣኦት አምላኪ የሆነና በክፉ ስራው በአገልጋዮቹ የተገደለ
9.	አሜሲያስ	29	〃 〃 25÷1	እግዚአብሔርን በማምለክ ጀምሮ ጣዖት በማምለክ የጨረሰ
10.	ዖዝያን	52	〃 〃 26÷3	የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈፃሚ
11.	ኢዮአታም	16	〃 〃 27÷1	ጻድቅና ደግ ሰው የነበረ
12.	አካዝ	16	〃 〃 28÷1	አምልኮ ጣኦትን ያስፋፋ ክፉ ሰው
13.	ሕዝቅያስ	29	〃 〃 29÷10	በጣም ጻድቅ የይሁዳ ንጉሥና በንስሐው 15 ዓመት በእድሜው ላይ የተጨመረለት
14.	ምናሴ	45	〃 〃 33÷1	መምለኬ ጣኦት የነበረ
15.	አሞን	2	〃 〃 33÷21	ክፉ የነበረና በአገልጋዮቹ የተገደለ
16.	ኢዮስያስ	31	〃 〃 31÷21	ባዕዳን አማልክትን ሁሉ ከአገሩ ያጠፋ እግዚአብሔርን የሚወድ ጻድቅ ንጉሥ
17.	ኢዮአክስ	3	〃 〃 36÷5	በክፉ መንገድ ቆሞ የነበረና በግብፃውያን ተማርኮ እዚያው የሞተ
18.	ኢዮአቄም	11	〃 〃 36÷9	ኃጢአትን በመስራት እዚአብሔርን ያሳዘነ
19.	ዮአኪን	3 ወር	〃 〃 36÷9	ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን በወረረ ጊዜ የነበረና ተማርኮ ወደ ባቢሎን የወረደ
20.	ሴዴቂያስ	11	〃 〃 36÷11	በክፉ ሥራው እግዚአብሔርን ያሳዘነ

2.2.4 ዘመነ ነቢያት /ካህናት/ ፀዋዌ

ነብይ ያለፈውንና የሚመጣውን የመናገር ስጦታ የተሰጠው የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው። ነብያት እውነተኛና ሀሰተኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። እውነተኞቹ ነብያት ደግሞ የፅሑፍና የቃል ተብለው ይከፈላሉ። የቃል ነብያት በስማቸው መፅሐፍ ያልተፃፈላቸው ሲሆኑ ነብዩ ኤልሳዕና ነብዩ ኤልያስ ለምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የፅሑፍ ነብያት ደግሞ በስማቸው መፅሐፍ የተፃፈላቸው ዐበይትና ደቂቅ ተብለው የሚከፈሉ ናቸው። ዐበይት ነብያት የሚባሉት ነብዩ ኢሳይያስ፣ ነብዩ ኤርምያስ፣ ነብዩ ሕዝቅኤልና ነብዩ ዳንኤል ናቸው። ደቂቀ ነብያት የምንላቸው ነብዩ ሆሴዕ፣ ነብዩ አሞፅ፣ ነብዩ ሚክያስ፣ ነብዩ ኢዩኤል፣ ነብዩ አብድዩ፣ ነብዩ ዮናስ፣ ነብዩ ናሆም፣ ነብዩ ዕንባቆም፣ ነብዩ ሶፎንያስ፣ ነብዩ ሐጌ፣ ነብዩ ዘካርያስና ነብዩ ሚልክያስ ናቸው። ሃብተ ትንቢት በቅድሚያ የተሰጠው የመጀመሪያው ሰው አዳም ሲሆን ሊቀ ነብያት የተባለው ደግሞ ነብይና መስፍን የሆነው ታላቁ ሰው ሙሴ ነው።

ክህነት 'ተክህነ' ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን አገለገለ ወይም ተሾመ ማለት ነው። ስለሆነም ክህነት ሹመት፣ አገልግሎት የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል። ካህን የቤተክርስቲያንን ምስጢር መፈጸም የሚችል በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ የማስታረቅ አገልግሎት የሚያከናውን ነው። እግዚአብሔር አዳምን ካህንና ነብይ አድርጎ ስለሾመው የመጀመሪያው ካህን አዳም ነው። በአጠቃላይ እስከ ሙሴ ያሉት አባቶች ትንቢትንና ክህነትን ገንዘብ ያደረጉት በሌሎች አባቶች በረከት እየተሾሙ ነው። ከሙሴ ጀምሮ ግን እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን በሕግ እንዲካኑ አደረገ። ዘዳ 28÷40፣ ዘጸ 29÷46፤ ዘሌ 8÷1። ከዚህ ውጭ ክህነት ሳይኖራቸው አገልግሎት ለመፈፀም የተነሱ ሰዎች ተቀጥተዋል። ዘኁ 16÷1-35፤ 2ኛዜና 26÷18-20

ዘመነ ነብያት በአጠቃላይ እስራኤላውያን በባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ከተማረኩበት አንስቶ እስከ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ያለውን ወቅት የሚያጠቃልል ነው። ዘመነ ነብያት የአይሁድ ንጉሥ ሴዴቅያስ በባቢሎን ምርኮ ከሞተ በኃላ ያለውን ጊዜ በተለይ የሚመለከት ክፍል ነው። ይህም በዘመን ሲቀመጥ ከ586 ቅ.ል.ክ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለው ጊዜ ነው። 2ዜና 36÷1-16.

በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የሚገናኘው በነብያቱ በኩል ነበር። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ነብያትን እየላከ ቢያስተምርም የሕዝቡ ልብ ከክፋት ሊመለስ አልቻለም። በዚህም እግዚአብሔር ህዝቡን ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። ሕዝበ እስራኤል በ922 ቅ.ል.ክ በሮብዓም ዘመን በአገዛዝ ተጣልተው እስራኤል /10 ነገድ/ እና ይሁዳ /2ቱ ነገድ/ ተባብለው ተከፈሉ። እርስ በእርሳቸውም ለዘመናት ይዋጉ ስለነበር ተዳክመው ለውጪ ጠላት ተጋልጠው በመቆየታቸው የሰሜኖቹን ህዝበ እስራኤል ስልምናሶር የተባለው የአሦር ንጉሥ በ792 ቅ.ል.ክ በመማረክ ከተማቸው የሆነችውን ሰማርያ ሲደመስስ ሕዝቡንም በቅኝ ግዛት ያዛቸው። በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ በኩል የነበሩት ሁለቱ ነገዶች ከሰሜኖቹ ሁኔታ ባለመማራቸው እንዲያውም የነዚያ መጥፋት የእነርሱን ትክክልኝነት ያረጋገጠ መስሏቸው ተደስተው ስለነበር እነ ኢሳይያስንና ኤርምያስን ሌሎችንም ነብያት እየላከ ከጥፋታቸው እንዲመለሱና እርሱን በማምለክ ሕጉን እንዲጠብቁ አስተማራቸው።

የባቢሎን ምርኮ

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ በመስራቱ በኤርምያስ እንደተነገረው ሦስት ዓመት ለባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ተገዛ። ኤር 22÷13-19፤ ኤር 22÷1። ነገር ግን ንጉሡ ኢዮአቄም በባቢሎን ላይ በማመፁ ናቡከደነፆር ጦሩን አስከትቶ በ597 ቅ.ል.ክ ኢየሩሳሌምን ከበበ። ኢዮአቄም ምሕረትን ለማግኘት ሲል የእግዚአብሔር ቤትን ንዋየ ቅዱሳት አውጥቶ ግማሹን ለናቡከደነፆር ገበረ። ዳን 1÷2 በኢዮአቄም መንበር ተተክቶ የነገሠው ልጁ ዮአኪንም እንደ አባቱ እግዚአብሔርን በማሳዘኑ የባቢሎን ሰራዊት ለሁለተኛ ጊዜ ኢየሩሳሌምን መዘበራት፤ ቤተመቅደሱን አጠፋ፤ አስር ሺህ ምርኮኞችንም አፈለሰ። ከድሆችና ከሀገሩ ህዝብ በስተቀር ማንም በኢየሩሳሌም አልቀረም። 2ኛ ነገ 24÷14። ዮአኪንም ወደ ባቢሎን ከተጋዘ በኃላ በኢየሩሳሌም ላይ የነገሰው ሴዴቅያስ ነው። ሴዴቅያስም እንደ ቀደሙት መሰሎቹ በስራው ሁሉ ክፉን አደረገ፤ በናቡከደነፆርም ላይ አመፀ። 2ኛ ነገ 24÷18-20 በዚህም በ587 ቅ.ል.ክ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ለመጨረሻ ጊዜ አጠፋት። 2ኛ ነገ 25፣1-7 ሕዝቅኤል፣ ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅ ተማርከው ወደ ባቢሎን የተወሰዱት በዚህ ዘመን ነበር። ዕዝራ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስና ዘሩባቤል የተባሉት ነብያት ደግሞ በምርኮ ጊዜ የተወለዱ ናቸው። የእስራኤላውያን የባቢሎን ምርኮ ያበቃው ከ70 ዓመት በኃላ ነበር። 2ኛ ዜና 36÷21። ይህ 70 ዓመት የተባለው ነብዩ ኤርምያስ /ኤር 25÷ 11-12/ ከተናገረ ጊዜ ጀምሮ (606) ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም እስከተመለሱበት ጊዜ ያለው ሲቆጠር ነው። አይሁዳውያን በምርኮ ሳሉ ባቢሎናውያን እንደ እስረኛ አልቆጠሯቸውም። መኳንንት የሆኑትን ብቻ በጥብቅ ይጠብቋቸው ነበር። የነገስታት ልጆች በቤተ መንግስት መብታቸው ተጠብቆ ይቀመጡ ነበር። የተመረጡ ወጣቶችም ንጉሱን በጥበብ ለማገዝ 3 ዓመት ትምህርት ቤት ይገቡ ነበር፤ ሌሎችም በእርሻና በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር። ይህም ናቡከደነፆር እስራኤልን የወረራት ለማጥፋት ወይም ለመጉዳት ሳይሆን ህዝቡ እርሱን አላገለግልም በማለታቸው ብቻ መሆኑን ያሳያል።

- የፋርስ ዘመንና የአይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ

(ከ539 ቅ.ል.ክ - 332 ቅ.ል.ክ)

በ539 ቅ.ል.ክ ዘመነ ባቢሎን አብቅቶ ዘመነ ፋርስ ሲጀምር የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ ወደ ሃገራቸው ይመለሱ ዘንድ ፈቀደላቸው። በ538 ቅ.ል.ክ የታወጀው የቂሮስ አዋጅ ለኢየሩሳሌም አዲስ ሕይወት ዘራባት። ዘሩባቤል ያሰባሰባቸው አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። መቅደሱንም መስራት ጀመሩ። ዕዝራ 3÷8-13። በሐጌ፣ በሶፎንያስ እና በዘካርያስ ትምህርት መሠረት ቤተመቅደሱ በ515 ቅ.ል.ክ ተጠናቀቀ። ዕዝ 6÷13-15። በ5ኛው መ/ክ/ዘ ቅ.ል.ክ አጋማሽ በነህምያ ትጋት የኢየሩሳሌም ከተማ እንደገና ተሰራች። የከተማዋ ቅጥርም በ52 ቀናት ተጠናቀቀ። ነህ 6÷15። በኢየሩሳሌም ላይ የተጫነው የፋርስ ምርኮም 200 ዓመታት ቆይቶ ነበር።

- የግሪክ ዘመን (ከ332 ቅ.ል.ክ - 142 ቅ.ል.ክ)

በ332 ቅ.ል.ክ ታላቁ እስክንድር የፋርስ መንግሥትን ድል በማድረግ ኢየሩሳሌምን ተቆጣጠረ። በዚህም የተነሳ የግሪክ ቋንቋ፣ ትምህርት፣ ባህልና ስልጣኔ የኢየሩሳሌምን መልክ ቀየረው። አንጥያኮስ 4ኛ /ከ175-

164 ቅ.ል.ክ/ መላዋን ኢየሩሳሌም በሁለመናዋ ግሪካዊት ለማድረግ ሲነሳ ከአይሁድ በኩል ታላቅ ተቃውሞ ገጠመው። ግዘረትን፣ ሰንበት ማክበርን፣ መሥዋዕትን፣ ኦሪት ማንበብን ከለከለ። በምትኩም በከተማው ለግሪክ አማልክት መሰዊያ ሰሩ። ይህም አልበቃ ብሎ በ168 ቅ.ል.ክ በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መሰዊያ ላይ እሪያ አረደበት። ይህን በመቃወም በ167 ቅ.ል.ክ ሽማግሌው ካህን ማትያስ ሞዳይን በምትባል ትንሽ ከተማ ውስጥ ለግሪክ ጣኦት እንዲሰዋ የታዘዘውን ትዕዛዝ ባለመቀበል የንጉሡን አገልጋይ ገደለው። ይህም ለመቃብያን ንቅናቄ መቀስቀስ ምክንያት ሆነ።

- ዘመነ መቃቢያን

የመቃቢያን ንቅናቄ እስራኤልን ከቅኝ ገዢዎች ነፃ ለማውጣት የተደረገ የነፃነት እንቅስቃሴ ነው። ይህን ንቅናቄ የወጠኑት የካህኑ የማትያስ ልጆች ናቸው። የንቅናቄው መሪም ይሁዳ ዘመቃቢ ይባላል። በ165 ቅ.ል.ክ ቤተመቅደሱ ታድሶ ተቀደሰ። ይህም 'የመቅደስ መታደስ በዓል' እየተባለ መከበር ጀመረ። ዮሐ 10÷22 ኢየሩሳሌም ከግሪክ ቅኝ ግዛት ነፃ የወጣችው በ142 ቅ.ል.ክ ነው። ከዚህ በኃላ ለተወሰኑ ዓመታት ኢየሩሳሌም የነፃይቱ ይሁዳ ዋና ከተማ ሆነች።

- የሮም ዘመን

በ63 ቅ.ል.ክ ፖምፔይ የተባለው የሮም የጦር አዛዥ ኢየሩሳሌምን ተቆጣጠሮ የሮም ቅኝ ግዛት አደረጋት። በዚህ የተነሳ አገሩና ህዝቡ በጠቅላላ ከሮም ቁሳር እጅ በታች ሆኑ። በግሪካዊው ባህልና ስልጣኔ ላይ የሮማውያን ባህልና ስልጣኔ ተዳምሮ የኢየሩሳሌምን አይሁዳዊ ባህልና ኦሪታዊ እምነት መሸርሸር ጀመሩ። በዚህ ረዥም የተፋልሶ ዘመን አይሁዳውያን የእነርሱ ያልሆነ ፀባይ ከመሸመታቸው በተጨማሪ እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ የተለያዩ የእምነት ቡድኖችም ተመስርተዋል። የሮማ ኢምፓየር በግዛቱ ስር የሚገኙትን ህዝቦች ያከብራል እንዲባል የሃይማኖት ነፃነት በመስጠቱ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ ኤሳውያን፣ ሳምራውያን የተባሉና ሌሎችም ቡድኖች በምድረ ፍልስጥኤም ተቋቁመው ነበር። በአጠቃላይ እስራኤላውያን በምርኮ ጊዜም ከምርኮ በኃላም ህዝቡን እየመከሩ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቁ፣ መስዋዕት በማቅረብ ያገለግሉ የነበሩት ካህናት/ ነቢያት ናቸው። በዚህ መልኩ አዳምን ከሲኦል ባርነት ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ ለማወጣት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር የቆረጠለት 5500 ዘመን ደረሰ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው 'ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ'።

ምራፍ ሦስት

የአማናዊቷ ቤተክርስቲያን አመሠራረት

3.1 የክርስቶስ መምጣት ተስፋና የእስራኤል ሕዝብ አምልኮ

አስቀድሞ ባለው ምዕራፍ መጨረሻ ላይ በተመለከተው ሁኔታ ባለው የቅኝ ግዛት ቅብብሎሽ ሂደት ውስጥ አይሁድ ባሕላቸው፣ ሃይማኖታቸውና አኗኗራቸው ሁሉ ችግር ላይ ወድቆ ነበር። በዚያን ዘመን የዓለም ሕዘብ ጣዖት በሚያመልክበት ወቅት እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበሩት የእሥራኤልና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብቻ ነበሩ። ምንም እንኳን ከአይሁድ መካከል ጥቂቶች ፍጹም እምነት ስለነበራቸው የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣት ቢጠባበቁም /ዮሐ1÷46፤ ሉቃ 2÷25-32/ ብዙዎች ግን የተሳሳት እምነትን በመከተል በነብዩ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት ስለ ምድራዊ ገዥ ነው ይሉ ነበር።
ክርስትና በፍልስጥኤም ምድር ሲመሰረት ፍልስጥኤም እንደ ሌሎች የመካከለኛ ምስራቅ የሰሜን አፍሪካ እና የታናሽ እስያ አገሮች በሮም ቅኝ ግዛት ስር ነበረች። የቅኝ አገዛዙም ስለመረራቸው ነጻ ወጥተው የዳዊት መንግስት እንደገና ተመስርታ ለማየት እጅግ ይናፍቁ ነበር። ነገር ግን በሃገሪቱ ውስጥ የነበሩ ህዝቦችም የተከፋፈለ የሃይምኖት እና የፓለቲካ ክፍል ነበራቸው። የጌታችን በሥጋ መገለጫ በተቃረበበት ዘመን ደግሞ ራሳቸው አይሁድ እንኳን ሳይቀሩ በእምነትም በአመለካከትም ተለያይተው የተለያዩ ቡድኖች/ክፍሎች ተመስርተው ነበር። ከእነዚህ የሃይማኖት ክፍሎች ዋናዎቹ የፈሪሳውያን፤ የሰዱቃውያና እና የኤሳው ክፍሎች ነበሩ።

ፈሪሳውያን

ፈሪሳዊ ፓራሽ ከሚለው የዕብራይስጥ ቋንቋ የወጣ ቃል ነው ትርጉሙም የተለየ ማለት ነው። እነዚህ ወገኖች አፍአዊ ትእዛዝን ብቻ በመጠበቅ **የሕግ ፈጻሚዎች መስለው የሚታዩ** እንደነርሱ እርምጃ የማይሔደውን የሚወቅሱ የሚከሱ ነበሩ።

ፈሪሳውያን ምንም እንኳን የቀኝ ግዛት ቀንበር መላልሶ ቢያደቃቸውም ባሕልና ልምዳችን አይነካ የሚሉ ነበሩ። በሃይማኖት የሙሴን የሕግ መጻሕፍትንና የነቢያትን ትንቢት የምንቀበል እኛ ብቻ ይላሉ፤ ፈጻሚዎችም እኛው ብቻ ነን ይላሉ። ከአይሁድ ዘር ውጭ ከሆነ ከማንኛውም ጎሳና ዘር ጋር የሚደረግ የባሕልና የሥልጣኔ መቀራረብን እንደመርከስ አሊያም ሕግን እንደመተላለፍ ይቆጥሩት ነበር።

አምስቱ ብሔረ ኦሪት (የሙሴ ሕግ) ሞራላዊውን የሥነ-ምግባር ትእዛዝና የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ሕግ ሁሉ አጠቃለው የያዙ መሆናቸውን የሚያምኑ ሲሆኑ የሙሴ ሕግ ጋርም የሚተባበሩ ያልተጻፉ አፍአዊ ወጎች ወይም ትውፊቶች በእግዚአብሔር በቅድመ አያቶቻቸው የተገሩጹባቸው (የተነገሯቸው) መሆናቸውን በማመን ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እያስተላለፉ እንዳሉም ያምናሉ። እነዚህን ባሕላዊ ወጎች ወይም ትውፊቶች እየተረጎሙና እያባዙ ልዩ ልዩ አዲስ ሥርዓቶችንና ሃይማኖታዊ ቀኖናዎችን በተራ አይሁዳውያን ምእመናን ላይ ይጭኑባቸው ጀመር። በዚህም ወግና ባሕላቸው ጌታ ነቅፏቸዋል። በመልካቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በትምህርታቸው፣ በዘራቸው እና በእምነታቸው ከሌሎች የተሻልን ነን ብለው ስለሚመጻጸደቁ ግብዞች ተባሉ። (ማቴ. 6፥2፣5፣16፣ 7፥15፣ 15፥7፣ 22፥18፣ ማር. 12፥15፣ ሉቃ. 11፥37-41፣ 12፥1፣56፣ 13፥15)

ከሮም አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ብርቱ ጉጉት ነበራቸው። እንደ እነርሱ አስተሳሰብ ‹‹መሲህ ሲመጣ የጦር ኃይል አቋቁሞ እርሱ የጦር መሪ በመሆን የሮማን የቀኝ ግዛት ቀንበር አውልቆ ጥሎ የዳዊት መንግሥትን የማያድል ነው።›› በማለት ይጠባበቁ ነበር። በዕለታዊ ኑሯቸው ብዙ ሀብት የሌላቸውና በእውቀት መጠኞች ነበሩ።

የመሲሁን መምጣት ነቅተውና ተግተው ይጠብቁ ነበር። ከሮም አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ብርቱ ጉጉት ነበራቸው። እንደነርሱ አስተሳሰብ #መሲህ ሲመጣ የጦር ኃይል አቋቁሞ እርሱ የጦር መሪ በመሆን የሮማን የቀኝ ግዛት ቀንበር አውልቆ ጥሎ የዳዊትን ቤተ መንግሥት የሚያድስ ነው; በማለት ይጠባበቁ ነበር። ምንም እንኳን ከትንሣኤ በኋላ የሥጋዊ ኑሮ /ማግባት፣ መጋባት/ አለ ብለው ቢያምኑም ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ያውቁ ነበር። ፈሪሳውያን በሃሳባቸው ሰው የሚጸድቀው በግል ሕይወቱና ሕግን በመፈጸሙ ነው የሚሉ ነበሩ። /ሐዋ 15÷5/ ምንም እንኳን ግትር ሀሳብ ቢኖራቸውም በመካከላቸው እንደ ኒቆዲሞስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ያሉ ቅን ሰዎች ይገኙባቸው ነበር። ብዙዎቹ ፈሪሳውያን በሕግ ላይ የተጨመረውን ወግ እየተመለከቱ ዋናውን የሕግ መንፈስ ፍርድን፣ ምህረትን፣ ታማኝነትን ረስተው አምልኮታቸውም ለመታየትና ውዳሴ ከንቱ በመሻት ነበር እንጂ እግዚአብሔርን በመፍራት በማክበር ከልብ በመነጨ ስሜት አልነበረም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩራት መንፈስና በመመጻደቅ ጎሳብ የተሞሉ መሆናቸውን በመመልከት እንደገና መወለድ እንዳለባቸው አሳስቧቸዋል። (ማቴ. 23፥13-34፣ ዘሌ. 18፥1-5፣ ዮሐ. 3፥3-8)

የፈሪሳውያን መለያ ጠባዮች (ማቴ. 23፥6-15፣ ሉቃ. 11፥42-52)

፩. የልብሳቸውን ዘርፍ እያስረዘሙ በልብሳቸው ላይ 10ቱን ትእዛዛት ይጽፉ ነበር።

፪. በማዕድ የከበሩት ወንበር ይሹ ነበር፤ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር ይፈልጉ ነበር።

፫. በገበያ የሰላምታንና መምህር ሆይ ‹‹ረቡኒ›› መባልን ይወዳሉ።

፬. ጸሎት ያስረዝማሉ።

፭. የመበለቶችን ቤት ይበዘብዛሉ።

ፈሪሳውያን በጎሳባቸው ሰው የሚጸድቀው በግል ሕይወቱና ሕግን በመፈጸሙ ነው የሚሉ ነበር። (ሐዋ. 15፥5) ምንም እንኳን ግትር ጎሳብ ቢኖራቸውም በመካከላቸው እንደ ኒቆዲሞስና ቅዱስ ጳውሎስ ያሉ ቅን ሰዎች ይገኙባቸው ነበር። ብዙዎች ፈሪሳውያን በሕግ ላይ የተጨመረባቸው ወግ እየተመለከቱ ዋናውን የሕግ መንፈስ ፍርድን፣ምሕረትን፣ታማኝትን፣ረስተው አምልኮታቸውም ለመታየትና ውዳሴ ከንቱ በመሻት ነበር እንጂ እግዚአብሔርን በመፍራት በማክበር ከልብ በመነጨ ስሜት አልነበረም።

ፈሪሳውያን ጌታ በምድር ተመላልሶ ሲያስተምር ብዙ ጊዜ ይፈትኑት ነበር፡፡ በመጨረሻም ጌታን ለመግደል ተማክረው /ምንም እንኳን ጌታ የተሰቀለው በገዛ ፈቃዱ ቢሆንም/ በእነርሱ አስተሳሰብ ሰቅለውታል (ዮሐ 11÷47-57)፡፡ አንዳንዶቹ አይሁዳውያን በክርስቶስ አምነዋል፡፡

ሰዱቃውያን

እነዚህ ወገኖች የፈሪሳውያን ተቃራኒዎች ናቸው፡፡ ለባሕል እና ለሥነ ስርዓት ግድ የለሾች ናቸው፡፡ ከሀብታሞችና ከባለሥልጣኖች የተውጣጡ የካህናት ክፍል ነው፡፡ የዘር ግንዳቸውም የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሊቀካህናት ከነበሩት ከሳዶቅ ልጆች ተያይዞ የመጣ ነው፡፡ የጽርዓውያን ቁሳዊ ባሕልና ሥልጣኔን የሚደግፍና ስለሌላ ባሕልና ሃይማኖት ግድ የሌለው ከቀኝ ገዥዎች ጋር ተስማምተው በእነርሱ ሥልጣኔ ለመጠቀም ብቻ የሚፈልጉ ቡድኖች ነበር፡፡ ኑሯቸውም ብዙ የባዕድ ባሕል የተጫነው ነበር፡፡ ስለዚህ ሰዱቃውያን የዘመኑ ቁስ አካላውያን (ማቴሪያሊስቶች) ነበሩ፡፡ (ማቴ. 22፥23-28) ይህም የጽርዕ ተገዢነት ውጤት ነው፡፡ ሳንሄድሪን በተባለው የአይሁድ የፍርድ ሸንጎ በሚቀመጡበት ጊዜ የሰው ነገር የማይገባቸው ጎሳበ ግትር ነበሩ ይባላል፡፡

ባለሥልጣኖችን በፈሪሳውያን ላይ በማስጨከን ብዙ ጭቆናን ያደርሱባቸው የነበሩት ሰዱቃውያን ከሮም መንግሥት ጋር በመስማማት በሕዝቡ መካከል ሰላም እንዲኖር ይጥሩ ነበር፡፡ በእምነታቸው ሥርዓታዊ ሕግን ከመንፈሳዊ ሕግ አልቀው /አብልጠው/ የሚያዩ ነበሩ፡፡ ከሃይማኖት መጻሕፍትም የሙሴ ሕግን ብቻ ይጠቀሙ ነበር፡፡ በራሳቸው አስተያየት ይተረጉሙት ስለነበር በትንሣኤ ሙታን በሚመጣው ዓለም የሰው ልጅ እንደ ሥራው ዋጋውን ይቀበላል የሚለውን አያምኑም ነበር፡፡ (ማቴ. 22፥23-33፣ ዘዳ. 25፥5-11፣ ሐዋ. 32፥2፣ ማር. 12፥19፣ ሉቃ. 20፥29)
ለሰው ልጅ ነጻ ፍቃድ እንዳለው የሚያምኑ ሲሆኑ በተጨማሪ የሰው ልጅ መጨረሻው ሞት ስለሆነ በሕይወቱ ሳለ የሚያስፈልገውን ሁሉ እየፈጸመ እስከተቻለው ድረስ መደሰት አለበት፡፡ (ሄዶኒዝም) ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡ ክርስቶስን አሳልፈው ከሰጡት በኋላም ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለው ሲሰብኩ የነበሩ ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን (ሐዋርያትን) ወደ ወኅኒ ጥለዋል፡፡ (ሐዋ. 4÷1-22) እንዲሁም የክርስቶስን ትንሣኤ ለማጭበርበር ለመቃብር ጠባቂ ወታደር የሐሰት ምስክርነት እንዲሰጡ የገንዘብ ኃይላቸውን ተጠቅመዋል፡፡ ባይሳካላቸውም እውነቱ በጊዜ ተገልጧል፡፡ (ሐዋ. 4፥1-2) ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ ስለሰዱቃውያን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡ (ማቴ. 11፥6-12፣ ማር. 12፥26-27)
ከጠላቶቻችን እጅ ነጻ ያወጣናል ባዮች ነበሩ፡፡

ኤሳውያን (ኤሰናውያን)

እነዚህ ወገኖች የመነናውያን ማኅበር ነበሩ፡፡ ከፈሪሳውያን ጋር በአመለካከት ተጣልተው የተገነጠሉ ንዑስ ቡድኖች ነበሩ፡፡ ይኸውም፡- ፈሪሳውያን በጦር ኃይል ነጻ እንወጣለን ሲሉ ኤሴናውያን ደግሞ በተአምራት በእግዚአብሔር ኃይል ፍልስጤም ነጻ ትወጣለች ወይም መሲህ ሲመጣ በተአምራት ከጠላቶቻችን እጅ ነጻ ያወጣናል ባዮች ነበሩ፡፡ ኩምራን በምትባለው ቦታ (አካባቢ) ገዳም ገድመው የመሲሕን መምጣት ይጠባበቁ ነበር፡፡ ኤሰኖች (ኤሰንስ) በመባል ይታወቃሉ፡፡ ኤሳውያን በገዳማቸው በጾም፣ በጸሎት፣ በትህትና የሚኖሩ ነበሩ፡፡
እነዚህ ወገኖች፡-

- መጻሕፍትን በመጻፍ፣
- ልዩ ልዩ የእጅ ሥራዎችና የግብርና ሥራን በመሥራት፣
- ጸሎትን በማድረስ፣ ሰንበትን በማክበር፣ ኃጢአትን በማስወገድ የንጽሕና የጥምቀት የንስሐና የኑዛዜ ሥርዓትን በመፈጸም ይኖሩ ነበር፡፡

በዚህ ሥርዓት የሚመራቸው አለቃቸውም የጽድቅ መምክር እየተባለ የሚጠራ ሲሆን እነሱም ተላውያነ ፍኖት ደቂቀ ብርሃን በመባል የአምላክ ብርሃን ተከታዮች መሆናቸውን ያመለክቱ ነበር፡፡

የእምነታቸው መሠረታዊ ዓላማ እግዚአብሔርን መውደድ፣ ግብረ ሠናይን መፈጸምና ሰውን ማፍቀር ነበር። ሁሌም እሴናውያን ሀብታውን አንድ ላይ አድርገው በመተዳደራቸውም የዚህን ዓለም ብልጽግና ይምቁ ነበር። በነፍስ እንጂ በሥጋ ሕያውነት አያምኑም ነበር። እንዲያውም ሥጋ የነፍስ ወኅኒ ቤት ነው የሚል እምነት ነበራቸው። የነበራቸው ሥርዓተ አምልኮ በተግባር ሲታይ ከአይሁዳዊ ጠባይ ይልቅ ወደ ዞራስትራዊና ፕላቶናዊ ጠባይ ያዘነበለ ነው። ይህም የፋርስ ተገዢነት ውጤት መሆኑ ነው።

ኤሰኞች በዚህ ሥርዓተ ብህትውና ተጠምደው ሲኖሩ በ68 ዓ.ም በአይሁዳውያን ነጻ አውጪ ግንባሮችና በሮማውያን ወታደሮች መካከል በተደረገው ኃይለኛ ጦርነት ምክንያት ይህ ገዳም የነጻ አውጪ ግንባሮች ደጋፊ እንደሆነ ተቆጥሮ ሮማውያን ፈጽመው ደመሰሱት። ይህንኑ የኤሰኖች ታሪክና የጥንታውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ለማነጻጸርና ለማመሳከር በማስቻሉ ትልቅ የእምነት አስተዋጽዖ አድርጓል።

የአይሁዳውያንና የሳምራውያን ልዩነት

ፈሪሳውያን (አይሁድ)

- 5ቱን የሙሴንና የነቢያትን መጻሕፍት ይቀበላሉ።
- ንጹሕ የአብርሃም ዘሮች ናቸው።
- ጣዖት አያመልኩም።
- በሰሎሞን ቤተ-መቅደስ ያመልኩ ነበር። (በኢየሩሳሌም)
- ትንሣኤ ሙታን በዚያም ማግባትና መጋባት አለ ብለው ያምናሉ።
- ብዙ ሀብት የሌላቸው መጠነኞች ነበሩ።
- ሕግን የሚጠብቁ ባሕልና ልምዳችን አይነካ የሚሉ።

ሳምራውያን (ሰዱቃውያን)

- 5ቱን የሙሴ መጻሕፍት ብቻ ይቀበላሉ።
- የአይሁድና የአሕዛብ ቅልቅል (በምርኮ)
- ጣዖት ያመልኩ ነበር።
- በገሪዛን ተራራ ቤተ መቅደስ ሠሩ።(ዕዝ. 4፥1፣ዮሐ. 4፥20)
- ሀብታምና የካህናት ክፍል
- ለባሕል፣ ለሥነ-ሥርዓትና ለሃይማኖት ግድ የሌላቸው ናቸው።

ከላይ በተጠቀሰው መለያየት ምክንያት አይሁድ ሳምራውያንን አጥብቀው ይጠሏቸው ነበር። ለዚህም በብሉይ ኪዳን አይሁድ ከባቢሎን ሲመለሱ ሳምራውያን ከእነርሱ ጋር ቤተ መቅደስን ለመስራት ቀረቡ። ዘሩባቤል ግን ጥንታውያን የእስራኤል ዘሮች ስላይደሉ አልተቀበላቸውም። ዕዝ 4÷1-4። ነህምያም ከኢየሩሳሌም አባረራቸው። ነህ 13÷14-19። በሐዲስ ኪዳንም ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይገናኙም /አይተባበሩም/ ነበር። ዮሐ 4÷14።

ሳምራውያን መባል እንደ ንቀት ይቆጠር ነበር። ሉቃ 10÷33-37፤ ዮሐ 8÷48። ለዚህ ነው አንተ አይሁዳዊ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምትሆን ከእኔ መጥተህ እንዴት ትለመናለህ ያለችው። አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩምና። ዮሐ 4÷7-10። አይሁድ ቢነቅፏቸውም በሰማርያ ክርስቶስን የተቀበሉ ብዙ ነበሩ። ዮሐ 4÷39-42። ከተፈውሱት ከአሥሩ ለምጻሞች ክርስቶስን ያመሰገኑ ሳምራውያን ብቻ ነበሩ። ሉቃ 17÷16። እንዲሁም በመልካም አርአያ የተጠቀሰው ርህሩህ ሣምራዊ ብቻ ነው። ሉቃ 10÷32። ጌታ ከትንሣኤው በኋላ ደቀመዛሙርቱን እንዲመሰክሩ ባዘዛቸው መሠረት ፊሊጶስ ያስተማረባት ናት (ሐዋ. 1፥8፣ 8፥5-25)። **ሳምራውያን** በዓመት ሦስት ጊዜ ገሪዛን ተራራ ላይ በዓለ ኀምሳን የዳስን በዓል ያከብሩ ነበር።

3.2 የኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ

የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የመሆን ታሪክ የሚጀምረው በቅዱስ ገብርኤል አብሳሪነት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተፀነሰ በኋላ በይሁዳ ቤተልሔም ከተወለደ ጀምሮ ነው። ይሁንና የጌታ መወለድ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ ሳይሆን ትንቢት ተነግሮለት ዘመን ተቆጥሮለት የተከናወነ ነው። በእርግጥም እርሱ ጌታ ቅድመ ዓለም የነበረ በኋላም በተዋሕዶ ፍፁም ሰው የሆነ ከኃጢአት በቀር ሁሉን የፈፀመ ስለ በደላችን ተላልፎ የተሰጠ፤ ስለእኛ የሞተ በሞቱም ሞትን ድል የነሳ ነው። ዕብ 4÷4

የትውልድ ሐረጉ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ ሀረግ ከዳዊት ዘር፤ ከቤተይሁዳ ሲሆን፣ የሰው ልጅ የተባለ የአብርሃም ልጅ፤ የያዕቆብ ልጅ፤ የይሁዳ ልጅ የሆነ በአጠቃላይ ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ትውልድ ሁሉ 46 የሆነ ነው። ማቴ 1÷1-17

- **ፅንሰቱ**

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰው በብስራተ ገብርኤል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። ይህ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል በመጀመሪያ ወደ ዘካርያስ በተላከ በስድስተኛው ወር ወደ ድንግል ማርያም ተልኮ ኢየሱስን እንደምትወልድ አበሰራት። ማርያምም እነሆ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ባለችው ጊዜ በማህረ መንፈስ ቅዱስ ቃልን ጸንሳለች።

- **ልደቱ**

እስራኤላውያን በሮም ቅኝ ግዛት ሥር በነበሩበት ጊዜ በይሁዳ፤ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ 9 ኪ.ሜ ርቃ በምትገኘው በቤተልሔም ከተማ በአውግስጦስ ቄሳር ዘመን ነቢያት እንደተናገሩት በከብቶች በረት መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ። ይህም እንዲህ ነው፡- አውግስጦስ ቄሳር ሕዝቡ ሁሉ እንዲፃፍ አዋጅ አስነገረ፤ ይህም ህዝቡ ሁሉ በየወገኑ እንዲመዘገብ የሚል ነበር። ዮሴፍም ከንጉሥ ዳዊት ቤት ስለሆነ ቅድስት ማርያምን ይዞ ወደ ቤተልሔም ተጓዘ። ቤተልሔምም በደረሱ ጊዜ ለእነርሱ የሚሆን ማደሪያ ስፍራ ስላላገኙ በከብቶች በረት አደሩ። በዚያም ሳሉ የድንግል ማርያም የመውለጃ ጊዜዋ ደርሶ ነበርና የበኩር ልጅዋን ወለደችው። በጨርቅም ጠቅልላ በግርግም አስተኛችው። እርሱ የዳዊት ልጅ እንደሆነ እንዲሁ የዳዊት ፈጣሪ የሆነ ከአብርሃም ዘር እንደተገኘ እንዲሁ ከአብርሃም በፊት የነበረ፤ ባልነበረበት

ባሕርይ ይገኝ ዘንድ በሰው ባሕርይም ይጠብቁት ለነበሩት እረኞች መላእክት አበሰሯቸው። ሉቃ 2÷1-10፣ ሉቃ 1፣26።

- **እድገቱ**

ጌታችን በተወለደ በ8ኛው ቀን ተገዘረ። ገና ሳይፀነስ መልአኩ እንደተናገረው ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ፤ በ40ኛውም ቀን ወደ ቤተመቅደስ ወሰዱት። ሁለት ዓመት ሲሞላው ሰብዓ ሰገል መጥተው ሰገዱለት፤ እጅ መንሻም አቀረቡለት። ንጉስ ሔሮድስ ሕፃኑን መግደል ይፈልግ ነበር። የጌታ መልአክም በሕልም ለዮሴፍ ታየና "ሔሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልጋልና ተነሳ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ።" አለው። ዮሴፍም እናቱንና ሕፃኑን ይዞ ወደ ግብፅ ሸሸ። በዚያም ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ቆየ። ሔሮድስም ከሞተ በኃላ ወደ ናዝሬት ተመለሱ። 12 ዓመት ሲሞላው ወደ ኢየሩሳሌም መጣ። በዚያም እጅግም ብዙ ተዓምራትን ያደርግ ነበር። ጥንት የሌለው ቃል በሁሉም ፍፁም ሲሆን በእግዚአብሔርና በሰው ፊት በጥበብና በቁመት፣ በሞገስም አደገ። ማቴ 1÷21፤ሉቃ 1÷31፤ማቴ 2÷1-21፤ማቴ 2÷13፤ ማር 6÷3፤ ሉቃ 2÷40-52።

- **ጥምቀቱ**

መጥመቀ መለኮት ዮሐንስ ለጌታ መገለጥ ብዙ ሰዎችን ካዘጋጀ በኃላ ኢየሱስ ክርስቶስ በባሪያው በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ መጣ። ዮሐንስም " እኔ በአንተ ልጠመቅ እሻለሁ፤ አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ?" አለው። ጌታችን ኢየሱስም " አሁንስ ተው እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና።" ባለው ጊዜ ተወው፤ አጠመቀውም። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ ከሰማይ በመጣ በአብ ቃል በርግብ አምሳል በወረደ በመንፈስ ቅዱስ ተመስክረለት ማቴ 3÷17፤ ማር 1÷2-22፤ ዮሐ 1÷31-34። ከዚያም በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ። በዚያም 40 ቀን እና ሌሊት ፆመ። በሰይጣንም ተፈተነ። ጌታ ኢየሱስ ግን የሰይጣንን ሥልጣን ሽሮ ደቂቀ አዳምን ለማዳን መጥቶ ነበርና የሰይጣንን ፈተና ድል አደረገ። ማቴ 4

- **ትምህርቱና ተአምራት ማድረጉ**

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሦስት ዓመታት ያህል በገሊላ፣ በሰማርያና በይሁዳ እየተመላለሰ ያስተምር ነበር። ይህም በምኩራብ፣ በመቅደስ፣ በቤት ውስጥ እንዲሁም በባሕርዳር፣ በተራራና በሜዳ ላይ ለህዝቡ እየሰበከ ያስተምር ነበር። ሲያስተምርም በምሳሌ እንዲሁም አስገራሚ ተአምራትን በማድረግም ጭምር ነው። የመጀመሪያው ተአምር በገሊላ ቃና በሰርግ ቤት ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ ሲሆን እንጀራ ማበርከት፣ በደረቅ ግንባር ላይ ዓይን መፍጠር፣ በውኃ ላይ መራመድ፣ ነፋስን ፀጥ ማድረግ፣ ከብዙ ሰዎች አጋንንትን ማውጣት፣ ህመማን ሰዎችን ከደዌያቸውና ከበሽታቸው መፈወስ፣ ሙታንን ማስነሳትና የመሳሰሉ በርካታ ተአምራት ያከናውን ነበር። ሉቃ 4÷31፤ ዮሐ 2÷1-11፤ ማቴ 4÷23-25። ከመጀመሪያው ጀምሮ ባሕላቸውንና ወጋቸውን ስላልጠበቀና በሚያደርጉት የግብዝነት ስራ ይወቅሳቸው ስለነበር ፈሪሳውያኑ ተቃውመውት ሊገድሉት ፈለጉ።

- **የመጨረሻ ሳምንቱና መያዙ**

ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ፤ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው። በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት፤ ሆሳዕና በአርያም; በማለት እየጮሁ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ሆኖ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ብዙ ሰዎችን አስከትሎ ገባ። ብዙዎች ልብሳቸውን ሌሎች የዘንባባ ዝንጣፊዎች በመንገድ ላይ እያነጠፉ በእልልታና በዝማሬ ተቀበሉት። ማቴ 21÷1-11፤ ማር 11÷1-10። ኢየሱስ ክርስቶስም ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ። በቤተ መቅደስም የሚነግዱትን ገርፎ አስወጣቸው። በመቅደስም ዕውሮችን አበራ፣ አንካሶችና ድውያንን ፈወሰ፤ በምሴተ ሐሙስም የሐዋርያትን እግር አጠበ፤ ቀጥሎም ቅዱስ ቁርባንን መሰረተ፤ ስለመሄዱና መንፈስ ቅዱስን ስለመስጠቱ ለሐዋርያቱ አስተማራቸው። ከዚያም ወደ ጌቴሰማኒ መጣ። በዚያም እየጸለየ ሳለ የአስቆሮቱ ሰው ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ሊሸጠው ተስማምቶ ነበርና በርካታ ሰዎችን አስከትሎ በመምጣት አሳልፎ ሰጠው። እነርሱም

ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ውሰዱት፡፡ በነጋታው አርብ ጠዋትም ካህናቱ ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት፡፡ እርሱ ግን ይህ ሰው ንፁህ ነው ጥፋት አላገኘሁበትም አላቸው፡፡ እነርሱ ግን ሰይጣን ልባቸውን አደንድኖት ነበርና አይሆንም በደለኛ ነውና ሞት ስለሚገባው ስቀልልን በማለት አብዝተው ጮሁ፡፡ ጲላጦስም የህዝቡን ተቃውሞና ሁከት ስለፈራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሞት አሳልፎ ሰጠው፡፡

- **ሞቱ**

በሮማውያን ሥርዓት የሚገረፍ አይሰቀልም፤ የሚሰቀልም አይገረፍም፡፡ ነገር ግን ጌታችንን 6,666 ጅራፍ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪታይ ድረስ ገረፉት፤ መስቀሉንም አሸክመው ወደ ቀራንዮ እያንገላቱና እየመቱ ወሰዱት፡፡ የቀሬናው ሰው ስምዖንም በመንገድ ያልፍ ነበርና የጌታን መስቀል አሸከሙት፡፡ ቀራንዮ እንደደረሱም የጌታን ልብስ አውልቀው የሾህ አክሊል ደፍተው በሁለት ወንበዴዎች መሐል ሰቀሉት፡፡ ተጠማሁ ባለ ጊዜ ምድርን በውኃ ላይ ላፀና ጌታ ሆምጣጤ አመጡለት፡፡ ጎኑንም በጦር ወጉት፤ ከመስቀሉ ራስ ላይም #የአይሁዱ ንጉስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ; የሚል ጽሑፍ ለጠፉበት፡፡ በልብሱም ላይ እጣ ተጣጣሉበት፡፡ ካህናቱ ጭፍሮቹም ሳይቀሩ አብሮት የተሰቀለውም ጭምር ይሰድበው ይዘብትበት ነበር፡፡ ጌታም በመስቀል ላይ ሆኖ ሰባት ቃላትን ተናገረ፡፡ ዘጠኝ ሰዓትም በሆነ ጊዜ ነፍሱን በገዛ እጁ ለሞት አሳልፎ ሰጠ፡፡ በዚህም ጊዜ በምድር ላይ መናወጥና የተለያዩ ተአምራት ተከናወነ፡፡ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን የአርማትያስ ሰው ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ወስደው በአዲስ መቃብር ቀበሩት፡፡ 1ጴጥ 3÷19

- **ትንሣኤው**

ኢየሱስ ክርስቶስም አስቀድሞ እንደተናገረው ከሞተ በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ፡፡ እዚህ ላይ አርብ ተሰቅሎ ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ከተነሣ እንዴት ብሎ ሦስት መዓልት (ቀን) እና ሌሊት ይሞላል ሊያሰኝ ይችላል፡፡ ለዚህ ምላሽ የዕብራውያንን የቀን አቆጣጠር ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በዕብራውያን አንድ ሙሉ ቀን መቆጠር የሚጀምረው የማታውን ስዐ ነው፡፡ በመሆኑም ጌታችን ከተሰቀለበት ዕለተ አርብ ጀምረን እስከ ትንሳኤው ያለውን ማታና ቀን ስንቆጥር አርብ መዓልት የሐሙሱን ሌሊት ስዐ አንድ ቀን ሲያስቆጥርልን የቅዳሜው ቀን የአርቡን ሌሊት ስዐ ሁለተኛውን ቀን እንዲሁም የቅዳሜው ሌሊት የእሁዱን ቀን ስዐ ሦስተኛውን ቀን ያስገኙልናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በትርጓሜ የሚፈቱ አቆጣጠሮችንም አክለን በአጠቃላይ ጌታችን ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር ቆየ እንላለን፡፡

ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኃላ በመጀመሪያ ለመቅደላዊት ማርያም በኃላም ለደቀመዛሙርቱ ተገለጠላቸው፤ አርባ ቀናትም እየታየ አስተማራቸው፡፡ በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ወንጌልን በዓለም ሁሉ እንዲሰብኩ አዘዛቸው፡፡ ተመልሶም ለፍርድ እንደሚመጣ ከነገራቸው በኃላ እጆቹን ጭኖ ባረካቸው፡፡ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው፡፡ ሰማያት ለእርሱ ተከፈቱ፡፡ በመለኮቱ ከዙፋኑ ተለይቶ ያለነበረ እርሱ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ሆኖ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጌትነቱ ዙፋን ተቀመጠ፡፡ በእውነት አይቀርም በኃለኛው ዘመን እንዲሁ ለፍርድ ተመልሶ ይመጣል፡፡ ማቴ 28÷18፤ ሉቃ 24÷25፤ የሐዋ 1÷1-11፤ ኤፌ 1÷19-23፤ ዕብ 7÷23-25፤ ዮሐ 2÷1፤ 1ቆሮ 15÷23-28፡፡

3.3 የሐዋርያት ጉዞ / ዘመነ ሐዋርያት / ከ34 ዓ.ም - 70 ዓ.ም /

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖርስ ከተጠመቀ በኃላ የማስተማር ስራውን ሲጀምር አስቀድሞ ያደረገው ነገር ቃሉን ተምረውና ተዓምራቱን በዓይናቸው ተመልክተው ዓለምን የሚሰብኩ ደቀመዛሙርቱን መምረጥ ነበር፡፡ •እነዚህ ደቀ መዛሙርትም ሐዋርያት

ተብለው ይጠራሉ፡፡ ሐዋርያት የተጠሩት በዓይናቸው ያዩትን በጆሮዋቸው የሰሙትን ወንጌል ለዓለም እንዲመሰክሩ ነው:: (1ኛ ዮሐ 1፥1) ከጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኃላ ያለው ዘመን ሐዋርያቱ ወንጌልን በተማሩት መሠረት ያስፋፉበት ስለሆነ በሐዋርያቱ ስም ዘመነ ሐዋርያት ይባላል፡፡ ዘመነ ሐዋርያት እስከ 70 ዓ.ም የዘለቀና ጥጦስ ኢየሩሳሌምን ባጠፋ ጊዜ የተጠናቀቀ ዘመን ነው፡፡

- 3.3.1 በዓለ ጰራቅሊጦስ

አማናዊ ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው ግንቦት 18 ቀን 33 ዓ.ም እንደሆነ ተጽፏል፡፡ ጊዜውም በበዓለ ሃምሳ ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ የበዓለ ሃምሳን በዓል ለማክበር ቤተ እግዚአብሔርን ለመሳለም በመጡት አይሁድ መካከል፣ በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ተቀምጠው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለመልበስ በተስፋ ይጠብቁ ለነበሩት ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ኃይልን ሰጣቸው፡፡ የሐዋ 2÷1-5፡፡ ከዚህ በኃላ ሐዋርያት በየሃገሩ ቋንቋ ይናገሩ ጀመር፡፡ በዚህ ቀን በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ብቻ ሦስት ሺህ ሰዎች አምነው ተጠምቀዋል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ሦስት ጥቅሞችን አስገኝቷል፡፡ እነዚህም ፡-

1. ለሐዋርያት ድፍረትንና መታደስን /ኃይል መንፈሳዊን/ ሰጠ፡፡
2. በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ሦስት ሺህ ሰዎች አምነው ተጠምቀዋል፡፡
3. ያመነው ሕዝብ በየሄደበት ሁሉ ወንጌል ለመስበክ ለማስተማር ለመመስከር በቃ፡፡ የሐዋ 2÷37-41፡፡

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኃላ ጌታውን አሳልፎ በሰጠው በይሁዳ ምትክ ሐዋርያ ለመሾም ማትያስንና ዮሴፍን መርጠው እንዲህ ብለው ጸለዩ፡፡ #የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ሥፍራ ይሔድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ሥፍራን እንዲቀበል የመረጥከውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው;፡፡ ዕጣም ተጣጣሉባቸው፡፡ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአስራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ፡፡ የሐዋ 1÷21-26፡፡

ሐዋርያት በኃይለ መንፈስ ቅዱስ እየበረቱ ስብከታቸውን በማስፋፋታቸው ማኅበረ እስጢፋኖስ ተመሰረተ፡፡ ቅንዓት ሰይጣናዊ ያነሣሣቸው አይሁድ ግን እስጢፋኖስን በመግደል ማኅበረ እስጢፋኖስን አፈረሱ፤ ሐዋርያትን አሠሩ፤ ማኅበረ እስጢፋኖስም በየሃገሩ ተበታትነው ቤተ ክርስቲያንን አስፋፉ፡፡ የሐዋ 7÷57-68፤ 8÷1-17፡፡ ከ33-34ዓ.ም ባለው ወቅት ከተከሰቱ አስደናቂ ነገሮች የሚቆጠረው ቤተክርስቲያንን ያሳድድ የነበረው ሳውል ወደ ክርስትና እምነት ተመልሶ ጠንካራ ሐዋርያ መሆኑና በጠንካራው ስብከት ቤተክርስቲያንን መገንባቱ ነው፡፡ የሐዋ 9÷1-31፡

- 3.3.2. የሐዋርያት አመራረጥ ታሪክ ፣ ገድልና ክብር

1. ቅዱስ ጴጥሮስ

ጴጥሮስ ማለት ዐለት (መሠረት) ማለት ነው፡፡ በግሪክ ጴጥሮስ በአረማይክ “ኬፋ” በዐረብኛ “አለሀየር” ይባላል፡፡ የመጀመሪያ ስሙ “ስምዖን” ሲሆን “ስምዐኒ እግዚአብሔር” ማለት ነው፡፡ የተወለደው በገሊላ ባሕር ዳር በቤተሳይዳ ሲሆን በአባቱ በዮና የሮቤል በእናቱ የስምዖን ነገድ ነው፡፡ ሚስቱም ኮንኮርድያ (ጴርጴጥዋ) ትባላለች፡፡ በስምንተኛው ወደ ግዝረት ቤት አግብተው ስሙን በእናቱ ነገድ ስም ስምዖን ብለው ሠየሙት፡፡ (ማቴ. 16፥17-18፣ ዮሐ. 21፥16፣ ማር. 8፥29፣ ሉቃ. 9፥20) ዕድሜውም 5 ዓመት ሲማለው እንደ አይሁድ ሥርዓት ሕገ ኦሪትን እንዲማር ባደገበት ከተማ በቤተሳይዳ አጠገብ ወደምትገኘው ወደ ቅፍረናሆም ምኩራብ (ት/ቤት) አስገቡት፡፡ በጎልማሳነቱ ከወንድሙ እንድርያስ ጋር **በገሊላ ባሕር** ዓሣ ማስገር ጀመረ፡፡ ለደቀመዛሙርትነትም ሲመረጥ ዕድሜው 55 ዓመት ነበር፡፡ ወደ ጌታችንም ያመጣው ወንድሙ እንድርያስ ነው፡፡ ይኸውም ዓሣ በማጥመድ ላይ ነበር፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ በርናባስና ወንጌላዊ ማርቆስ ቤተ ዘመድ ናቸው፡፡ በማርቆስ አባት አርስጦቡሎስ እና በርባናስ በእናት የሚገናኙ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ያገባው የአርስጦቡሎስን እኅት ስለነበር በጋብቻ ይዛመዳሉ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ከአዕማድ ወይም የምሥጢር ሐዋርያት ከእነ ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ያዕቆብ ጋር የሚቆጠር ነው፡፡ (ገላ. 2፥9) አዕማደ ሐዋርያት የተባሉበት ዐቢይ ምክንያትም፡-

፩. የኢየሩሳሌምን ቤ/ክ በዋናነት ያስተባብሩ ስለነበር፡፡

፪. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡-

- ምሥጢረ መለኮቱን ክብሩን በደብረ ታቦር ሲገልጥ (ማቴ. 17፥1-8፣ ማር. 9፥2)
- ሥርዓተ ጸሎትን በጌቴሴማኒ ባሳየ ጊዜ ወይም በጌቴሴማኒ ሲጸልይ (ማቴ. 26፥36-47፣ ማር. 14፥32-42) ይዟቸው ሄዶ ነበርና፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ ከእነዚህ ተለይቶ ሊቀ ሐዋርያ (ርዕሰ ሐዋርያት፣ የሐዋርያት አለቃ) ይባላል፡፡ምክንያቶቹም

- ጌታ በቂሳርያ ከተማ ለሐዋርያት ያቀረበውን ጥያቄ በመመለሱ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻና በሥልጣነ ክህነት የመፍታትና የማሰር ሥልጣን ስለተሰጠው፡፡ (ማቴ.16፥13-19)
- ‹‹በጎቼን ጠብቅ›› በሚለው የአደራ ቃል መሠረት የ120 ቤተሰብ (ማኅበር) መሪ ነበርና (ዮሐ. 21፥15) ይህም ሥልጣን እስከ ዛሬ ድረስ ለቤ/ክ የምሥጢረ ክህነት መሠረት ሆኖ ያገለግላል፡፡
- ሐዋርያት ከጌታ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ሁሉ በመጀመሪያ የሚናገር ጴጥሮስ ስለነበር፡፡ (ማቴ. 16፥16፣ ማር. 8፥29፣ ሉቃ. 9፥20)፤ (ማቴ. 19፥27፣ ማር. 10፥28፣ ሉቃ. 18፥18)

ቅዱስ ጴጥሮስ በሐዋርት ዘመን

የሐዋርያት ስም ዝርዝር በተመዘገበባቸው በአራቱም ክፍሎች በመጀመሪያ ተመዝግቦ የሚገኘው የጴጥሮስ ስም ነው፡፡ (ማቴ. 10፥2፣ 37 ማር. 3፥16፣ ሉቃ. 6፥14፣ ሐዋ. 1፥13) ቀዳሚውን ሥፍራ ይዞ የተገኘውም፡- በሽምግልና አባትነቱ፣ ጌታ በቂሳርያ በሰጠውቃል ኪዳን፣ የሐዋርያት አፈ ጉባኤ ሆኖ ይናገር ስለነበር፣ በጥብርድያዶስ ባሕር በተሰጠው ቃልኪዳን መሠረት ነው፡፡

በክርስቶስ ፈቃድ በጥብርያዶስ ባሕር ላይ ተራምዷል፡፡ (ማቴ. 14፥22-33)፣ ጌታችን እሞታለው ቢላቸው ቅዱስ ጴጥሮስ አይሁንብህ አይደርብህ ብሎታል፡፡ (ማቴ.16፥21-23)፣ ይኽውም ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ይወድ ነበር፡፡ ፍቅሩ ግን ቅንዓት የተቀላቀለበት በመሆኑ ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ የሞቱን ነገር ቀድሞ ሲነግራቸው አይሁንብህ በማለት ተከራክሯል፡፡ (ማቴ.16፥23) ከክርስቶስ ጋር ለመንግሥት (ለገዢቸው) ግብር ገበረ፡፡ (ማቴ. 17፥24-27)፣ ከዮሐንስ ጋር የፋሲካን ራት አሰናዳ (ሉቃ. 22፥7-13)፣ ጌታችን በአይሁድ እጅ ከተያዘ በኋላ ጌታው አስቀድሞ ‹‹ትክደኛለህ›› ብሎ የነገረው መድረሱንና አምላኩን በመካድ መበደሉን እንዳወቀ ከግቢው ወጥቶ መራራ ለቅሶን ተንሰቅስቆ በማልቀስ በፍጹም ንስሐ ተመለሰ፡፡ (ማቴ. 26፥31-35፣ 69-75፣ ማር. 1427-31፣ 60-72)፣ ጌታችን ‹‹ዛሬ የሰው ልጅ ተላልፎ ይሰጣል›› ብሎ አስተምሯቸው ነበርና መከላከያ ይሆነኛል ብሎ ሠይፍ ደብቆ ይዞ ነበር፡፡ የሮም ጭፍሮችም ጌታችንን ለመያዝ ሲጠጉ የሊቀ ካህናቱን ባርያ (ማልኮስን) በሰይፍ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው፡፡ (ዮሐ. 18፥10-18) ጌታችን ግን ሞቱ በፈቃዱ ለድኅነተ ዓለም ነውና ‹‹ሰይፍህን በሰገባው መልስ›› ሲል ገሰጸው፡፡ በሕጽበተ እግር ጊዜ አልታጠብም ብሎ ኋላ ታጥቧል፡፡ (ዮሐ. 13፥6-11) ጌታ ከሞት የተነሣ ዕለት ከዮሐንስ ጋር ሮጦ ሄዷል፡፡ የጌታንም ሥጋ በመቃብሩ አላገኘም፡፡ (ዮሐ. 20፥2-10)

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በዕድሜው ታላቅነት በሐዋርያት ዘንድ እንደ አባት ይታይ ስለነበር ጌታችን ከተሰቀለ በኋላ ሐዋርያቱን ሊመግብ ወደሚያውቀው ሙያ ዓሣ ማስገሩ ተሰማራ፡፡ ጌታችንም አስቀድሞ የመረጠው እርሱ ነውና ቢክደው እንኳ በንስሐ በመመለሱ ንስሐውን መቀበሉን ዛሬም እንደሚወደው ይገልጽለት ዘንድ ዓሣ በሚያጠምድበት በጥብርያዶስ ባሕር ተገለጠለት ሦስት ጊዜ ክዶት ነበርና ቀኖና ሰጠው፡፡ ‹‹ትወደኛለህን›› ብሎ ሦስት ጊዜ ከጠየቀው በኋላ ግልገሎቼን፣ ጠቦቶቼንና በጎቼን ጠብቅ ብሎ ወጣንያንን፣ ማዕከላዊያንና ፍጹማንን እንዲንከባከብ ኃላፊነት ሰጥቶታል፡፡ (ዮሐ. 21፥15-18) መሠረት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚያም በሞቱ እንዴት አድርጎ እንዴት አድርጎ እግዚአብሔርን እንደሚያከብረው ነግሮት ወደ ሰማያት አረገ፡፡

ከጌታ ዕርገት በኋላ ካደረጋቸው ነገሮች በሐዋርያት ሥራ የተመዘገበ፡-


♣ በኢየሩሳሌም በይሁዳ ፈንታ ማትያስ በተተካ ጊዜ የጉባኤው መሪ ነበር፡፡ ሐዋ. 1÷16-23

- በበዓለ ኀምሳ ለደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ጊዜ ለተሰበሰቡት አይሁድ አፈ ጉባኤ ሆኖ ወንጌልን የሰበከ፤ በአንዲት ዕለት ሦስት ሺ ምዕመናንንም አሳምኖ የመጀመሪያው ን አጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የመሠረተ እርሱ ነው። (ሐዋ. 2፥14-37)
- በመቅደስ ከዮሐንስ ጋር የ፴ ዓመት ሽባ በክርስቶስ ስም ፈውሶ ባደረገው ስብከት 5 ሺ ሰው አሳመነ። (ሐዋ. 3፥1-4፣ 22)
- በቃሉ ሐናንያና ሰጲራ ሞተዋል። (ሐዋ. 5፥1-11)፤ የታመሙ ሁሉ በጥላው የፈወሱ ነበር። (ሐዋ.5፥15)
- በሰማርያ ሲስተምር ሲሞን የሚባል መሠርይን አጠፋው። (ሐዋ. 8፥9-24)
- በልዳ ከ8 ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የተባለውን ሰው በክርስቶስ ስም ፈወሶ ብዙዎችን አሳመነ። (ሐዋ. 9፥32-35)፤ ጣቢታን (ዶርቃን) ከሞት አስነሣና ብዙዎችን አሳመነ። (ሐዋ. 9፥36-43)
- በ50 ዓ.ም አካባቢ በኢየሩሳሌም በተደረገው የሐዋርያት ሲኖዶስ ከአንጾኪያ ክርስቲያኖች ለቀረበው ጥያቄ የመጀመሪያውን መልስ የሰጠው እርሱ ነው።
- ኢጣሊቃ ለተባለ የሮም ጭፍራ መቶ አለቃ የነበረ በኅዳር 22 ቆርኔሌዎስን በራዕይ ታዞ ከነቤተሰቡ አጠመቀው ብዙ ድዊያንንም ፈወሰ። (ሐዋ. 10፥1-48)
- በንጉሥ ሄሮድስ እጅግሩን በሰንሰለት አስሮ በእስር ቤት ከቶ በአራት ጭፍራ እያስጠበቀው በምዕመናን ጸሎት የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል በሚያዚያ 12 ቀን በሩ ሳይከፈት ሰንሰለቱን በጥሶ ከወኅኒ ቤት አውጥቶታል። ቅዱስ ጴጥሮስም ‹‹ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስና ከአይሁድ እጅ እንዳዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ›› አለ። (ሐዋ. 12፥1-17)

ቅዱስ ጴጥሮስ በማናቸውም ነገር ፈጣንና ቀልጣፋ ነበር። በቤተ ክርስያን ታሪክ መሠረት ቅዱስ ጴጥሮስ በፍልስጤም፣ በሶሪያ፣ በጳንጦን፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያ፣ በቢታንያና በሮሜ ወንጌል ሰብኳል። ቅዱስ ጴጥሮስ በሮሜ አንድ ዓመት ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ካስተማረ በኋላ የሮሜ ክርስቲኖች እየበዙ ከመምጣ ታቸውም በላይ የክርስትናው ጉዞ እስከ ሮማ ባለሥልጣናት ደረሰ።

ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር የሃያውን ቀን መንገድ በአንድ ቀን ተጉዘው በአንጾኪያ ሲያስተምሩ የከተማው ነዋሪዎችና የጣዖታቱ አገልጋዮች ደብድበው፣ አጎሳቁለውና ግማሽ ራሳቸውን ላጭተው ተዘባበቱባቸው። አሥረውም ከግንቡ ውጭ አስወጥተው ጣሏቸውና ሲጸልዩ ጌታችን ተገልጦ ‹‹በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ፣አትዘኑ መላጨታችሁና መናቃችሁ መመኪያ ክብርን፣ የክህነት ሥርዓትና ምልክትን ይሆናላችኋልና›› አላቸው። በኋላም በቅዱስ ጳውሎስ አጋዥነት ዕውር ካበሩና ሙት ካስነሡ በኋላ ብዙ መካንትና አሕዛብን አሳምነዋል። ቅዱስ ጴጥሮስ መምህረ አይሁድ (መምህረ ሕግ) በመባል ሲታወቅ ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ መምህረ አሕዛብ በመባል ይታወቃል። **‹‹ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደተሰጠው፤ እንዲሁ ለኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደተሰጠኝ አዩ፤ ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቷልና። ...እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱ ወደተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናበስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን›› እንዲል።** (ገላ. 2፥7-9፣ ሐዋ. 13፥2-3) ***ዕረፍቱ***

ጌታ በዮሐ. 21፥18-19 በተናገረው መሠረት በኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግሥት በሮማ ከተማ ቁልቁል ተሰቅሎ በሐምሌ 5 ቀን 67 ዓ.ም በሰማዕትነት ያረፈ ታላቅ ሐዋርያ ነው። ሥጋውን ደቀ መዝሙሩ መርቁሎስ ከመስቀሉ አውርዶ በወተት ወይን አጥቦ ሽቶ ቀብቶ በነጭ ሐር ገንዞ እንዳይፈርስ በማር በተመላ ሳጥን አድርጎ ቀብሮታል። በስመ የሚጠሩ ሁለት መልእክታት አሉት። በእንደኛው መ/ክ/ዘ የነበረው የቤ/ክ ታሪክ ጸሐፊ ቅዱስ ጴጥሮስ በቫቲካን ኮረብታ ጳውሎስ ደግሞ በሮም በኦስትያ መንገድ መቀበራቸውን መስክሯል።



2. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ

ያዕቆብ ማለት “ተረከዝን ይይዛል” ማለት ነው። በዚህ ስም የሚጠሩ ቅዱሳንም ብዙ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሚታወቁት መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክልም፡-

ሀ) ርብቃ ለይስሐቅ ከወለደችለት መንታዎች አንዱና የዐሥራ ኹለቱ ነገደ እሥራኤል አባት ቅዱስ ያዕቆብ /ዘፍ.፳፭፡፳፫/፤

ለ) የዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ታላቅ ወንድም የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ /ማቴ.፬፡፳/፤

ሐ) መልእክት የጻፈውና የጌታ ወንድም እየተባለ የሚጠራው ያዕቆብ ወልደ ቀለዮጳ (ወልደ እልፍዮስ) /ማር.፬፡፫/።

መ) በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ማተብ (ማዕተብ) በአንገት ላይ ማሰርንያስጀመረው የቅዱስ ዲዮስቆሮስ ደቀ መዝሙር ያዕቆብ ዘእልበረዲ ይገኙበታል።

በዚህ ክፍል የምንመለከተው ግን በኹለተኛ ደረጃ ስለገለጽነው ስለ ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስን ነው። ይኽ ሐዋርያ አባቱ ዘብዴዎስ ተብሎ የሚጠራ ዓሣ አጥማጅ ሲኾን እናቱም ማርያም ባውፍልያ እንደምትባልና ከ፸፪ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ እንደነበረች ሊቃውንት ይናገራሉ /ማቴ.፳፯፡፶፮/። ቅዱስ ያዕቆብ የፍቁረ እግዚእ የዮሐንስ ታላቅ ወንድም ሲኾን የመጀመርያ ሥራውም ከአባቱ ጋር ዓሣ ማጥመድን ነበር። አንድ ቀን ግን ይኽን ሥራው በገሊላ ባሕር አጠገብ እየሠራ ሳለ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ሰዎችን ለወንጌል ያጠምድ ዘንድ ጠራው። እርሱም ያለ ምንም ማንገራገር ከታናሽ ወንድሙ ጋር ተከተለው//። በሐዋርያት ዝርዝር ውጥም ከመጀመርያዎቹ የሚጠቀስ ነው/ማቴ.፲፡፪/።

ቅዱስ ያዕቆብ ከአዕማድ (የምሥጢር) ሐዋርያት አንዱ በመኾኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን፣ በቤተ ኢያኢሮስ ተአምራቱን፣ በጌተ ሴማኒም ምሥጢረ ጸሎትን ሲገልጽ አብሮት ነበር። በአራቱም ወንጌላት በተለያየ ቦታ ተጽፎ እንደምንመለከተው ሐዋርያው ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ ወንጌልን የማስተማር ፍላጐታቸውና ሥራቸው ታላቅና ኃይል የተሞላው ነበር። በዚህም ቦኤኔርጌስ (የነጐድጓድ ልጆች) ተብለዋል /ሉቃ.፱፡፶፬/።

የቅዱሱን ዕረፍት በሚያወሳው የሚያዝያ ፲፯ ስንክሳር ምንባብ ላይ ሐዋርያው የ፲፪ ነገድ ቋንቋ ይችል እንደ ነበር ይነግረናል። ከዚህም በተጨማሪ “የእንስሳትና የአራዊት ቋንቋ ይረዳ ነበር” ይላል።

ቅዱስ ያዕቆብና ኹለቱ ጠንቋዮች

ገድለ ሐዋርያት እንደሚነግረን ፊሊጦስ የተባለ ጠንቋይ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት ማመኑን ሄሮሞጌኒስ ለተባለ ጓደኛው ይነግሯል። ሄሮሞጌኒስም የራሱን ታላቅነት ለማሳየት ሲል በአስማት እጁንና እግሩን አሳሰረው። ፊሊጦስም የደረሰበትን ኹሉ በመዘርዘር ለሐዋርያው ያዕቆብ ላከበት። ይኽን የሰማው ሄሮሞጌኒስም ቅዱስ ያዕቆብን አስረው እንዲያመጡለት በአስማት አጋንንትን ላካቸው። የተላኩት አጋንንት ግን በቅዱስ ያዕቆብ ላይ ኃይል ስላልነበራቸው የተላኩበትን ማድረግ ተሳናቸው። እንዲያውም ቅዱስ ያዕቆብ መልሶ ሄሮሞጌኒስን አስረው እንዲያመጡት አዘዛቸው። እነርሱም እጅ እግሩን ጠፍረው ይዘዉት መጡ። ፊሊጦስ ክርስቲያን ሆኗልና ቅዱስ ያዕቆብ ምሕረት እንዳደረገለት (ከእስራቱ እንደፈታው) ለሄሮሞጌኒስም ምሕረትን ለመነለት። ቅዱስ ያዕቆብም "እኛ ክፉን በክፉ ስለማንቃወም በሰይጣናት እየተሰቃየህ እንዳትኖር ከክርስቶስ ምሕረትን እለምንልሃለሁ" በማለት ሄሮሞጌኒስ ከታሰረበት እንዲፈታ አደረገ። አስማተኛው ሄሮሞጌኒስም የክርስቲያኖችን ኃይል፣ ርኅራኄና ቸርነት አይቶ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት አመነ። ወደ ቤቱም ተመልሶ የጥንቆላ መጻሕፍቱንና ዕቃዎቹን ኹሉ ሰብስቦ በማምጣት በቅዱስ ያዕቆብ እግር ሥር አቃጠላቸው።

የቅዱስ ያዕቆብ ሰማዕትነት

ይኽ ሐዋርያ በቅዱሳን ነቢያት ተነግሮ የነበረውን ነገረ ድኅነት ካስተማሩትና እንደ በግ በሰይፍ ከታረዱት ሐዋርያት መካከል አንዱ ነው። በወንጌል እንደምናነበው እናታቸው ማርያም ባውፍልያ ጌታችንን አንድ ጥያቄ ጠይቃው ነበር። ይኸውም ወደ ኢየሩሳሌም ከገባ በኋላ አንዳቸውን ቀኛዝማች አንዳቸው ደግሞ ግራዝማች ብሎ ልጆቿን እንዲሾምላት ነው። ይኽንንም ያለችው ጌታችን ስለ መንግሥቱ በተናገረ ጊዜ ስለ ምድራዊ መንግሥት የተናገረ መስሏት ነው /ማቴ.፳፡፳፩/። ጌታችንም ለያዕቆብና ለዮሐንስ አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው። "እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?" ሲል። እነርሱም ከፍቅራቸው የተነሣ "እንችላለን" አሉት። ጌታችንም ""እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃላችሁ" በማለት በግራና በቀኝ መሰቀል ትንቢት ለተነገረላቸው ለፈያታዊ ዘየማንና ለፈያታዊ ዘጸጋም መኾኑን ገልጾ እነርሱም ኋላ ላይ መከራ መስቀሉን እንደሚካፈሉ ነገራቸው /ማር.፲፡፴፰-፴፱/።

ይኸው የጌታችን ትንቢትም በ፴፬ ዓ.ም ሚያዝያ ፲፯ ቀን በያዕቆብ ላይ ተፈጸመ /ሐዋ.፲፪፡፩-፪/። ከታሪክ እንደምንረዳው በዚህ ጊዜ የነበረው "የሥልጣኔ" ዓይነት ሄሌኒዝም ይባላል። ይኸውም የጥንቱን የግሪክ ፍልስፍና ከምሥራቃውያኑን ሕዝቦች የባሕል ቅይጥ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የነበረው ንጉሥም ሄሮድስ አግሪጳ ይባላል። አርኬላውስና /ማቴ.፪፡፳፪/ የመጥምቁ ዮሐንስን አንገት የቆረጠው ሄሮድስ አንጢጳስ /ማቴ.፲፬፡፩-፲፪/ የዚኹ ሄሮድስ አጐቶች ናቸው። ዘፋኟ ሄሮድያዳ ደግሞ እኅቱ ነች።

እውቁ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ ከቀሌሜንጦስ ዘእስክንድርያ ጠቅሶ እንደጻፈው "አንድ አይሁዳዊ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት ስለተናደደ በነገር ከስሶ ለአይሁድ ሸንጎ አቀረበው። በሸንጐው ከመቅረባቸው በፊት በጉዞ ላይ እንዳሉ ግን ከሳሹ አይሁዳዊ ቅዱስ ያዕቆብ ለሃይማኖቱ ያለውን ፍቅርና ቆራጥነት አይቶ ሐዋርያዉን በመክሰሱ ተጸጸተ፤ በሐዋርያው ትምህርት ተማርኮም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አመነ። ይቅርታ እንዲያደርግለትም ቅዱሱን ለመነው። ትንሽ ቆይቶም ቅዱስ ያዕቆብ ይቅርታ አድርጐለት በፍቅር ሳመው። በሸንጐው ፊት ከቀረቡ በኋም ቅዱስ ያዕቆብ ያለ ፍርሐትና ያለ ሐፍረት ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሰከረ። በዚህ የተበሳጨ ሄሮድስ አግሪጳም ቅዱስ ያዕቆብንና ከሳሹ አይሁዳዊውን (በኋላ ተጸጽጾ ክርስቲያን የሆነውን) በአንድ ጊዜ በሰይፍ አስገዳለቸው።"

“እንደውም” ይላል አውሳብዮስ ሲቀጥል “እንደውም አይሁድ በዚህ (በቅዱስ ያዕቆብ ዕረፍት) ደስ እንዳላቸው በተመለከተ ጊዜ ሄሮድስ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስንም ወደ በወኅኒ አሳስሮት ነበር። እግዚአብሔር በሌሊት መልአኩን ልኮ ሰንሰለቱን ፈትቶ ለወንጌል አገልግሎት ባያድነው ኖሮ ሊገድለውም ይችል ነበር” በማለት ያኔ የነበረውን ሁናቴ በስፋት ይገልጣል /ሐዋ.፲፪፡፩-፲፩፣ Eusebius, Church History, Book II, Chap.9:2-3/።

አበው እንደሚያስተምሩት ሐዋርያው ያዕቆብ በዕድሜ ገፍቶ ስለነበር እንደሌሎች ሐዋርያት ብዙ አልተዘዋወረም። ከ፲፯ኛ መ/ክ/ዘ ወዲህ ግን በሰማዕትነት ከማረፉ በፊት በስፔን እንደሰበከ የሚናገሩ አንዳንድ መዛግብት አሉ። በዚህች ሀገር ፯ ልዑካንን ሾሞ ሲመለስ በኢየሩሳሌም በሰማዕትነት እንዳረፈ የስፔን ሊቃውንት ይናገራሉ። እንዲያውም በመካከለኛው ዘመን ዐፅሙን ከኢየሩሳሌም አፍልሰው በስፔን ሳንቲያጎ ዲ ኮምፐስተላ ያሳረፉት መኾናቸውን እየመሰከሩ ያረፈበትን ቦታ ያሳያሉ።

3. ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ

ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሲሆን /ማቴ.፲፡፫/ የስሙም ትርጓሜ “የተሎ ሜዎስ ልጅ” ማለት ነው። የትውልድ ሐረጉ ከነገደ ንፍታሌም ነው።

ሐዋርያት ዓለምን ዞረው ያስተምሩ ዘንድ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጣቸው ትእዛዘ መሠረት ለቅዱስ በርተሎሜዎስ በዕጣ የደረሰችው አልዋሕ የምትባል ሀገር ነበረች። ይህችም ሀገር በአርመን የምትገኝ ናት። ይህ ቅዱስ ሀገሩን ስለማያውቀው (ስንክሳሩ የሀገሩን ቋንቋ ስለማያውቅ ይላል) ቅዱስ ጴጥሮስን ውሰደኝ አለው። ቅዱስ ጴጥሮስም ቅዱስ በርተሎሜዎስን ለማድረስ ተዘጋጀ። ወደዚያች ከተማ ለመሄድም ሰዎችን መጠየቅ ጀመሩ። በጉዞአቸውም በአሥር ግመል የሚነግድ ነጋዴን አገኙ። ሐዋርያው ጴጥሮስም ወደ ነጋዴው ቀረበና ሰላምታ ሰጥቶት ወዴት እንደሚሄድ ጠየቀው። ነጋዴውም አልዋሕ እንደሚሄድ ይነግሯል። ሁለቱም ሐዋርያትም ወደዚያች ሀገር መሄድ እንደሚፈልጉ ነግረውት እንዲያደርሳቸው ጠየቁት። ነጋዴውም፡- የምትሸጡትና የምትለውጡት ነገር ምን ሳይኖራችሁ እንዴት ወደዚያች ሀገር ለመሄድ አሰባችሁ? ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም “እኛ የምንሸጠውና የምንለውጠው ነገር የለንም። ነገር ግን የዓለመ ቤዛ ከሆነው ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች ሐዋርያት የምንቁጠር ነን። የተጣለብንም አደራ በዓለም ዙርያ ዞረን፣ ሕገ ወንጌልን ሰብከን አሕዛብን ከኃጢአት ጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን፣ ከፍጹም ክሕደት ወደ ፍጹም እምነት፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከማይጠቅም ትዕቢት ወደሚጠቅም ትሕትና በመመለስ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትና የአማናዊት ሕገ ወንጌል ታዛዦች ማድረግ ነው። በደዌ ዘሥጋ የተያዙትን በተአምራት፣ በደዌ ዘነፍስ የተያዙትንም በትምህርት እንድንፈውስ ሀብተ ፈውስ ተሰጥቶናል። ስለዚህ ሥራችን ከእርሱ ለራቁትና ለተበተኑት ተስፋም ለቆረጡት ተስፋ መስቀልን ሰጥተን፣ ለሥጋም ለነፍስም የሚሆን ሕገ ወንጌልን አስተምረን፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቀን፣ የሥላሴ የጸጋ ልጅነት ካሰጠን በኋላ የመንግሥቱ ወራሾች የስሙ ቀዳሾች እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው” አሉት። ያም ነጋዴ “በስብከታችሁ ሰዎችን እንደምታስቱ ሰምተናል። ሚስትን ከባሏ የምትለያዩ ናችሁ ይባላል። ይህን ትምህርት በዚያች ሀገር ካስተማራችሁ ደግሞ ሚስቴ በእናንተ ስብከት ተመርታ ጥላኝ እንደምትሄድ ነው። ስለዚህ ወግዱ፤ ተመለሱ፤ ከሀገሬም እንዳትገቡ” ብሎ እምቢ አላቸውና ትታቸው ሄደ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱም ሐዋርያት ሌላ ነጋዴ ሲመጣ ጠብቀው በሌላ ዘዴ እንደምን ወደ ሀገሪቱ እንደሚገቡ፣ ይህንንም መሰናክል እንደምን እንደሚያልፉት ተመካከሩ። አንድ ነጋዴም ሲመጣ አገኙና ቅዱስ ጴጥሮስ፡- “ይህንን ባርያዬ አልዋሕ በምትባል ሀገር ሸጬው እንድመጣ እፈልጋለሁና እባክህ ወደ ሀገርህ ውሰደኝ” ሲል ጠየቀው። ያም ነጋዴ “ለብዙ ጊዜ ከሀገሬ ወጥቼ የምኖር በመሆኔ ለቤቴ አገልጋይ

የሚሆን ሰው አጥቼ እኖር ነበር። ዛሬ አገኘሁ። ለመሆኑ ሙያው ምንድነው" ብሎ ይጠቁል። ቅዱስ ጴጥሮስም ቀለል አድርጎ "ወይን ጠባቂ ነው" አለው። ያም ነጋዴ እጅግ በጣም ብዛት ያለው ወይን ስለነበረው በ፴ እስታቴር በርተሎሜዎስን ገዛው። እስታቴር ማለት የሮሜ መንግሥት የብር ምንዛሬ ሲሆን አንድ እስታቴር ሁለት የኢትዮጵያ ብር ያህል ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ብሩን ከነጋዴው ከተቀበለ በኋላ "አደራ ለሌላ ጌታ እንዳትሸጠው፤ ስቃይና መከራ እንዳታበዛበት" ሲል ነጋዴውን ተናገረው። ነጋዴውም የግመሎቹን ሸክም ሲያስተካክል ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ለበርተሎሜዎስ ሰጠውና "ለድሆች መጽውተው" ብሎት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

ያደረጋቸው ተአምራት

፩) ሐዋርያውና ነጋዴው ረኾቦሙን የበረሃው ጉዞ እንደተያያዙት መንገድ ሳቱ። ፍጹም ውኃና ምግብ ወደሌለበት ሥፍራም ደረሱ። ውኃ ጥሙና ችግሩ ጠናባቸው። ግመሎቹ በረሃብ አለቁ። በዚህ ጊዜ ሐዋርያው በርተሎሜዎስ እንዲህ ሲል ጸለየ፡- "አቤቱ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ሰማይንና ምድርን በውቧም ያሉትን ፈጥረህ የምትገዛ፣ አባቶቻችን በበረሃ ሲሰደዱ አብረህ የምትሰደድ፣ ለቅዱሳንህ ኃይልንና በረከትን የምትሰጥ፣ ከዓለት ላይ ውኃን አፍልቀህ ለወዳጆችህ ሕዝበ እስራኤልን እንደ ሰጠሃቸው፣ እኛም በዚህ ቦታ ረግፈን እንቅር። እነዚህ ግመሎችም ይነሡ። ተአምራትህን በበረታች ክንድህ አሳይና ይመኑብህ።" ይሽኔ በምድር ረግፈው የነበሩት ግመሎች ተነሡ። ብርታቱንም አግኝተው እንደተጫኑ የአልዋሕን መንገድ አግኝተው በሰላም ደረሱ።

፪) ሐዋርያው በርተሎሜዎስ በሀገሩ ገብቶ ሲመላለስ አንድ ዐይነ ስዉር መጥቶ "አድነኝ" ብሎ ጮኸበት። ነጋዴውም "የክርስቶስ ባርያ መሆንህን ሳለውቅ ገዛሁህ፤ ወደ ሀገሬም አስገባሁህ" አለው። በርተሎሜዎስም "የክርስቶስ ባርያ መሆኔን መግለጽ አልፈለግሁም" አለው። ዐይነ ስዉሩንም "እንድትናገር ያዘዘህ ብርሃን ይስጥህ" አለው። ዐይነ ስውሩም ብርሃኑን አገኘ።

፫) ነጋዴውም በርተሎሜዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ ሾመው። በርተሎሜዎስ ቀን ቀን ወይኑን እያስጠበቀ፣ እየኮተኮተና እየተከለ ሌሊት ሌሊትም ወደ ከተማ እየሄደ ወንጌልን እየሰበከ ለ፸ ቀናት ያህል ቆየ። ነገር ግን ያመነ ሰው አልነበረምና አብዝቶ ያለቅስ ነበር። አንድ ቀንም ፫ የወይን ግንዶችን ቆርጦ በሌላ ዛፍ ላይ ቢሰቅለው ወዲያውኑ ለምልሞ፣ አብቦ ፍሬ አፈራ። የወይኑ ባለቤትም ይህን ተአምር ለማየት መጣ። "አንተ በዚህች ምድር ላይ ለሰው ልጆች የተገለጥክ አምላክ ነህን?" ብሎ ጠየቀው። እርሱ ግን "እኔ የአምላክ ባርያ እንጂ አምላክ አይደለሁም" ብሎ መለሰለት። በዚያ የነበሩ ሰዎችም አመኑ።

፬) ሐዋርያው በዚህ ብቻ አልተወሰነም። በሌላም ቀን የወይኑ ባለቤት ወይኑን ሊጎበኝ ሲመጣ እባብ ከጉድጓድ ወጥቶ ነደፈው። መርዙም ተሰራጭቶ ገደለው። ወዳጅ ዘመዶቹም ለለቅሶና ለቀብር ተሰባሰቡ። በርተሎሜዎስ ግን ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር። አሽከሮቹም፡- አንተ ጨካኝ! ጌታህ ሲሞት እንደ ማልቀስ አፍጠህ ታያለህን? እያሉ ጮኹበት። በርተሎሜዎስ ግን ጸሎቱ እስከሚፈጽም ድረስ ታገሣቸውና ያን ባለጸጋ ከእንቅልፍ እንደሚነቃ አፈፍ ብሎ እንዲነሣ አደረገው። ያም ባለጸጋ ለዚህ ያበቃው በርተሎሜዎስ መሆኑን መሰከረ። ከዚህም የተነሣ በጉዞ ላይ እያሉ ጀምሮ ብዙ ተአምራትን ያየው ባለጸጋና የሰበሰበው ሕዝብ ባደረገው ተአምራት ተደነቁ፤ እምነታቸውም ጸና። በእግሩ ስር ወድቀውም በአክብሮት ሰገዱለት። "በምድር ላይ ይህን ታላላቅ ተአምራት የምትሠራ ከከአማልክት ውስጥ አንተ ማን ነህ? ምን እንድናደርግልህስ ትወዳለህ?" በማለትም ጠየቁት። ሐዋርያው ግን፡- "እናንተ እንደምታስቡት በስሕተትም እንደምታመልክዋቸው ጣዖታት ሳልሆን የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ነኝ። እርሱም የሰማይና የምድሩ ጌታ፣ የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ፣ ሰው ሆኖም በከበረ ደሙ ፈሳሽነት የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሠርይ፣ የሰይጣንን ተንኰል በረቀቀ ጥበቡ ድል ያደረገና የዓለሙ

ሁሉ ቤዛ የሚሆን ፈጣሪን አምናለሁ። በስሙም ሙታንን እናነሣለን፤ ጠላቶቻችንም እናሳፍራቸዋለን” በማለት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምልቶና አስፍቶ አስተማራቸው። ሕዝቡም “ከአምላክ በርተሎሜዎስ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም” አሉ። ከአምልኮተ ጣዖት ተላቅቀውም የሥላሴ የጸጋ ልጅነትን በጥምቀት ተቀበሉ። ከሞት የተነሣውም ባለጸጋ “ምን ላድርግ” ብሎ ሲጠይቀው ቤተ ክርስቲያንን እንዲያንጽ አዘዘው። ቤተ ክርስቲያንን አሠርቶ ሲጨርስም በቅስና ማዕረግ ሾመው፤ ሌሎችንም ዲያቆናትንና አገልጋዮችን አድርጎ ሾመላቸው።

ከዚህ በኋላ ትምህርቱን በሁሉ ዘንድ እንደተዳረሰ ከተረዳና የወንጌልን ፍሬ ከአፈራ፣ ብዙዎችንም ከደዌአቸው ከፈወሳቸው፣ በእኩያት አጋንንት የተያዙትንም ካነጻ በኋላ ንኢንዶስ ወደተባለች ሀገር እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ አዘዘው። በዚያ ሀገር እንደደረሰም “በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብዑዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። የሚያዝኑ ብዑዓን ናቸው፥ መፅና ናትን ያገኛሉና። የዋሆች ብዑዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብዑዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና። የሚምሩ ብዑዓን ናቸው፥ይማራሉና። ልበ ንጹሖች ብዑዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና። የሚያስተራርቁብዑዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብዑዓንናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔምምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብዑዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያትታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትንእንዲሁ አሳድደዋቸዋልና” እያለ አብራርቶ አንቀጸ ብፁዓንን አስተማራቸው /ማቴ.፭፡፩-፲፪/። እግዚአብሔርም የሰዎቹን ልቦና ከፈተላቸው። በመንፈሳዊ ጥበብም በለጸጉ፤ በንስሐም ወደ ፈጣሪአቸው ተመለሱ፤ ወደ ሕገ ወንጌል ፍጹም ተመለሱ፤ ቅዱሱንም ሐዋርያ አከበሩት።

ከዚህ በኋላ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ባርቤርያን ሀገር ባርበር ወደምትባል ከተማ እንዲሄድ አመለከተው። ቅዱስ እንድርያስንም እንዲረዳው ወደ እርሱ ላከለት። ሕዝቡም በባዕድ አምልኮ የተጠመዱ ስለነበር ባይቀበሏቸውም እግዚአብሔር ከመካከላቸው አንዱን ሰው የሐዋርያትን ትምህርት እንዲቀበልና ያዘዙትን ሁሉ እንዲያደርግ አዘዘው። ስሙም ካኒበልስ ይባል ነበር።

ወደ ከተማውም አብረው በሄዱ ጊዜ የከተማው ሕዝብ ሐዋርያቱን እንዲበልዋቸው አውሬዎቹን ላኩባቸው። ከኒባልስ ግን አውሬዎቹን ሁሉ መግደሉንና ማጥፋቱን በተመለከቱ ጊዜ በከተማው ካለው ሕዝብ አብዛኛውን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አመኑ። ከመካከላቸውም ካህናትን መርጠው ቤተ ክርስቲያንን አሠሩ።

ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ቦታ ተዘዋውሮ ወንጌል ማስተማሩን ሩፊኖስና ሶቅራጠስ የተባሉ የታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም በኢትዮጵያ ወንጌልን ካስተማሩ ሐዋርያት መካከል አንዱ መሆኑንና ሕዝቡን ያጠመቀባቸው ወንዞች እስከ ዛሬ ድረስ ብረትና ሎሚ (ውኃ) እየተባሉ እንደሚጠሩ ይናገራሉ።

የመጨረሻ ዕረፍቱ

በመጨረሻም ሐዋርያው ጊስሚፌንና ጊኤንዶስ ወደተባሉ ሀገራት አመራ። እነዚህን ሀገሮች የሚገዛው የንጉሥ አግሪጳ ሚስት እንኳን እስክትለወጥ ድረስ ብዙዎችን ክርስቲያን እንዲሆኑ አደረገ። ንጉሡም በርተሎሜዎስ ተጠርቶ እንዲመጣ አደረገ። “በርተሎሜዎስ የምትባል መሰርይ አንተ ነህን?” ሲልም ጠየቀው። ሐዋርያው ግን “በክርስቶስ ኢየሱስ ስም የሚሠራ ስራይ የለም፤ የረከሰውንና የሰይጣን ሥራ የሆነው ስራይ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሻራል፤ ይደመሰሳል እንጂ” ሲል መለሰለት። የበርተሎሜዎስ ንግግር ጥብአትና ድፍረት የተሞላ ነበር። የዚህን ጊዜ ንጉሡ በርተሎሜዎስን እንዲያርቁት አዘዘ። ራቀም። ነገር ግን በርተሎሜዎስ እየጸለየ ሳለ አንድ ቀኝ ዐይኑ የታወረና ከተወለደ

ጀምሮ ሁለቱ እግሮቹ ሽባ የሆነ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ እንዲፈውሰው ለመነው። መፃጉዕንም ሕዝቡ በተሰበሰበበት ፈወሰው። ይህን አምላካዊ ተአምር ያዩትም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አመኑ። ንጉሡም የሕዝቡ መለወጥ፣ የአምልኮ ጣዖታቱ መቅረት፣ ሕዝቡም ከእርሱ ይልቅ ለሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ቃል መታዘዙን ተመልክቶ በእጅጉ ተናደደ። እንዲገደልም አዘዘ። መኳንንቱና መሳፍንቱ ግን በጣም አዘኑ። ይባረር እንጂ አይገደል ሲሉም ለንጉሡ ነገሩት። እርሱ ግን አባባላቸውን አቃለለ። መኳንንቱና መሳፍንቱም አንዳች የተቃውሞ ቃል ለመናገር ፈሩ። በርተሎሜዎስ ሌት ተቀን እየተሯሯጠ ወንጌል እየሰበከ ነው። ዋና ትምህርቱም "በመስቀሉ ዓለሙን ያዳነውን ክርስቶስን እመኑ" የሚል ነበር። ንጉሡ ግን የሞት ፍርድ ፈረደበትና ታማኝ ወታደሮቹን ጠርቶ መስከረም ፩ ቀን አሸዋ በተሞላ ከረጢት ውስጥ ከትተው ከነሕይወቱ ባሕር ውስጥ እንዲወረወሩት አዘዘ። ብጹዕ የሚሆን በርተሎሜዎስም በዚያ በሰማዕትነት ዐረፈ። በነጋታውም ምዕመናን ከባሕር አውጥተው በክብር ቀበሩት።

4. ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ቅዱስ ማቴዎስ ነው። እርሱም ቀራጭ ነበር። ለሐዋርያነት ከመመረጡ በፊት የመጠሪያ ስሙ ማቴዎስ ሳይሆን ‹‹ሌዊ›› ተብሎ ይጠራ ነበር። ይኸውም ወንጌላዊ ማርቆስ ስለማቴዎስ ጥንታዊ ስም ሲገልጽ ‹‹በባሕር አጠገብ ሲያልፍ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮስ ልጅ ሌዊን አየና ተከተለኝ አለው›› በማለት ‹‹ሌዊ›› በሚል ስም መጠራቱንና የአባቱም ስም እልፍዮስ መሆኑን ጨምሮ ጽፎ ይገኛል። ማር 2፡14።

ይህ ብቻ አይደለም ወንጌላዊው ሉቃስም በበኩሉ ስለ ማቴዎስ የመጀመሪያ ስም ሲጽፍ ‹‹ሌዊ የሚባል ቀራጭ በመቀመጫው ተቀምጦ ተመለከተና ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት›› ሲል ስሙንና ስራውን አስፋፍቶ ገልጾአል። ሉቃስ 5፡2 እንግዲህ ያዕቆብ ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጆች፤ ጴጥሮስና እንድርያስም የዮና ልጆች እንደሆኑ ሁሉ ማርቆስ ሌዊ፣ ወልደ እልፍዮስ ያለውን ይዘው ማቴዎስ የያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ወንድም መሆኑን የሚገምቱ አሉ። ማቴዎስ ለሐዋርያነት የተጠራው በዚህ ዓይነት ሲሆን፣ ኋላ ቅዱሳን ሐዋርያት ይህንን ዓለም ወንጌል ለማስተማር በዕጣ ተከፋፍለው በሚሄዱበት ጊዜ ምድረ ፍልስጥኤም ለቅዱስ ማቴዎስ በዕጣ ደርሳዋለች።

ቅዱስ ማቴዎስ ከዚያ ገብቶ ጌታችን ኢየሱስ ከተጸነሰበት ቀን ጀምሮ ወደ ሰማይ እስካረገበት ድረስ ያስተማረውን ትምህርት ያደረገውን ተአምራት ቢያስተምራቸው የፍልስጥኤም ሕዝብ ሁሉ በሕገ ኦሪት የነበሩ ወደ ሕገ ወንጌል፡ በአምልኮ ጣዖት የነበሩ ደግሞ ጣዖቶቻቸውን እየሰበሩ አብያተ ጣዖቶችንም እየመዘበሩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው ተጠመቁ። ቅዱስ ማቴዎስ በዚህ ሳይወሰን የወንጌል ትምህርት ወደ አልደረሰባቸው አገሮች ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ለምሳሌ፤ ፋርስ ባቢሎን፡ ኢትዮጵያንም እንዳስተማረ በታሪክ ተጽፎ ይገኛል። ቅዱስ ማቴዎስ ሀገረ ይሁዳንና ፍልስጥኤምን እንዳስተማረ አውሳብዮስ የተባለ ሊቅ ጽፏል። ወንጌላዊው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን ማስተማሩን የሚገልጹት እነ አውሳብዮስ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ታሪኮች በብዛት ይገኛሉ። ለምሳሌ በዓረብኛ ቋንቋ ተጽፎ የታተመና ስንክሳር የተሰኘው መጽሐፍ የሚከተለውን ቃል አስፍሮ ይገኛል። ‹‹ወንጌላዊው ማቴዎስ ለማስተማር በታዘዘው መሠረት የወንጌልን ትምህርት በፍልስጥኤም ለሚኖሩ ሕዝብ ካስተማራቸውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሳምኖ በስሙ ካጠመቃቸው በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሄደ ይልና ከኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራት በትግራይ ክፍለ ሃገር ያስተማረ መሆኑን ይገልጻል።››(ገጽ 76)

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 71 ከቁጥር 9-11 ላይ ‹‹የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፡ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ›› ሲል በትንቢቱ እንደተናገረ የተርሴስና የደሴትች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የተባሉት ከፋርስና ከባቢሎን የመጡ መሆናቸው ይነገራል፡፡ እንዲህ ሲል የኢትዮጵያን ስም ጠርቶ መናገሩ ራሱ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩልም ሰብአ ሰገልን ከማቴዎስ በቀር ሌሎች ወንጌላውያን አያነሷቸውም፡፡ ይህም ማቴዎስ የሰብአ ሰገልን ታሪክ፡ ከየት እንደመጡ፡ ወደየት እንደሚሄዱ፡ ምን አይነት ሥራ ሰርተውም ወደ ሃገራቸው እንደተመለሱ በሰፊው መግለጹ እርሱ በነዚህ ሃገራት ማስተማሩን ይገልጻል፡፡

ማቴዎስ የጻፈውን ወንጌል አተኩረን ስንመለከተው ለአይሁድ በአይሁድ እምነት ለነበሩ ሕዝብ የጻፈው ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ጠቅሷቸው የሚገኙት ቃላት ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ናቸው፡፡ ወንጌሉንም የጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን አጻጻፍም በአይሁድ ሕግና ሥርዓት ወይም ወግ መሠረት ነው፡፡ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት አይሁድ ምክንያት ፈላጊዎች መሆናቸውን ስለሚያውቅ ሕጋቸውን ወይም ወጋቸውን ቢያፈርስ /ባይከተል/ ሕጋችንን አፈረሰ ወጋችንን አበላሸ በማለት ወንጌልን አንቀበልም እንዳይሉ ነው፡፡

ቅዱስ ማቴዎስ ብዙ ድንቅ ተዓምራትን ያደርግ ነበር ይህንን ያልወደዱ መኳንንት ለንጉሡ ይከሱታል፡፡ ንጉሡም በማቴዎስ ላይ ምት ፈረደበት፡፡ ጥቅምት አሥራ ሁለት ወን አንገቱን ተሰይፎ ዐረፈ፡፡

5. ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ

ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሲሆን ከሌሎች ሐዋርያት ይልቅ አስቀድሞ የተጠራ ሐዋርያ ነው /ማቴ.፬፡፲፰/፡፡ በዚህም ምክንያት “ፕሮቶክሌቶስ” ይባላል፡፡ የተጠራ ማለት ነው፡፡ የትውልድ ቦታው እንደ ወንድሙ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ሳይዳ ሲኾን ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ዓሣ እያጠመደ በቅፍርናሆም ይኖር ነበር /ዮሐ.፩፡፵፫/፡፡

ሐዋርያ ከመሆኑ በፊት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ለመሸራው የማዘጋጀትና የማስረከብ እንጂ ለራሱ የማድረግ ዓላማ አልነበረውምና “እነሆ የእግዚአብሔር በግ” እያለ ወደ ጌታችን ያመለክታቸው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ቅዱስ እንድርያስ ጌታችንን ያወቀው፡፡ ቅዱስ እንድርያስ መጥምቁ እንዳመለከተው ወደ ጌታችን መጣ፡፡ የምሥራቹንም ተማረ፡፡ ነፍሱ የወደደችውን አገኘ፡፡ ነገር ግን ብቻውን ሐሴት ያደርግ ዘንድ አልወደደም፡፡ መዝሙረኛው ዳዊት “ወንድሞች በጎበረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው” እንዳለ ወንድሙን ይጠራ ዘንድ ተቻኰለ እንጂ፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ጴጥሮስን ለመጀመርያ ጊዜ “መሢሕን አግኝተናል” ብሎ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አስተዋወቀው፡፡ ቅዱስ እንድርያስ ወንድሙን ብቻ ሳይሆን ከግሪክ ሀገር መጥተው የነበሩትን ሰዎች ከፊልጶስ ጋር ወደ ጌታችን አቅርቧል /ዮሐ.፲፪፡፳-፳፪/፡፡ ወንድሙን በመጥራቱ የቤተሰብ ሐዋርያ፤ የግሪክ ሰዎችን ወደ ጌታችን በማቅረቡ ደግሞ የአሕዝብ ወዳጅ ሐዋርያ ይባላል፡፡

ሐዋርያው ስለ ነገረ ምጽአት ጥያቄ ካቀረቡት ደቀ መዛሙርት አንዱ ሲሆን ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸሎት ከሚተጉት ጋር የተቆጠረ ነው /ሐዋ.፩፡፲፬/፡፡

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በተነሣ ጊዜ ለቶማስ አይሁድ የወጉትን ጐኑን ሲያሳየው ለእንድርያስ ደግሞ የእጆቹን ችንካሮች እንዳሳየው “አርአዮ ለቶማስ ግርዘተ ገቦሁ ወለእንድርያስ ቅንዋተ እደዊሁ” በማለት ቅዱስ ያሬድ ገልጾታል፡፡

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው ሐዋርያው ስብከቱን የጀመረው በፍልስጥኤም ነበር፡፡ ስንክሳሩ ልዳ ይላል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የነበረው አውሳብዮስ ከአርጌንስ ጠቅሶ እንደ ገለጠው ቅዱስ

እንድርያስ እስኰነስ በተባለች ሀገር ቅዱስ ወንጌል አስተምሯል። እስኰነስ በጥንት አጠራር በርባሮስ ተብላ የምትጠራ ስትሆን በአሁኑ ዘመን አጠራር ሩስያ ናት። ቀጥሎም በቢታንያ፣ በገላትያ፣ በሩማንያ፣ መቄዶንያ፣ በታናሽ እስያና አካይያ አስተምሯል። ከዚህም በተጨማሪ በገድለ ሐዋርያት ተጽፎ እንደምናገኘው ሐዋርያው በአስካትያ፣ አርጣልያኖስና ሱቅስ በተባሉ የክፉዎች አላውያን ሀገሮች ሳይፈራና ሳያፍር እስከ ሞት ድረስ የወደደውንና ፍቅሩን በገለጸለት "ፈጣሬ ወገባሬ ኵሉ አምላክ" በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስተምሯል። አላውያን ነገሥታትና አሕዛብ በእነርሱ ፍልስፍናና አምልኮተ ጣዖት ውስጥ ነግሦ የሚኖር ሰይጣን ከሚያሳያቸው ከንቱ ዕውቀት ውጪ አዲስ የሕይወት ትምህርትና ተአምራት ማድረጉን ቀጠለ።

"እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ" ተብሎ አጽናኝ መንፈስ ቅዱስንና ከፍርሐት ነጻ የሚያደርገውን ኃይልና ጸጋ የተገናጸፈው ይህ ክቡር ሐዋርያ የአሕዛብን ልቦና በሚስብና በተረዳ ሁኔታ በኃያላን ነገሥታት ፊት መሰከረ። በመንፈስ ቅዱስ በታደሰ አንደበቱ በሚሰጠው ትምህርትና በሚያሳየው ተአምራት የሀገሩ ሰዎች ልባቸው ተነካ። ከበፊቱ ክፋት ተመልሰውም ወደ ፍጹም ሰብአዊ ርኅራኄ ገቡ። ሐዋርያው ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ በአሕዛብ ዘንድ ጉልቶ ከሚታይ ምቀኝነትና ቅንዓት ወደ መንፈሳዊ ቅንዓት፣ ከሕገ ጣዖት ወደ አማናዊ ሕገ ወንጌል፣ ከሰይጣን ቁራኝነትና ግዞት ወደ መንፈስ ቅዱስ ማደርያነት ለውጦ፣ የክፋትና የኃጢአት መራራነታቸውን በትምህርት አጣፍጦ፣ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የመዳን ምሥጢር ሊደረግላቸው እንደሚችል አሳመናቸው። በሰይጣን ታውሮ የነበረው ዓይናቸው በራ። ቅዱሱን በፍቅር ተቀበሉት። በወንጌል አመኑ። በፈጣሪና በእርሱ ያደረሱትን በደል አስበው ንስሐ ገቡ። "ከጠላት ሰይጣን አድነን፤ ወደ ፈጣሪህም ጸልይልን፤ አንተም ከዚህ ሀገር አትሂድብን" እያሉ ተማጸኑት።

ያላመኑት ግን ሐዋርያው በሚሰጠው ትምህርትና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሚያደርገው ተአምራት ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት በማድረጉ ሰይጣናዊ ቅንዓት ያዛቸው። የሰላም ወንጌል ከሚያስተምርበት ቦታ ሄደው እርሱንና ደቀ መዛሙርቱን በእሳት ለማቃጠል አሰቡ። ከዚያም በላይ "ትምህርት አቁምልን፤ እምቢ ካልክ ግን በእሳት እናቃጥልሃለን" እያሉ ዐመፁበት።

ሐዋርያውም ምንም ሳይፈራና ሳያፍር፦ "እናንተ ሰይጣን ያደረባችሁ ዐመጸኞች! ከኃጢአታችሁ ተመለሱ፤ ጣዖታትን አጥፉ። በሰማይም በምድርም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም" አላቸው። እነርሱ ግን በዐመፃቸው ቀጠሉ። "እርስ በእርሳችን አለያየን፤ ሰላምም ነሳን፤" ሲሉ በከንቱ ከሰሱት። ታላቅ ግርፋትን ገርፈው በከተማው ሁሉ ራቁቱን አዞሩት። በምን ዓይነት አገዳደል እንደሚገድሉት ምክረ ሞት እስኪጨርሱ ድረስም ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው እስር ቤት በማቆየት ብዙ መከራ አደረሱበት። ከዚህ በኋላ ኤግያስ በተባለው ሀገረ ገዢ ትእዛዝ በቅዱሱም ጥያቄና ፈቃድ (ከጌታዬ ጋር እንዳልስተካከል ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ ብሎ በጠየቃቸው መሠረት) የ "X" ፊደል በሚመስልና በተለምዶ አሁን "የቅዱስ እንድርያስ መስቀል" ተብሎ በሚጠራ መስቀል ታኅሳስ ፴ ቀን በ፷ ዓ.ም. የቁልቁሊት ተዘቅዝቆ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ዐረፈ። ከዚህ በኋላ ግሪክ ውስጥ አካይያ በተባለች ቦታ ቀበሩት።

ቅዱስ እንድርያስ በግሪክ በማስተማሩና በዚሁ በመሞቱ ግሪካውያን "የግሪክ ቅዱስ ጠባቂ" ይሉታል። ሩስያውያን ደግሞ "የሩስያ ተራዳኢ ቅዱስ" የሚል ስም ሰጥተውታል። የቅዱሱ ዓፅም በ፲፱፴፮ ዓ.ም. ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ወደ ቢዛንታይን አስወስዶታል። በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ሬጉሎስ የተባለ መነኰሴ የቀኝ እጁን ጣቶች ወደ ስኮትላንድ ወስዶታል። በስኮትላንድም የቅዱስ እንድርያስ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመርያ ጊዜ እንደተሠራ ይነገራል።

ተወዳጆች ሆይ! እንደተመለከትን ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ስለ ርትዕት ሃይማኖቱ ክብርት ነፍሱን ለወጠ፤ ያስተማረው የወንጌል ብርሃን ግን ይኸው እስከ ዛሬ በዓለም ሲነገር ይኖራል። እኛስ? ክብርት ነፍሳችንን የምንለውጠው ለምን ይሾን? ለዘፈን? ለስካር? ለሙስና? ለስርቆት? ለክፉ ወሬ? ወይስ ...? የየራሳችንን እንመርምር!

6. ሐዋርያው ፊልጶስ

በሁሉ ነገር ጠንቃቃ ለሆነ ብዙ ትርፍ አለው" ይላል የመጽሐፈ ምሳሌ ጸሐፊ /ምሳሌ.፲፬፡፳፫/። ጌታችንም "የሚፈልግ ያገኛል" ብሏል /ማቴ.፯፡፰/። ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ስለ ጌታችንና ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማው ልክ እንደ ሀገሩ (የቤተ ሳይዳ ሰዎች) እንደነ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ እንድርያስ ከመጥምቁ ዮሐንስ አልነበረም /ዮሐ.፩፡፵፬/። ሌላ ሐዋርያም አልጠራውም፤ ጌታችን "ተከተለኝ" ሲለው ብቻ የተከተለው ነው እንጂ። ጌታ ሲጠራውም ተመልሶ አልሄደም፤ እንደውም ሌሎችን ይጠራ ዘንድ ይቻኮል ነበር እንጂ። ከዚህም መረዳት እንደምንችለው ሐዋርያው ገና ለሐዋርያነት ሳይጠራ እንኳ ምን ያህል ጠንቃቃና እንዴት መጻሕፍተ ብሉያትን ያጠና እንደነበር፣ ደግሞም እንደምንም የመሲሑን መምጣት በታላቅ ጉጉት ይጠባበቅ እንደነበር ነው። ናትናኤልን ሲያገኘው "ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱየጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል" ብሎ ወደ ሙሽራው እንዲመጣ ማድረጉ ይህን ጥንቃቄውና ጉጉቱ የሚያሰይ ነው /ዮሐ.፩፡፵፭/።

ሐዋርያው ፊልጶስ በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ በአምስተኛ ደረጃ የሚጠቀስ ሐዋርያ ነው /ማቴ.፲፡፪-፬/። ወንጌላዊው ዮሐንስ በሦስት ቦታዎች ላይ ስለ ሐዋርያው ፊልጶስ ጽፎ እናገኛለን። እነርሱም፡-

- ጌታችን አምስት ሺሕ ሕዝብ በመገበ ጊዜ የሕዝቡን ብዛት ተመልክቶ ለዚህ ሁሉ የሚበቃ እንጀራ የለንም ብሎ እንደ ነበር /ዮሐ.፮፡፭-፯/፤
- ግሪኮች ከጌታ ጋር መገናኘት ሲፈልጉ ለሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ የነገረላቸው እርሱ ነው መሆኑን /ዮሐ.፲፪፡፳-፳፩/፤
- "ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል" ብሎ ጌታችንን በየዋህነት በመጠየቁ ምሥጢረ ሥላሴን ለመማር መብቃቱን /ዮሐ.፲፬፡፰/።

ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች ሐዋርያውን ከዲያቆኑ ፊልጶስ ጋር ያምታቱታል። ዲያቆኑ ፊልጶስ ግን በሐዋርያት አሳሳቢነት ማኅበረ ምእመናን ሊያገለግሉ ከተመረጡ ሰባቱ ዲያቆናት መካከል አንዱ ነው /ሐዋ.፮፡፭/። መኖርያው በቂሳርያ ሲሆን ባለትዳርና የአራት ሴቶች ልጆች አባት ነው /ሐዋ.፳፩፡፰/። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ሲያደርግ ያስተናገደው ዲያቆኑ ፊልጶስ ነው።

ሐዋርያት ዓለምን ሁሉ በወንጌል መረብ ለማጥመድ ዕጣ በተጣጣሉ ጊዜ ለፊልጶስ ሐዋርያ የደረሰችው ሀገር አፍራቅያ ትባላለች። ዕጣው እንደወጣለትም በደስታ ለመሄድ ተነሣ። ቅዱስ ጴጥሮስንም እንዲህ ሲል ጠየቀው፡- "አንተ ሐዋርያት ሁላችን ወደየተመደብንበት ሀገር ስንሄድ እንድታደርሰን እግዚአብሔር አዞሃልና እኔንም ታደርሰኝ ዘንድ እለምንሃለሁ።" ቅዱስ ጴጥሮስም አብሮት ሄደ።

ወደ ሃገሩ ለመግባት በተጠጉ ጊዜ ግን ሰይጣን ያደረበት ሰው ተቀብሎ፡- "የክርስቶስ ሐዋርያት ሆይ! ከሀገሬ እንድትገቡ አልፈቅድላችሁም" እያለ ይጮኽ ጀመር። ብጹዕ የሚሆን ሐዋርያው ፊልጶስም ጋኔን መሆኑን ስላወቀ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲወጣ አዘዘው። ሰይጣኑም ወጥቶ ሄደ። ሰውየውም ስለዳነ ሐዋርያቱን ሊከተላቸው ወደደ። ከሃገሩ መግቢያ መዝጊያም ከፍና ዝቅ እስኪል ድረስ ተአምራት ታየ። ካደረበት ጋኔን የተፈወሰው ሰውዬም እጅግ ተደነቀ። በከፍተኛ ቦታ ላይ

በመውጣትም፡- “የሀገሬ ሰዎች ሆይ! የእግዚአብሔርን በረከት ትቀበሉ ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ፊልጶስ ካሉበት ቦታ ተሰብስቡ” በማለት አሰምቶ ተናገረ፡፡ ወዲያውም መብረቅና ነጐድጓድ ሆነ፡፡ ከመብረቁና ከነጐድጓዱ የተነሣም ብዙ ሰዎች ሞቱ፡፡ የተቀሩትም ተሰብስበው መጡ፡፡ ሐዋርያቱም እጃቸውን ዘርግተው ሲጸልዩ አገኟቸው፡፡ ሰዎቹም በሐዋርያቱ እግር ስር ወድቀው ሰገዱላቸው፡፡ “የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆይ! ይቅር በሉን፤ መብረቁንና ነጐድጓዱንም አስወግዱልን” አሏቸው፡፡ ወዲያውም በእነ ጴጥሮስ ጸሎት መብረቁና ነጐድጓዱ ተወገደ፡፡ ሕዝቡን ለመጥራት ወደ ከፍተኛው የበሩ ግንብ የወጣው ሰውዬም ግንቡ ዝቅ ብሎለት ወረደ፡፡ ሕዝቡም ሰውዬውን “አምላክ ነህን?” አሉት፡፡ እርሱ ግን “እኔ ከእናንተ አንዱ ነኝ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በእነዚህ ሐዋርያት ትእዛዝ ተናገረ፡፡ አሁንም ወደ እነርሱ ቅረቡና ስለ ሀልዎተ እግዚአብሔር እንዲሁም ድኅነት ስለሚገኝበት ትምህርት ያስተምርዋችኋል” አላቸው፡፡

እነርሱም ወደ ሐዋርያው ፊልጶስ ቀረቡ፡፡ ሐዋርያውም “ምንን ታመልካላችሁ?” አላቸው፡፡ እነርሱም፡- “ከወርቅ የተሠራ የአሞራ ምስልን” አሉት፡፡ ፊልጶስ ይህን ምስል እንዲያመጡት አዘዛቸው፡፡ ካህናተ ጣዖቱ ግን “ዋይ ዋይ” እያሉ ያለቅሱ ነበር፡፡ የሀገሩንም ሰዎች፡- “የሚያድኑን አማልክቶቻችን አታጥፏቸው” እያሉ ይማልዷቸው ነበር፡፡ ሕዝቡ ግን “ይህስ ሰው ሠራሽ ነው፤ የሐዋርያትን ቃል እናከብራለን እንጂ” አሉ፡፡ ካህናቱ ተከትለው ከመጡ በኋላ ፊልጶስ መጸለይ ጀመረ፡፡ የእሳት ደመናም ወርዶ ከበባቸው፡፡ ጴጥሮስም ጣዖቱን ወረወረው፡፡ ካህናቱ በፍርሐት ተያዙ፡፡ እጅግም ተጨነቁ፡፡ አለቀሱም፡፡ ሐዋርያው ፊልጶስም “በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመኑና እሳቱ ይወገድላችኋል” አላቸው፡፡ እነርሱም “እናምናለን” አሉ፡፡ ተወገደላቸውም፡፡ ስለ ሀልዎተ እግዚአብሔርና ተምረውም “ከአንድ እግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ በሰማይም በምድርም የለም” አሉ፡፡ አጠመቅዋቸውም፡፡ ቀድሰውም አቆረብዋቸው፡፡ ኤጲስ ቆጶስን፣ ካህናትን ዲያቆናትን ሾሙላቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ተከሉላቸው፡፡ አንባብያን እዚህ ጋር ልናስተውለው የሚገባ ነገር አለ፡፡ ካህናተ ጣዖቶቹ ከአፍአ ስናየው ተገድደው ያመኑ ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፈተና የተግሳጽ ፈተና ይባላል፡፡ ይኸውም ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን ለማሳደድ በደማስቆ መንገድ ጌታችን በብርሃን ብልጭታ እንደገሰጸው ዓይነት ነው፡፡ ጌታ ይህን ያደረገውም የሰዎቹ ልብ መመለስ የሚችል መሆኑን ስለሚያውቅ ነው ማለት ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ወደ ሌላ ሀገር ወጣ፡፡ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰበከላቸው፡፡ ሰዎቹ ግን አጋንንት እያመለኩ ስለነበር “ኢየሱስ” የሚለውን ስም አያውቁትም ነበር፡፡ ሐዋርያውንም “ይህ ኢየሱስ የምትለው ማን ነው?” ብለውም ጠየቁት፡፡ እርሱም “እኔ የማመለክው አምላክ፣ ላመኑበት ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት የሚሰጥ፣ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ዓለምንም የፈጠረ እግዚአብሔር ነው” አላቸው፡፡ ቀጥለውም “የት ይገኛል?” አሉት፡፡ እርሱም “ሕያው እግዚአብሔር በሰማይም በምድርም ፈቃዱን በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ ነው፡፡ መሉዕ በሆለሄ ስለሆነ የሌለበት ስፍራ የለም” አላቸው፡፡ እነርሱም በዚህ ጌታ አመኑ፡፡

ሰይጣን ግን በዚህ በእጅጉ ቀና፡፡ አንዳንዶቹንም አስነሥቶ ሊያስገድለው ፈለገ፡፡ ቃለ እግዚአብሔር እንዳይነገር ወደደ፡፡ ከዚህ በኋላ ሐዋርያውን ለመግደል አንዳንዶቹ እጃቸውን አነሡ፡፡ ነገር ግን ዐይናቸው ታወረ፡፡ ይህን ድንቅ ተአምር ያዩ ሰዎችም “ስለምን ትገድሉታላችሁ? ከጨለማ ሕይወት ወደ ብርሃን፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ያወጣን ደገኛውን ፊልጶስ ስለምን ልትገድሉት ወደዳችሁ?” አሏቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ከመገደል ተረፈ፡፡ በዚህም ምክንያት በሃገሩ ሁሉ እየዞረ ክርስቶስን ሰበከላቸው፡፡ ብዙዎችም አመኑ፡፡ ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት ሕሙማነ ነፍስንም በትምህርት እየፈወሰ ሀልዎተ እግዚአብሔርን አሳወቃቸው፡፡ ሐዋርያውን ለመግደል ሰይጣን ያነሣሣቸው ሰዎች ግን በተደበቀ ቦታ እየተሰበሰቡ ፊልጶስን ለመግደል ወሰኑ፡፡ የሀገሩ ንጉሥም በነዚህ

ክፉ ሰዎች ሐሳብ ተስማማ፡፡ ሐዋርያውንም ይዘው እየደበደቡ፣ እየዛቱ፣ እያንገላቱም ወደ ወጎኒ ወሰዱት፡፡ እርሱ ግን በሚደርስበት መከራ ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ይደሰት ነበር፡፡ እንዲህም ይላቸው ጀመር፡- ከዘለዓለም ሕይወት ስለ ምን ትርቃላችሁ?የነፍሳችሁንስ ድኅነት ለምን አታስቡም? እነርሱም ልቡናቸው ደንድኗልና ብዙ መከራ ካጸኑበትና ካሠቃዩት በኋላ ኅዳር ፲፰ ቀን ሐራፖሊስ በተባለች ከተማ ሰቀሉት፤ ነፍሱንም በእግዚአብሔር እጅ ሰጠ፡፡ ሥጋውን በእሳት ሊያቃጥሉት በወደዱ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተለካ መልአክ ከእጆቻቸው መካከል ነጠቃቸው እያዩትም ወስዶ ሠወረው፡፡ ይህንንም ተመልክተው ስለገደሉት ተጸጽተው ያዘኑና ያመኑ ብዙዎች ቢጾሙና ቢጸልዩ ቢለምኑ ሰውን የሚወድ ቸው ይቅር ባይ ጌታችን ልመናቸውን ተቀብሎ በ፫ ቀን መልሶላቸው በፍጹም ደስታ አሳረፉት፡፡ ይህን ያዩ ሁሉ ወደ እምነቱ ገቡ፡፡ ከሐዋርያ ፊልጶስም ሥጋ ታላላቅ የሆኑ ድንቅ ድንቅ ተአምራት ተገልጠዋል፡፡

7. ሐዋርያው ናትናኤል

የተወለደው በናዝሬት በምትገኘው በቃና ዘገሊላ ነው፡፡ ዮሐ. 21÷2 የመጀመሪያ ስሙ ስምዖን ሲሆን ናትናኤል ብሎ የጠራው ጌታ ነው፡፡ የትውልድ ዘመኑ ጌታችን በተወለደበት ዘመን አካባቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ሄሮድስ የቤተልሔም ሕጻናትን በሚያስፈጅበት ጊዜ እናቱ ከበለስ ሥር ደብቃ አትርፋዋለች፡፡ ጌታም ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ሥር ሳለህ Aውቅሃለሁ ያለው ለዚህ ነው፡፡ ወደ ጌታ የጠራው ፊልጶስ ሲሆን ናትናኤል ምሁረ ኦሪት ነበርና ‹‹ ከናዝሬት መልካም ነገርAይወጣም›› በማለት የነቢያትን ቃል የጠቀሰው የመጻሕፍትን ቃል በማወቁ ነበርና፡፡ ዮሐ.1÷44-52 ናትናኤል ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ለሕገOሪት ቀናተኛ ስለነበር ቀናተኛ ተባለ፡፡ ማር. 3÷19 ሐዋርያው ስምዖን ወንጌልን በሶርያ፣ በባቢሎን በግብጽ እና ሊቢያ እየተዘዋወረAስተምሯል፡፡ ማቴ. 10÷4 በመጨረሻ በግብጽ ሲያስተምር ሕዝቡ በትምህርቱAምነው በመብዛታቸውAረማውያኑ ስለቀኑበት ለግብጹ ንጉሥEንድርያኖስ ከሰው በሠራዊትAስይዘው በማምጣት በንጉሡ ትእዛዝ ሐምሌ10 ቀን በሠይፍ አስገደሉት፡፡/ስንክሳር ሐምሌ10 /

8. ቅዱስ ቶማስ ሐዋርያ

ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው፡፡ ከመጠራቱ በፊት ስሙ ዲዲሞስ ነበር ትርጉሙም ጨለማ ማለት ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ ነው፡፡(ማቴ 10-3 ዩሐ. 20፡24 ሐዋ 1፡3)

መንፈሳዊ እድገት

ቅዱስ ቶማስ ሲጠራ ከሰዱቃውያን ወገን ስለነበር በትንሣኤ ሙታን(በሙታን መነሳት) የማያምኑት ሰዱቃውያን የወሰደውን ትምህርት ይዞ ጌታችን ከሙታን በተነሳ ጊዜ እጆቹን ካልዳሰስኩ በጦር የተወጋ ጎኑን አይቶ ዳሶ ካረጋገጠ በኋላ ያመነ ደቀመዝሙር ነው በሰዱቃውያን ትምህርት ሰው ከሞተ ሊነሣ አይችልም ብለው ያምናሉና.....በኋላም

ቅዱስ ቶማስ የእመቤታችንን ዕርገት ቀድሞ ያየ ሐዋርያ ነው

አገልግሎት

ለደቀ መዛሙርቱ በ50ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ ያገለግሉት ዘንድ ዓለማቱን በሃገረ ስብከት ከፋፈሉ፡፡ የሐዋርያው ቶማስ ሃገረ ስብከቱ ሕንደኬ ነው፡፡ ወንጌል ለመስበክ ምክንያት ይሆነኛል ብሎ በመስፍኑ ሉክዮስ ቤት በሠላሳ ብር ተቀጥሮ መስራት ጀመረ፡፡ ሕንጻ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ እችላለሁ አለ በዚህም መስፍኑ ቤተ መንግስቱን ያንጽለት ዘንድ ለቶማስ ብዙ ገንዘብ ቢሰጠው መጸወተው

ሉክዮስም ከሄደበት ሲመለስ ይታነጻል የተባለው ሕንጻ የለም ሕንጻውስ ቢለው ድሆቹን አሳየው በሃብት ንብረትህ በሰማይ መንግስት ተሰራልህ ሲለው ነው።መስፍኑም ተቆጣ ይህ ክፉ ባርያ ተጫወተብኝ ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ቆዳውን አስገፍፎ ስልቻ ሰፍቶ በአሸዋ ሞልቶ አሸክሞ ሲያዞረው የሉክዮስ ሚስት አዘነችለት በቃሉ ትምህርት ከልጆችዋ ጋር አምና ነበርና በድንጋጤ ወድቃ ሞተች። በአንተ ምክንያት ሞተች ስለዚህም ዳግመኛ ሚስቱ ትነሳና በአንተ ልመን የቃልህን ትምህርት ልቀበል አለው፤ ጌታ ቁስሉን አቀዝግዞለት ሕማሙን አስችሎት እርሷ ካለችበት ሄዶ በስልቻው ቢያስነካው ተነሳች በዚህም የእጁን ተዓምራት የቃሉን ትምህርት ሰምቶ ሉክዮስ አመነ ተጠመቀም።

ሰማዕትነት(ዕብ 11-36)

ከዚህም በኋላ ስልቻውን ተሸክሞ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ድውያንን እየፈወሰ አእዛብን እያስተማረ እያጠመቀ ቀንጦፍያ ደረሰ ቀንቶፍያም ሰባት ልጆች የሞተበትን ሽማግሌ አዝኖ አገኘው ልጆቹንም ከሞት አስነሳለት የእጁን ተዓምራት የቃሉን ትምህርት እየሰሙ ብዙዎች በወንጌል አመኑ። ከልጅ እስከ አዋቂ ከባርያ እስከ ገዢ ከሕዝብ እስከ ንጉሥ ድረስ በዚህም ካህናተ ጣኦት ቅንዓት አደረባቸው ስለዚህም ከንጉሥ ከመኳንንት አጣልተው በዚች ዕለት በሰይፍ አስመተሩት ።

9. ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ

ዮሐንስ የሚለው ስም ዮሐናን ከሚለው ቃል የተገኘ ሲኾን ትርጓሜውም " ከያሕዌ (ከእግዚአብሔር) የተሰጠ" ማለት እንደኾነ ብዙ ሊቃውንት ይስማማሉ። ትርጓሜ ወንጌል ግን "ዮሐንስ ማለት ፍስሐ ወሐሴት ማለት ነው" ይላል። ቅዱስ ዮሐንስ ብዙ ቅጽል ስሞች አሉት። ከእነዚኽም መካከል፦

- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በመግለጡና ለጌታችን ባለው ቅንዓት ባሳየውም የኃይል ሥራ **"ቦኤኔርጌስ -ወልደ ነጐድጓድ"** / ማር.፫፡፲፯/፣
- ኃላፍያትንና መጻእያትን ስለሚናገር **"አቡቀለምሲስ-ረአየ ኅቡአት- ባለ ራዕይ"**፣
- የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ስለሚናገር **"ታዖሎጐስ-ነባቤ መለኰት"**፣
- እንዲሁምየጌታን ጸዋትወ ሞካራ አይቶ ፊቱ በሐዘን ተቋጥሮ ይኖር ስለነበር **"ቁጹረ ገጽ- ፊቱ በሐዘን የተቋጠረ"** ይባላል፡ ፡
- ጌታችን ግርማመለኮቱን ሲገልጥ /ማቴ.፲፯፡ ፩/፣ የኢያኢሮስን ልጅ ሲያነሣ /ሚር.፭፡ ፴፯/፣ በጌቴሴማኒ የአታክልት ቦታ ሲጸልይ /ማቴ.፳፮፡ ፴፯/፣ ስለ ኢየሩሳሌምመጥፋት ትንቢት ሲናገር /ሚር.13፡ 3/ ዮሐንስ አብሮ ስለነበር **"የ ምሣጥር ልጅ"**ምይባላል፡ ፡
- ቅዱስ ጳውሎስ "Pillars of the Church- **አዕማደ ቤተ ክርስቲያን"** ብሎ ከሚጠራቸው ሐዋርያት አንዱ ዮሐንስ ነው/ገላ.፪፡ ፱/፡ ፡
- ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት በተለየ አኳኋንም ጌታን ይወደው ስለነበር ሁሌ ከእቅፍ አይለይም ነበር። በዚህም **"የጌታ ወዳጅ-ፍቁረ እግዚእ"** ተብሏል /ዮሐ.፲፫፡፳፫/።
- ከነዚህ በተጨማሪ ወንጌላዊው፣ ሐዋርያው፣ ድንግል፣ ዘንሥር፣ ዘረፈቀ ውስተ ህፅኑ ለኢየሱስ፣ ካልእ ረድእ፣ ባሕረ ጥበባት፣ አበ ልሳናት... እየተባለም ይጠራል።

የቅዱስ ዮሐንስ አባቱ ዘብዴዎስ የሚባል የሲዶና ሀገር ገሊላዊ ሲሆን ዓሣ አጥማጅ ነበር። እናቱም ማርያም ባውፍልያ እንደምትባልና ከ፸፮ቱ ቅዱሳት አንስት አንዲ መኾኗን የቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት ያስረዳል /ማቴ.፳፯፡፭/።

ቅዱስ ዮሐንስ በመጀመርያ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙር ነበር/ ዮሐ.፩፡፴፭-፵/፡፡ በኋላ ግን ከታላቅ ወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ሰዎችን እንደ ዓሣ በወንጌል መረብ ከዚሁ ዓለም ባሕር ለማጥመድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የስብከት ሥራውን እንደ ጀመረ በቅፍርናሆም ከተማ በገሊላ አጠገብ ሲመላለስ ሳለ ጠራው /ማቴ. ፬፡፳፩/፡፡ እርሱም ወዲያው ከወንድሙ ጋር ታንኳይቱንና አባቱን ትቶ ተከተለው፡፡ ጌታችን ሲጠራው የሃያ ዓመት ወጣት እንደ ነበረም ሄራኤዎስ የተባለ ደቀ መዝሙሩ ጽፏል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ ኹሉ የተለየ ፍቅር ስለነበረው ጌታችንን እስከ እግረ መስቀሉ ድረስ ተከትሎታል፡፡ ለዚኽም መላው የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖችን ወክሎ የእመቤታችንን እናትነት ከጌታ ተቀብሏል፡፡ በዚያች የመከራና የኑዛዜ ሰዓት የተገኘ የቁርጥ ቀን ወዳጅ በመኾኑ በአደራ መልክ “እነኂት እናትኽ” ተብሏል፡፡ እርሱም ለእመቤታችን ልዩ አክብሮትና ፍቅር ስለነበረው በእናትነት ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወስዷታል፡፡ አደራውን አክብሮ በመጠበቅና በማጽናናትም ፲፭ ዓመት ሲታዘዛት ኖሯል /ዮሐ.፲፱፡፳፭-፳፯/፡፡

ሐምሌ ፭ የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር እንደሚገልጠው ቅዱስ ዮሐንስ የስብከቱን ሥራውን በኢየሩሳሌምና በአከባቢው የጀመረው ወደ አንጾክያ ሄዶም ያስተማረው ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ነው፡፡ ከኢየሩሳሌም እስከ አንጾክያ በፈረስ ፰ ቀን ያስኬዳል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ጴጥሮስ ግን በእግዚአብሔር ርዳታ በአንዲት ሌሊት ደረሱ፡፡ ዮሐንስም ወደ ከተማይቱ ቀደም ብሎ ገባና ስለ ሀገሩ ጥናት ሲያደርግ የሀገሩ ሰዎች እጅግ ክፉዎች እንደ ኾኑ ተረዳ፡፡ ምንም እንኳ በክፋታቸው ቢያዝንም ቅዱስ ጴጥሮስ አጽናንቶ አደፋፈረውና ወደ ከተማይቱ ገብተው በክርስቶስ ስም ወንጌልን ሰበኩ፡፡ ጣዖትን ከሚያመልኩ ሰዎች ብዙ መከራ ቢደርስባቸውም በአንጾክያ ውስጥ ተአምራትን እያደረጉና በስብከት በክርስቶስ ወንጌል ብዙ ሰዎችን አሳመኑ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ከዚህ ሌላ ያስተማረባት ሀገር ሎዶቅያ እንደምትባል ስንክሳሩ ይገልጣል፡፡ በከተማ አጠገብ ያለ ቁድሮስ የሚባል ወንዝ ሞልቶ የሀገሪቱን ብዙ ንብረት ባወደመ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ ከቅዱስ ጴጥሮስ ዘንድ ሄደና በተአምራት የውኃውን መላት አቆመላቸው፡፡ ወደ ከተማዋም ገብቶ ብዙ ተአምራትን እያደረገ ወንጌልን ሰበከ፡፡ ካዩት ተአምራትና ከሰሙት ትምህርት የተነሣም ብዙዎች አመኑ፡፡

ጥር ፬ በሚነበበው ስንክሳር እንደምናነበው ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ በሕይወቱ መጨረሻ አከባቢ ያስተማረው በእስያ ሀገር ሲኾን ዋና መንበሩም ኤፌሶን ነበረች፡፡ ዮሐንስ ወደዚህች ከተማ የመጣው ከደቀ መዝሙሩ ከአብሮኮሮስ ጋር ነው፡፡ የስብከት ሥራቸውን በቀጥታ መጀመር ስላልቻሉም ሮምና የምትባል አንዲት ሞግዚት ቤት ውስጥ ባሮች ኾነው ገቡ፡፡ እርሷም ዮሐንስን እንጨት ፈላጭ፣ አብሮኮሮስን ደግሞ ውኃ ቀጅ አደረገቻቸው፡፡ አንድ ቀን ከምታሳድጋቸው ልጆች አንዱን ይዛ ወደ ቤተ ጣዖት ስትገባ ዮሐንስና አብሮኮሮስ አብረዋት ገቡ፡፡ ያን ጊዜ በቤተ ጣዖቱ ያደረው ሰይጣን እነ ቅዱስ ዮሐንስን ሲያይ የቤቱን ዕቃ አደናብሮ ወጣ፡፡ አስከትላው የነበረው ልጅም በድንጋጤ ሞተ፡፡ ያን ጊዜ “የእናንተ መምጣት ነው ለዚህ ኹሉ ያበቃኝ” ብላ ደበደበቻቸው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም “አስነሡልኝ አትዱምን?” ብሎ መለሰላት፡፡ “ያሁኑ ይባስ! ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ የሞተ ሰው የሚነሣው?” ብላ የበለጠ ተቆጣች፡፡ ይህን ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስና አብሮኮሮስ ጸሎት አቅርበው አስነሡላት፡፡ በዚህ ተአምር አምና ተጠምቃለች፡፡ በቤቷም የምእመናን ጉባዔ ተመሠረተ፡፡ እርሷንም ለዚያ እመ ምኔት አድርገው ሾሟት፡፡ ከዚያም በኤፌሶንና በአከባቢዋ ወንጌልን ለመስበክ ሰፊ በር ተከፈተለት፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ በኤፌሶን በሚያስተምርበት ጊዜ ከኔሮን ቄሣር ቀጥሎ በሮም የነገሠው ድምጥያኖስ (፹፮-፺፮ ዓ.ም) የራሱን ምስል አሠርቶ እንዲሰገድለት ወደ ኤፌሶን ላከ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ግን ከምእመናን

ጋር ኾኖ ይህን ድርጊት ተቃወመ። ከዚያም ወደ ሮም ተወሰደና በፍል ውኃ ተሰቃይቶ በመንግሥት ላይ ያመፁ ኹሉ ወደ ሚታሠሩባት በደሴተ ፍጥሞ እንዲታሰር ተፈረደበት። ራዕዩን ያየውና የጻፈውም በዚያ ቦታ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ድምጥያኖስ ከተገደለ በኋላ ከግዞቱ ተመልሶ ሦስቱን መልእክታቱና ወንጌሉን እንደ ጻፈ ይነገራል።

ስለ ቅዱስ ዮሐንስ የመጨረሻ ሕይወት ኹለት የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። አንደኛው በዮሐ.፳፡፳-፳፫ ላይ የተጻፈውን መነሻ በማድረግ "ዮሐንስ ሞትን አልቀመሰም" የሚል ሲኾን ኹለተኛው ደግሞ በማር.፲፡፴፰-፴፱ የተጻፈውን ቃል በመጥቀስ "የጌታን የሞት ጽዋ ጠጥቷል፤ የሞትን ጥምቀት ተጠምቋል፤ በግልጽ አነጋገር ሞቷል" የሚል ነው።

አባ ጀሮም ስለ ወንጌላዊው ሲገልጥ ዮሐንስ የመጨረሻውን በምድር የኖረበትን የዕድሜ ዘመን በኤፌሶን ከተማ እንዳሳለፈው ጽፏል። በዚህ ወቅትም እጅግ ከማርጀቱ የተነሣ "እርስ በራሳችሁ ተዋደዱ ይህ የጌታችን ትእዛዝ ነውና ይህን ከጠበቃችሁ ይበቃችኋል" የምትለዋን ቃል ብቻ ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ነበር። ይህ የዮሐንስ የዘወትር ትምህርቱ ነው። ደቀ መዛሙርቱም "አባታችን ለምን ኹል ጊዜ አንድ ዓይነት ትምህርት ታስተምረናለህ" ሲሉትም "ልጆቼ ይህ የጌታ ትእዛዝ ነው" በማለት ይመልስላቸው ነበር።

ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የወንጌላዊው በዓል በየዓመቱ ጥር ፬ እና በየወሩ በ፬ እርሱ የደረሰው የቁርባን ምስጋና እንዲቀደስ ታዛለች።

ቅዱስ ዮሐንስና የጌታ ሥዕል

ለጌታችን ሥዕል ምንጭ ከኾኑት አንዱ ወንጌላዊ ዮሐንስ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ዘመን የነበረው የሮማ ቄሣር ጢባርዮስ ቄሣር ይባላል። የቄሣሩ ልጅም ታማሚ ነበር። ቄሣሩም የጌታን የማዳን ሥራ እየሰማና እነ ጲላጦስንም የጻፉለትን ደብዳቤ እየተመለከተ "ከዚያ ደግሰው መቃብር ወስዶ ልጄን ማን ባሳለመልኝ?" እያለ ይመኝ ነበር። በመጨረሻም ልጁን ወስደው በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ከሕመሙ ስለተፈወሰለት ፍቅሩን ለመግለጥ የጌታን ሥዕል የሚሥልለት ሰው ያፈላልግ ጀመር። ከዚያ በኋላም ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ተገኝና ልክ በዕለተ ዓርብ እንዳየው አድርጐ ሥሎ ሰጠው።

ቅዱስ ዮሐንስና አስቸጋሪው የሽፍቶች አለቃ

አንድ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ ከኤፌሶን ከተማ ተነሥቶ ክርስቲያኖችን ለማስተማር ሲዘዋወር ወደ አንድ ትልቅ ከተማ ገባ። በዚያች ከተማ የሚገኙ ምእመናንም ጊልስ ስለሚባልና በዐሥራዎቹ ዕድሜ ክልል ስላለ አንድ ወጣት ታሪክ አጫወቱት። ወጣቱን በጣም ይወዱት ስለነበርና እናትና አባቱ ስለሞቱ "የሚንከባከበውና የሚያስተምረው ካጣ ሊበላሽ ይችላል" ብለው ለቅዱስ ዮሐንስ ነገሩት።

ቅዱስ ዮሐንስም ይኽንን ሲሰማ ወጣቱ ጊልስን ወደ ከተማይቱ ጳጳስ ወሰደውና "እንደ ልጅህ ተንከባከበው፤ እውነተኛ ክርስቲያንም አድርገው" ብሎ ሰጠው። የከተማዋ ጳጳስም ደግ ስለነበረ ጊልስን በደስታ ተቀበለው። ዘወትርም ያስተምረውና ይንከባከበው ነበር። በመጨረሻም የአከባቢው ምእመናን በተሰበሰቡበት ጊልስ ተጠመቀ።

ከዚህ በኋላ ግን ነገሮች መቀያየር ጀመሩ። እኒያ አባት ሥራ በጣም ስለበዛባቸው ጊልስን "መቼም ተጠምቋል" ብለው እንደ በፊቱ መቆጣጠርና ማስተማሩን ተዉት። ጊልስም የለመደው የአባትነት ፍቅር ሲያጣ ወደ ከተማ ወጣ ብሎ ከእኩዮቹ ጋር መቀራረብ ጀመረ። ጓደኞቹ ግን መልካም አልነበሩም። ጠጭዎች፣ ቁማርተኞችና ተደባዳቢዎች ነበሩ።

አንድ ቀን ማታ በአንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ጊልስና ጓደኞቹ ሲጠጡ አመሹ። ኹሉም ስክረው በያሉበት ሲወደቁ ጊልስ ብቻውን ቀረ። በመጨረሻም የኹሉንም የመጠጥ ሒሳብ ከፍሎ ያለውን ገንዘብ ጨረሰ። በነጋታው ጊልስ ለጓደኞቹ "ለእናንተ ስል ገንዘቤን ኹሉ አባክንኹ፤ አሁን ባዶ ኪስ ሆኛለኹ" ብሎ ነገራቸው። ኹሉም ሳቁበትና "ጅሉ ጊልስ ! እኛ ገንዘብ ከየት የምናመጣ ይመስልኻል? ይልቅ የምታገኘውን አጋጣሚ ተጠቅመኽ ስረቅ" አሉት።

በዚህ መሠረት ጊልስና ኹለቱ ጓደኞቹ የአንድ ሰው ቤት ሰብረው ገቡና ገንዘቡንና ጌጣጌጡን ዘረፉ። በዚህም የተነሣ ጊልስ "መስረቅ ማለት በጣም ቀላል ሥራ ነው" ብሎ አመነ። ከዚያ በኋላ ጊልስና ጓደኞቹ የታወቁ ዘራፊዎች ኾኑ። እነርሱ ባሉበት መንገድ ማንም በጤና ማለፍ አይችልም ነበር። አንድ ቀን ሰው ሲደበድቡ ነፍሱ በእጃቸው ስለ ጠፋች ጊልስና ጓደኞቹ ከተማዋን ጥለው ጠፉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም የጊልስ ስም በአከባቢው እየገነነ ስለ መጣ ሰው ኹሉ ይፈራው ጀመር። እርሱና ጓደኞቹ አላፊ አግዳሚውን አላስቀምጥ አሉ። መንገደኞች ኹሉ በሰላም መጓዝ፣ ነጋዴዎችም በጤና መነገድ አልቻሉም። ጊልስ አለቃቸው ነበር። መግደልና መዝረፍም የዘወትር ሥራቸው ኾነ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ግን ቅዱስ ዮሐንስ ወደዚያች ከተማ መጣ። እኒያን ጻጻስም ስለ ወጣቱ ጊልስ ጠየቃቸው። እርሳቸውም በጣም አፍረውና አዝነው፡- "ያልከኝን አልሰማኹም፤ ያዘዝኸኝንም አልፈጸምኩም። ጊልስ ዛሬ ሰው ኹሉ የሚፈራው ወንበዴ ኾኗል። ዛሬ አላፊ አግዳሚውን አያስቀምጥም። ይህ ኹሉ ግን የእኔ ስሕተት ነው" በማለት በፊቱ አለቀሱ።

ቅዱስ ዮሐንስም ይህንን ሲሰማ በእጅጉ አዘነ። ወዲያውም ጊልስ ያለበትን ጠየቀና በፈረስ እየጋለበ ተጓዘ። የአከባቢው ምእመናን "ጨካኝ ናቸውና ይገድሉኻል" ቢሉትም አልተመለሰም።

በተባለው ቦታ ሲደርስም ኹለቱ ሽፍቶቹ አገኙት። ወዲያውም ጩቤያቸውን መዝዘው ከፊቱ ቆሙ። ቅዱስ ዮሐንስም ፍቅር በተሞላበት ንግግር "እርሱ የድሮ ጓደኛዬ ነውና ከመግደላችሁ በፊት እባካችሁ ወደ አለቃችሁ ውሰዱኝ?" አላቸው።

ሽፍቶቹም እየሳቁ ወደ አለቃቸው ዘንድ ወሰዱት። ጊልስ መጣ። ቅዱስ ዮሐንስም በፍቅርና በፈገግታ ተመለከተው። ጊልስ ዐወቀው። ደነገጠ። ዘወር ብሎም መሮጥ ጀመረ። ያን ታላቁን ሰው ዮሐንስን ፈራ። ቅዱስ ዮሐንስም "ልጄ ለምን ትሸሻለህ? እኔ አባትህ ነኝ ምንም የሚጐዳ መሳርያም አልያዝኩም" አለው። ያ ጨካኝ የሽፍቶች አለቃ ምርር ብሎ አለቀሰ፤ አነባ። መሳርያውን ኹሉ አምዘግዝጎ ጣለ። ጓደኞቹንም፡- "እኔ ወደ ጌታዬ መመለሴ ነውና ደኅና ኹኑ" አላቸውና ከቅዱስ ዮሐንስ ኋላ ተፈናጥጦ ወደ ጥንቱ ቦታው ተመለሰ። ትቷት ሄዶ በነበረችይቱ ቤተ ክርስቲያንም ዕድሜ ልኩን እግዚአብሔርን እያገለገለ ኖረ።

የዘመኑ ማጅራት መቺዎች ከጊልስ ምን ይማሩ ይኾን?

ቅዱስ ዮሐንስና ምሳሌው

ቅዱስ ዮሐንስ ከአራቱ እንስሶች መካከል በንስር ይመሰላል። በንሥር የመመሰሉ ምክንያትም እንዲህ ነው። በሥነ አንስርት (አሞሮች) ጥናት ሊቃውንት እንደሚነገረው ንስር ዐይኑ ፅሩይ ነው። ወደ ላይ መጥቆ ይበራል። ወጥቶ ረቦ ቁልቁል በተመለከተ ጊዜም የሰናፍጭ ቅንጣት የምታኽል ሥጋ ብትኾንም አትሰወረውም። ያቺን አንሥቶ ይመገባታል። ቅዱስ ዮሐንስም አካልና ሕልውና ተገልጦለት፣ ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት "ቀዳሚሁ ቃል" ብሎ ተናግሯልና። ይህም መጥቆና ረቅቆ የሚያስብ ልዑለ ስብከት መኾኑን ያመለክታል። ዳግመኛም ንስር በእግሩ ይሸከረከራል፤ በክንፍ መጥቆ ይበራል። በእግር እንዲሸከረከር ዮሐንስም እንደ

ወንድሞቹ “ ወልደ እጓለ እም ሕያው ከሰማይ ወረደ ተወለደ” እያለ ይጽፋል። በክንፍ መጥቆ እንዲበር እርሱም አካል ከሕልውና ተገልጦለት “ቀዳሚሁ ቃል” ብሎ ተናግሯልና።

ቅዱስ ዮሐንስና መጻሕፍቱ

በሐዲስ ኪዳን ከቅዱስ ጳውሎስ ቀጥሎ ብዙ መጻሕፍትን የጻፈ ቅዱስ ዮሐንስ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ፲፬ መጻሕፍትን የጻፈ ሲሆን ቅዱስ ዮሐንስም ፭ መጻሕፍት ጽፏል። እነርሱም አንድ ወንጌል፣ ሦስት መልእክታትና አንድ ራዕይ ናቸው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት ከ፲፬ቱ መጻሕፍተ ቅዳሴ አንዱ የዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ መጽሐፍ ነው። የመጻሕፍቱን አጠቃላይ ዓላማ፣ መቼና የት እንደተጻፉ እንደሚከተለው በአጭር በአጭሩቀርቧል፡-

፩. **የዮሐንስ ወንጌል፡-** ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን ከፍጥሞ ደሴት ከግዞት ሲመለስ በኤፌሶን በ፺፮ ዓ.ም አከባቢ በዮኖናውያን (በግሪክ) ቋንቋ ጽፎታል። የመጽሐፉ ዋና ዓላማም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናምን ዘንድ አምነንም በስሙ ሕይወት ይኾንልን ዘንድ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በጊዜው ለነበሩ ኢስጦኢኮች ተብለው ለሚጠሩ የግሪክ ፈላስፎች መልስ ለመስጠት ተጽፏል። በሌላ አገላለጽ ለዕቅበተ -እምነት (Apology)። ፈላስፎቹ፡- “ነፍስን፣ መላእክትን እና ሌሎች ረቂቃን ፍጥረታትን የፈጠረ Logos ቃል የሚባል ደግ አምላክ አለ። ደግሞም ግዙፉን ዓለም እና የሰውን ሥጋ የፈጠረ ሌላ ክፉ አምላክ አለ። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በደጉ አምላክ የተፈጠረችውንና በሰው ውስጥ ያለችውንና ነፍስ ነጻ ለማውጣት የተላከ “ፍንጣሪ lon” ነው። ሥጋ የክፉ አምላክ ፍጥረት ስለሆነም እርሱ ሥጋ አልለበሰም” ብለው ስለሚያስተምሩ ዮሐንስ “ወልደ እግዚአብሔር በመጀመሪያው Logos ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበረ፥ ቃልም ራሱ እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው ከዘላለም ጀምሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። እናንተ የደጉ አምላክ ፍጥረትና የክፉ አምላክ ፍጥረት የምትሉት (የሚታየውም የማይታየውም) ሁሉ በእርሱ ተፈጠረ፥ ከተፈጠረውም አንድ ስንኳ ያለ እርሱ ቃልነት የተፈጠረ የለም ”እያለ ይቀጥልና “ያ ቀዳማዊ Logos ቃልም በመምሰል ሳይሆን በኩነት ሥጋን ተዋሕዶ በእኛ አደረ፤ አማኑኤል ሆነ” እያለ አስፍቶና አምልቶ በጥልቀት የሎጐስን እውነተኛ ትርጓሜ ጽፎላቸዋል።

፪. **የመጀመርያዋ የዮሐንስ መልእክት፡-** የተጻፈችው በመጀመርያ ምእተ ዓመት መጨረሻ አከባቢ (ከ፺፭-፺ ዓ.ም) በሀገረ ኤፌሶን መኾኑን ብዙዎች ይስማማሉ። የተጻፈችበት ዓላማም በዚያ ዘመን ከተነሡት መናፍቃን እንዲጠበቁ ምእመናንን ለማሳሰብ ነው።

፫. **ኹለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት፡-** በኤጅያን ደሴቶች ቀለብ እየተሰፈረላት የነገሥታትን ልጆች የምታሳድግ ሮምና የተባለች ሞግዚት ነበረች። ቅዱስ ዮሐንስ ከደቀ መዝሙሩ ከአብሮኮሮስ ጋር ኾኖ ጣዖት አምላኪ የነበረችውን ይህች ሴት አሳምነው የክርስቶስ አደረጓት። አምና የተጠመቀች ይህች ሴትም በቤቷ የምእመናን ጉባዔ ተመሠረተ። ኾኖም ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በታሰረ ጊዜ በሮምና ቤት ያለው የክርስቲያኖች ጉባዔ በመናፍቃን የክሕደት ትምህርት የተነሣ መከፋፈል ደረሰበት። ጠብና ክርክር ተነሣ። ይህን የሰማ ቅዱስ ዮሐንስም የድሮ ኑሮዋን ኹሉ አስታውሳ ያሁኑን መከራ እንድትረሳና አማኞች ተቀብለው የሚያስተናግዷቸውን መምህራን እነማን እንኾኑ ለይተው ያውቁ ዘንድ በ፺፮ ዓ.ም አከባቢ ይህን መልእክት ጻፈላት።

፬. **ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት፡-** ይህች መልእክትም በ፺፮ ዓ.ም አከባቢ የተጻፈች እንደኾነ ይገመታል። ጋይዮስ በስደት ምክንያት የሚንከራተቱትን ክርስቲያኖች እየተቀበለ የሚያስተናግድ ሰው ነበር። ይህን ደግነቱን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስ በዚያ በመከራ ዘመን እንዲህ ያለ ሰው መገኘቱን እያመሰገነና እያበረታታ ጽፎለታል።

፫. **የዮሐንስ ራዕይ፡-** የተጻፈበት ቦታ በፍጥሞ ደሴት ነው። ይህች ቦታ በሮማ መንግሥት ላይ ያመፁ ሰዎች የሚታሰሩባትና ልምላሜ የማይታይባት ደረቅና ድንጋያማ የኾነች ምድረ በዳ ቦታ ናት። ቅዱስ ዮሐንስም ከ81-96 ዓ.ም በነገሠው በድምጥያኖስ ዘመን ንጉሡ እንዲሰግድለት በኤፌሶን ያቆመውን ምስል በመቃወሙ በዚህች ደሴት እንደታሰረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። የተጻፈበት ዘመንም በ፺፮ ዓ.ም ገደማ እንኾነ እውቁ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ ተናግሯል /፫፡፲፰/። የተጻበት ዋና ዓላማም ክርስቲያኖች የነገሥታትን አምልኮ በጽናት እንዲቃወሙ ለመምከር ነው። ዲያብሎስ በምእመናን ላይ የሚያስነሣውን ስደትና መከራ እንዲሄድ ቢያደርግም ክርስቲያኖች ግን እስከ ሞት ድረስ ጸንተው መቆም እንዳለባቸው ለመምከር ጭምርም ነው። ከዚሁ ጐን ለጐን ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ እንደሚመጣ ለመግለጥ፣ ከመምጣቱ በፊት ግን በምድር ላይ ስለሚኾኑት ክፉና መልካም ነገሮች በትንቢት መልክ ለመግለጽ ተጽፏል።

፮. **ቅዳሴ ዘዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ፡-** ውስጡ ብዙ ነገሮችን በተለይም ምሥጢረ ሥላሴ፣ የወልደ እግዚአብሔር የቤዛነት ሥራ፣ ምልጃና ሌሎችም ያካተተ የቁርባን ምስጋና ነው። በአጠቃላይ ቅዱስ ዮሐንስ የሰማያት ምሥጢራት ተከፍቶለት ያየ፣ ለእመቤታችን ልዩ ፍቅር የነበረው፣ የእመቤታችን አስከሬን በዕፀ ሕይወት ሥር መቀመጡን ለሐዋርያት ያበሠረ ታላቅ ሐዋርያ ነው። ከሕይወቱም እጅግ በርካታ ቁም ነገሮችን እንማራለን። ቅንዓት፣ ተመስጦ፣ ፍቅር፣ ለእመቤታችን የነበረው ልዩ አክብሮትና ፍቅር፣ ጥብቅና (ለርትዕት ሃይማኖት)፣ ያዘኑትን ማጽናናት፣ በየዐውደ ምሕረቱና በየሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን፣ በየጽዋ ማኅበራቶቻችን ተቀብለን የምናስተናግዳቸውን መምህራን እነማን እንኾኑ ለይተን ማወቅ እንዲገባን፣ ...!!!

10. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ/ወልደ እልፍዮስ/

ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ትውልድ ነገዱ ከነገደ ጋድ ሲሆን በሌላ አጠራር ታናሹ ያEቆብ ይባላል። ወንጌልን ለማስተማር የደረሰችው ሀገር ኢየሩሳሌም ፍልስጥኤም ሲሆን በነዚሁ ሀገር አሚነ ክርስቶስን አስተምሮ ሕዝቡን ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ከሕገ ጣዖት ወደ ሕገ ወንጌል ከዲያብሎስ ቁራኝነት ወደ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ቢመልስ ጣዖት አምላኪያን የሐሰት ምሥክሮችን አቁመውና አጣልተው በድንጋይ ተወግሮ የካቲት 10 ቀን በ62 ዓ.ም በሰማዕትነት ዐርፏል።

11. ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ/ልብድዮስ/

የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ በመባል ይታወቃል። የሐዋ. ሥራ1÷13፣ ሉቃ. 6÷16 ታዴዎስ ልብድዮስ እየተባለ ይጠራል። ማቴ. 10÷4

የሐዋርያው ታዴዎስ ሀገረ ስብከት ሶርያ ነው። በአንድ ቀን ያለጊዜው እህልን ዘርቶ ለጐተራAብቅቷል። አንድ ዘማዊት ሴትን በነፋስ አውታር እንድትንጠለጠል አድርጓል። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ቃል በተግባር ፈጽሞ ያሳየ አባት ነው። ማቴ19÷24 በመጨረሻም ወንጌል በተለያዩ ሀገሮች አስተምሮ ሐምሌ2 ቀን በድንጋይ ተወግሮ በሰማEትነትACፏል።

12. ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ

ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ የተወለደው በቤተልሔም ነው። በከሀዲነቱ ቦታውን በለቀቀው በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ የተተካ ሐዋርያ ነው። (ሐዋ 1፥15-26) አስቀድሞ ቁጥሩ ከ72ቱ አርድዕት መካከል ነበር።
ለሐዋርያነት ከተመረጠ በኃላ ለወንጌል አገልግሎት የሄደው የሰው ሥጋ ወደሚበሉ ሰዎች ነበር። የእዚያ ሀገር ሰዎች እንግዳ ወደ ሃገራቸዉ ሲገባ ወደ እስር ቤት ይወስዱትና ለ 30 ቀናት ሳር እንዲበላ ካደረጉት በኃላ አውጥተው ሥጋውን ይበሉ ነበር። ሐዋርያው ማትያስንም ይዘውት ዓይኑን ካወጡት በኃላ እስር ቤት ሳር እንዲበላ አስገቡት። ጊዜውም ከመድረሱ በፊት ጌታችን ሐዋርያው እንድርያስንና ደቀመዝሙሩን

ወደ እርሱ ላከለት፡፡ እስር ቤትም ገብተው የሚደረገውን ተመልከቱ፡፡ በዚህ ጊዜ እነዚህን ሐዋርያት ይገድሏቸው ዘንድ ሰይጣን የከተማውን ህዝብ አነሳሳ፡፡

ሕዝቡም ሊይዟቸው ባሰቡ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ የእስር ቤቱ የውኃ ምንጭ ፈነዳና ከተማውን አጥለቀለቀው፡፡ ሕዝቡም በጨነቃቸው ጊዜ ወደ ሐዋርያቱ ቀርበው አለቀሱ፡፡ ሐዋርያቱም ስለ ክርስቶስ አስተማሯቸው እና አሳመኗቸውም፡፡ ወደ እግዚአብሔርም ጸልየው ጎርፉ ተወገደላቸው፡፡ ሐዋርያው ማትያስን ከእስር ፈቱት፡፡ የነበረባቸውንም የአውሬነት ጸባይ በጸሎት አስወገዱላቸው፡፡

ከዚህም በኃላ ሐዋርያው ማትያስ ወደ ደማስቆ ሄዶ ወንጌልን በሚያስተምሩበት ጊዜ ሕዝቡ ተቆጥቶ በብረት አልጋ ላይ አስተኝተው በስሩ ሰባት ቀናት ያህል እሳት ለቀቁበት፡፡ በሰባተኛውም ቀን ቢመለሱ ምንም ሳይሆን እንዲያውም ፊቱ እንደፀሐይ ሲያንፀባርቅ ታይቷል፡፡ በዚህም ተገርመው በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ተጠምቀዋል፡፡ በመጨረሻም በተለያዩ ሀገር ሲያስተምር ከቆየ በኃላ ፊላዎን በተባለች ቦታ ሸምግሎ እድሜ ጠግቦ መጋቢት 8 ቀን በሰላም አርፏል፡፡

13. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

ቅዱስ ጳውሎስ ነገዱ ከብንያም ወገን ሲሆን ጠርሴስ በተባለች ቦታ ተወለደ፡፡ የወቀድሞ ስሙ ሳኦል ይባለ ነበር፡፡ አባቱ የሮማዊ ዜግነት ስለነበረው ይህ ዜግነት ለልጁ ለጳውሎስ ተላልፎለታል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ 15 ዓመት ሲሆነው በኢየሩሳሌም ዝነኛ በነበረው የህግ መምህር ገማልያል የአይሁድን ሕግና ሥርዓት እየተማረ እስከ 30 ዘመኑ ድረስ ቆየ፡፡ ከትምህርቱም ጋር የዕለት ምግቡን ለማግኘት ድንኳን አሰፋፊን ተማረ (ሐዋ 18 ÷ 3)

የወንጌል ትምህርት ከኦሪት የሚለይ መስሎት ለኦሪት ትምህርት በመቅናት ክርስቲያኖችን ያሳድድ ጀመር፡፡ (ገላ 1፥13) በደማስቆም ብዙ አይሁድ ክርስትናን እንደተቀበሉ ሲሰማ እነሱን አስሮ ለማምጣት የሚያስችለውን ደብዳቤ ተቀብሎ ሲሄድ ጌታችን ከመንገድ ላይ ለልዩ አገልግሎት ጠርቶታል፡፡ ተጠምቆም ክርስቲያን እንደሆነ በየምኩራቡ እየገባ ስለ እየሱስ ክርስቶስ ሲሰብክ ብዙ ሰው ተቃወመው፡፡ ሊገድሉትም አጥብቀዉ ፈለጉት ከከተማውም እንዳይወጣ ቅጥሩን ዙሪያውን በጥብቅ ሲጠብቁ ሳለ ክርስቲያኖች በቅርጫት ውስጥ አድርገው በቅጥሩ ላይ አድርገው እንዲያመልጥ አደረጉት፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ለ 42 አመታት ያህል በሐዋርያነት አገልግሏል፡፡ በባህር በእግር ተመላልሷል፡፡ በ12ቱም ሐዋርያት ሃገረስብከት እየገባ ወንድሞቹን አግዟቸዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በጣም ትእግስተኛ ነበር፡፡ ለቆሮንቶስ በላከው ቀዳማዊ መልእክቱ 11፥25-33 እንደገለፀው ብዙ ፈተናዎችን አልፏል፡፡ ሁለት ጊዜ ታስሯል፤ ተደብድቧል፤ በረሃብ ተሰቃይቷል፡፡ ይህ ሁሉ ቢሆንበትም ደስተኛ ነበር፡፡ ሁሉንም በትዕግስት ያሳልፍ ነበር፡፡ ሐዋርያውን የቤተክርስቲያን አባቶች “መዶሻ” ይሉታል፡፡ መዶሻ ማዕዘናትን ቀጥቅጦ አንድ እንደሚያደርግ ቅዱስ ጳውሎስም በትምህርቱ ሕዝብና አህዛብን አንድ አድርጓል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ከተራ ሰዎች እስከ ነገሥታት ቤተሰቦች ድረስ በፍቅር እየሳበ ክርስቲያን አድርጓል፡፡ በመልእክቱ መጨረሻ ላይ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ስማቸውን እየጠራ ሰላምታ ማቅረብ ልምዱ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ላስተማራቸው ክርስቲያኖች ለሃይማኖት መዳኛ ለመንፈሳዊ ህይወታቸው መመሪያ እንዲሆንላቸው ብዙ መልዕክቶችን ፅፏል፡፡ አብዛኛዎችን የፃፋቸዉ በእስር ሳለ ነው፡፡ “ሊሰራ የማይወድ ቢኖር አይብላ ” እያለ ያስተምር ነበር፡፡ (2ኛ ተሰ 3 ÷10)

አራት ጊዜ ባደረጋቸዉ ጉዞዎች በተለያየ ቦታዎች አስተምሯል፡፡ ለምሳሌ በሜድትራንያን ባህር ዳር በሚገኙ አገሮች በእየሩሳሌም፤ በሮም፤ በአቴና ፤ በቆሮንጦስ፤ በኤፌሶን፤ በተሰሎንቄ፤ በአንፆኪያ ወዘተ በመጨረሻም በዘመነ ኔሮን ቄሳር ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ሰማእትነትን ተቀብሏል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ያረፈው አንገቱን በሰይፍ ተመትቶ ነው፡፡

◈ 3.3.3 ቤተ ክርስቲያን በአይሁድና በአሕዛብ መካከል

የክርስትና አዲስ አማኞች አስቀድመው አይሁዳዊ አሊያም አህዛብ እንደመሆናቸው መጠን ከበፊቱ እምነታቸው የያዙዋቸውና ክርስትናንም ከተቀበሉ በኃላ ያልተዋቸው ስለነበሩ በሃይማኖቱ ላይ ክፍተትን

ፈጥሮ ነበር። ቤተ ክርስቲያንም ከአይሁዶችም ይሁን ከአሕዛብ የመጣባት የቀድሞ ፈተና ለማወቅ የሁለቱን አካላት አመጣጥ መመልከትን ያሻል።

- አይሁድ

አይሁድ ማለት ታማኞች እውነተኞች ማለት ነው። አይሁድ በአንድ አምላክ በማመን የታወቁ የአብርሃምና የሳራ ልጆች ናቸው። አብርሃም በመጀመሪያ በአንድ አምላክ አመነ። ዘፍ 15÷6። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ዘሩን እንደሚያበዛለት ቃልኪዳን ገብቶለት እሱና ቤተሰቦቹ እንዲገዘሩ አዘዘው። ይህም ትዕዛዝ አብርሃም በአንድ እግዚአብሔር ለማመኑ እና ለመታዘዙ ምልክት መኅተም እንድትሆነው ነው። ሮሜ 4÷11። በአብርሃም የተጀመረው ግዝረት ለዘሮቹ ሁሉ ተላለፈ። ግዝረት ለእስራኤል (አይሁድ) ከአብርሃም ለመወለዳቸው ምልክት ብቻ ሳትሆን የአብርሃምን ሃይማኖት ስለመያዛቸው ማረጋገጫ ነበረች። ከዚህም የተነሳ ከቆላፋን አሕዛብ ጋር በጋብቻ አይቀላቀሉም ነበረ።
እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሲና ተራራ በሊቀ ነብያት ሙሴ አማካኝነት ከአብርሃም ያገኙትን ሃይማኖት የሚጠብቁበት ሕግና ሥርዓት የተፃፈበትን ጽላት ሰጣቸው። እስራኤላውያን ሕጉንና ትዕዛዙን ከመጠበቅ ቸል ባሉ ጊዜ እግዚአብሔር አሕዛብን በማስነሳትና በቸነፈር ይቀጣቸው ነበር። በንስሐ ተመልሰው ሲለምኑት ደግሞ አባት ለልጁ ይቅርታ እንደሚያደርግ ይቅር ይላቸው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የመሲህን መወለድና ሌሎችንም ታላላቅ ትንቢቶችን የተነበዩ ነብያት ትውልዳቸው ከቤተ እስራኤል ስለሆኑ እግዚአብሔር ለእነርሱ ብቻ እንደሆነ ያምኑ ነበር።

- **አሕዛብ**

አሕዛብ ማለት የቃሉ ትርጉም ሕዝቦች ማለት ነው። ይህ ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይ ከእስራኤል ወገን ላልሆኑ ተነግሯል። ዘፍ 10÷5፤ ኢሳ 11÷10። አህዛብ ትንቢት ያልተነገረላቸው ሱባኤ ያልተቆጠረላቸው በተለያዩ አማልክት ሲያመልኩ የሚኖሩ ግዝረትና የመመሪያ ስርዓት የሌላቸው የተበታተኑ ተስፋ የሌላቸው ሕዝቦች ነበሩ። ኤፌ 2÷11-12። አይሁድ ለአሕዛብ ከፍተኛ ጥላቻ ስለነበራቸው አረማውያን እያሉ ይጠሯቸው ነበር።

- 3.3.3.1 **በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረ አለመግባባት**

በአስራ ሁለቱ ሐዋርያት የተስፋፋችው ክርስትና በመቶ ሃያው ቤተሰብ ተጠናክራ እንዲሁም በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ማሕበረ ክርስቲያን ወደ ሦስት ሺህ አደገ፤ በኃላም በቅዱስ ጴጥሮስ እና በቅዱስ ዮሐንስ ተአምራት አምስት ሺህ ምእመናን አመኑ።
በኢየሩሳሌም ውስጥ በተመሰረተችው ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ምዕመናን ቁጥር እየበዛ ሄደ። በክርስቲያኖች መካከል የነበረው የእርስ በእርስ ፍቅር አሕዛብን ማቅረብ /መሳብ/ ጀመረ።
ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ የአንያኪያን ቤተክርስቲያን መስርተው ብዙ አሕዛብን በክርስትና ሃይማኖት አሳመኑ። ነገር ግን ክርስትናን የተቀበሉት አይሁድ ትክክለኛው የክርስትና ሕይወት እና ዓለም አቀፋዊነት ስላልገባቸው እነርሱ የተቀበሉትን የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ አሕዛብ ሲቀበሉት ማየት አላስደሰታቸውም።
አይሁድ የአሕዛብን ከእነርሱ ጋር መተካከል አምነው ሊቀበሉት አልፈቀዱም። በዚህ ምክንያት ወንጌል ያለአሪት፣ ጥምቀት ያለ ግዝረት፣ ክርስቶስ ያለ ሙሴ ሊያድን አይችልም ብለው አሕዛብን ማወክ ጀመሩ። የሐዋ 15÷1። ይህንን ሃሳባቸውን በሶርያና በቂልኪያ ለሚኖሩት ከአሕዛብ ወገን ለነበሩት ክርስቲያኖች ማስተማር ጀመሩ። በዚህ ጊዜ በአሕዛብ አገር የተመሰረተችው ቤተ ክርስቲያን ታወከች።

- 3.3.3.2 **የሐዋርያት ሲኖዶስ (50 ዓ.ም)**

ሲኖዶስ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ስለ ነገራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባዔ ማለት ነው። ቅዱሳን ሐዋርያት በሃምሳ ዓ.ም በቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ሊቀመንበርነት በኢየሩሳሌም ከተማ የመጀመሪያውን የሃይማኖት ሲኖዶስ አካሄዱ። ለሲኖዶሱ መካሔድ ምክንያት የሆነውም በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድነት በተመለሱትና ከአሕዛብነት በተመለሱት ክርስቲያኖች መካከል የተነሳውን ክርክር ለመፍታት ነበር። በሲኖዶሱ ላይ ሐዋርያት በሚያስተምሩበት ጊዜ ከአይሁድ በሚመለሱትና ከአሕዛብ በሚመለሱት ክርስቲያኖች አለመግባባት የተነሳ የገጠማቸውን ችግር አስረዱ። ሲኖዶሱ ጥናቱን ካጠናቀቀ በኃላ ሦስት ውሳኔዎችን አሳለፈ። እነርሱም፡-

1.ለጣዖት በመሠዋቱ ምክንያት የረከሰ ምግብ አትብሉ።

2.ሳይታረድና ደሙ ሳይፈስ ታንቆ የሞተ እንስሳ አትብሉ።

3.ከዝሙት ራቁ። የሐዋ 15

✠ 3.4. ዘመነ ሐዋርያውያን አበው ከ70 ዓ.ም - 160 ዓ.ም

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል የተናገረው ትንቢት ተፈፃሚነት አግኝቶ ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም በቄሳር ጥጦስ/ቲቶ ተደምስሳለች። እስራኤላውያን ከሮማውያን ቅኝ ግዛት ለመውጣት ሲሉ የትጥቅ ትግል ከ66 ዓ.ም ጀምሮ ያካሂዱ ነበር። በዚህ ጊዜ በተከታታይ የነገሡት የሮማ ቄሳሮች ቬስፓስያን እና ልጁ ቲቶ/ጥጦስ/ ሲሆኑ በተለያየ ጊዜ ከዕብራውያኑ ጋር ጦርነት ያካሔዱ ሲሆን የመጨረሻውን የማያዳግም እርምጃ የወሰደው ጥጦስ በ70 ዓ.ም ነበር። በዚህም ለአይሁድ ፋሲካ ተሰባስበው የነበሩትን አይሁድ እስከ መስከረም በዘለቀ ጦርነት ሲደመስሳቸው ከባቢሎን ምርኮ መልስ የተሰራውን ትልቁን የሰሎሞንን ቤተመቅደስ ሊያጠፋው ችሏል። ኢየሩሳሌምንም በማቃጠል አይሁዶች ድጋሚ እንዳያንሰራሩ አድርጓል።

ከዚህ ወቅት ጀምሮ ለ160 ዓመታት የሚዘልቀው ዘመን የመሸጋገሪያ ዘመን እንዲሁም በዘመኑ የነበሩት የቤተክርስቲያን አባቶች በሚያስታውስ መልኩ ዘመነ ሐዋርያውያን አበው ይባላል።

በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን በመንፈሳዊ ዕውቀት ያዳብሩ የነበረበት ወቅት ነው። በነፃ አውጪ አይሁዶችና በሮማውያን መካከል በሚደረገው ጦርነት ክርስቲያኖች አልተሳተፉም። በዚህም የተነሳ አይሁዶችም ሆኑ ሮማውያን ከፍተኛ በደል ያደርሱባቸው ነበር። በዚህና በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም በመቃጠሏ የተነሳ ክርስቲያኖች ጌላ ወደምትባል ቦታ ተሻግረው ለመጓዝ ተገደው ነበር።

ሐዋርያውያን አበው ከሚባሉት አባቶች መካከል ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም፣ ቅዱስ አግናጥዮስ (ምጥው ለአንበሳ)፣ ቅዱስ ፖሊካርፐስ፣ ቅዱስ በርናባስ፣ ኤርማና ፓፒያስ ተጠቃሾች ናቸው።

✠ 3.5 ዘመነ ሰማዕታት ከ160 -312 ዓ.ም

በቤተክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ስደት፣ ስቃይና እልቂት የተፈፀመበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመን በተለይም የሮም ነገሥታትን የመመለክ ልማድ በጥብቅ በመቃወሟ ምክንያት ቤተክርስቲያን ከነገሥታቱ ፈተና ይመጣባት ጀመር። ነገሥታቱ የሚያመልኳቸውን ጣኦታት ባለማምለክ ስግደትም የሚገባው ለአንድ ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ለጣኦታት አይደለም ብላ በማስተማሯ ከካህናተ ጣኦታትም ተቃውሞ ተሰማ። ስለሆነም በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን ያላትን መጻሕፍት፣ ቅርስ፣ በርካታ ሃብቶቿንና ታላላቅ አባቶች ያጣችበት ነው።

ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ክርስቲያኖች ላይ የሰማዕትነት እርምጃ መውሰድ የጀመረው የመጀመሪያው ቄሳር ኔሮን ነው። በ58 ዓ.ም የሮም ከተማ ሁለት ሦስተኛው በታላቅ የእሳት ቃጠሎ አመድ ሲሆን ይህንን ያደረሱት ክርስቲያኖች ናቸው በሚል የሐሰት ክስ መነሻነት ክርስቲያኖችን በአሰቃቂ ሁኔታ በከብት ቆዳ እየጠቀለሉ ለውሾች በመጣል፣ በእንጨት ላይ እየሰቀሉ በማቃጠል እና በመጋዝ በመሰንጠቅ ሰማዕትነት እንዲቀበሉ አደረጓቸው። በተለይም ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ወቅት ሰማዕትነት ተቀብለዋል። ከኔሮን ቄሳር በኃላ የተነሳውና ክርስቲያኖች ላይ ስቃይ በማድረስ የታወቀው ድምጥያኖስ

የነበረው ከ81-96 ዓ.ም ነበር። ትራጃን የተባለው ቁሳር ክርስቲያኖችን በዘዴና በማስፈራራት ቀስ በቀስ ለማጥፋት የሞከረና ከ98 -117 ዓ.ም የገዛ ነው። ማርቆስ ኦሊሪዮስ (120-180 ዓ.ም)፣ ቁሳር ኮሞዶስ (180-192 ዓ.ም)፣ እስክንድሮሳዊ ሮስ (202-205 ዓ.ም)፣ ፊሊጶስ ዓረባዊ (244-249 ዓ.ም) የተባሉ ቁሳሮች ክርስትናን በተለያየ ስልት ለመጥፋት የሞከሩ ናቸው።

- ንጉሥ ዳክዮስ (249 - 251 ዓ.ም)

በቤተክርስቲያን ላይ የመጨረሻውን ድል ለማግኘት ብዙ ቁሳሮች ባላቸው ኃይልና ዘዴ በሙሉ ተጠቅመዋል። ከዚህ ሁሉ ዘዴ ግን በዳክዮስ ዘመነ መንግስት የወጣው አዋጅ ነው። ዳክዮስ ወዲያው እንደነገሠ የክርስቲያኖችን መመሪያ አጥንቶ ክርስቲያኖችን በጣም የሚጎዳቸውን ነገሮች ከጠበብቱ ጋር ተመካክሮ የሚከተለውን አዋጅ አወጀ። አዋጁም በሮም ግዛት በሮማዊ ዜግነት የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በሮማ ባሕል መሠረት የሮማ መንግሥት ሕጋዊ ነው ብሎ የተቀበለውንና ነገሥታቱም ሲያመልኳቸው የኖሩትን ጣዖታት በግዴታ እንዲያመልኩና መባዕ እንዲያቀርቡ የሚል ነበር። ይህን ሳይፈፅም የተገኘ ማንኛውም ዜጋ በሞት ይቀጣ ነበር። ይህም መንግሥታዊ አዋጅ ሮም ለብዙ ዘመን ትከተለው የነበረውን የሃይማኖት ነጻነት ሕግ የሚያፈርስ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሮማ ግዛቶች በሚኖሩ አይሁዳውያንና አሕዛብ ሁሉ ሁከትን ፈጠረ። በዚህን ጊዜ ክርስቲያኖቹ ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው አዋጁን አላከበሩም። ስለዚህም ወንድ፣ ሴት፣ ሕፃን፣ ሽማግሌ ሳይለይ በሁሉም ላይ አሰቃቂ የሆነ የሞት ቅጣት ታዘዘ። ሕፃናት ሁሉ ከእናታቸው እቅፍ ታረዱ። እናቶችም የልጃቸውን መታረድ ካዩ በኃላ አንድ እግራቸው በግንደ ላይ እየታሰረ ሌላው አካላቸው ደግሞ ወደታች (ቁልቁል) እየተንጠለጠለ በአሰቃቂ አሟሟት የሰማዕታትን ጽዋቸውን ተረከቡ። ከዚህ ዘመን ጀምሮም ክርስቲያኖች ሥቃዩ ከጸናባቸው ኑሮአቸውን ለመኖርም ሆነ ሃይማኖታዊ ተልእኳቸውን ለመፈጸም እንዲችሉ በተለይም በሮማና በአካባቢዋ ዋሻ በማዘጋጀት የዐለት ፍርካታ ለመፈለግ ወደ ግበበ ምድር (ካታኮምብ) ገቡ።

- ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ (284 - 305 ዓ.ም)

በዓይነቱም ሆነ በብዛቱ ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው የክርስቲያኖች እልቂት የተፈፀመው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት ነው። ዲዮቅልጥያኖስ የሮማ መንግሥት ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ከተሾመበት ጊዜ አንስቶ እስከ 295 ዓ.ም ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት አልሞከረም ነበር። ጋሌሪዮስ የተባለ የልጁ ባል ከበታቹ እንደራሴ ሆኖ የምስራቁን ክፍል ይገዛ የነበረው ክርስትናን በጣም ይጠላ ስለነበር በእርሱ ምክር በመመረዝ መጀመሪያ በጦር ሠራዊቱ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለጣዖት እንዲሰግዱ ሲያዛቸው እምቢ ስላሉ ማዕርግ ያላቸውን ማዕረጋቸውን እየገፈፈ ተራ ሰዎችንም ጭምር አባረራቸው። ከ295-297 ዓ.ም ድረስ ለሁለት ዓመት ያህል እያከታተለ በክርስቲያኖች ላይ ልዩ ልዩ ጥብቅ የሆኑና የሚከተሉትን አዋጆችን አወጀ።

1. አብያተ ክርስቲያናት እንዲደመሰሱ
2. ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው እንዳይገናኙ
3. ስለ ክርስትና ሃይማኖት የሚናገሩ መጻህፍት ሁሉ እንዲቃጠሉ
4. የቤተ ክርስቲያን ንብረት ሁሉ እንዲወረስ
5. ክርስቲያን የሮም ዜጎች ከመንግሥት ሥራቸው እንዲወገዱ
6. ባሮች ክርስትናን ከተቀበሉ ነፃ የመውጣት መብት እንዳይኖራቸው

ክርስቲያኖች ምንም ሕጋዊ ምክንያት ቢኖራቸው በማንም ላይ ክስ መማሥረት እና ስለመብታቸው መከራከር እንዳይችሉ ማድረግ ናቸው።

ከዚህ በኃላ ለጣዖት መስዋዕት አናቀርብም ያሉት ክርስቲያኖች ደማቸው እንደ ጎርፍ ፈሰሰ። ከአራዊት በማታገል፣ በመጋዝ በመሰንጠቅ፣ በእሳት በማቃጠል፣ ለተራቡ አውሬዎች በመጣል ክርስቲያኖችን ፈጁአቸው። ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ በክርስቲያኖች ላይ ከደረሰ በኃላ የዲቅልጥያኖስ ዙፋን እየወደቀ

ሲሄድ በ305 ዓ.ም ሥልጣኑን ለአማቹ ለጋለሪዮስ ለቆ ወደ ግል የሥጋዊ ነሮው ተመለሰ። ይሁንና በፈፀመው ግፍ ቅጣት የተነሳ ሃብቱን ሁሉ አጥቶና በትል ተበልቶ በሮም መንገዶች ላይ እየለመነ ይኖር ነበር።

በክርስቲያኖች ላይ የደረሱት መከራዎች ክርስቲያኖችን በማጥፋት ፈንታ እያዳፋፈሩአቸውና እያበረቷቸው ይሄዱ ነበር። ከሦስት መቶ የመከራና የስደት ዓመታት በኃላ ጥቂት እረፍት ያገኘችው በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ነበር።

- የታላቁ ቆስጠንጢኖስ መነሳት (312 ዓ.ም)

ቆስጠንጢኖስ ዛሬ የዩጎዝላቪያ ግዛት በሆነችው በናይሳን ከተማ በ258 ዓ.ም ተወለደ። አባቱ ኮንስታንዲዮስ /ቁንስጣ/ እናቱ ቅድስት እሌኒ ይባላሉ። አባቱ አረማዊ የነበረ ሲሆን እናቱ ደግሞ ክርስቲያን ነች። ቅድስት እሌኒ ለቆስጠንጢኖስ የክርስትና ሃይማኖት ከልጅነቱ ጀምሮ እያስተማረች አሳደገችው። ምንግዜም ለክርስቲያኖች ርህራሄ እንዲያደረግ ትመክረው ነበር። ቆስጠንጢኖስ ወጣት ሳለ በዚያ ዘመን በነበረው ህግና ሥርዓት መሰረት በሮም የምስራቁ ክፍል በዲዮቅልጥያኖስና በጋለሪዮስ ቤተመንግሥት ውስጥ ጋሻ ጃግሬ ሆኖ በጊዜው ይሰጥ የነበረውን የውትድርና ሥልጠና ተማረ። ቆስጠንጢኖስ በምስራቅ በነበረበት ጊዜ አባቱ የመክስምያኖስ ቁሳር እንደራሴ ሆኖ የሮምን ምዕራብ ክፍል ያስተዳድር ነበር። ቆስጠንጢኖስ ወደ አባቱ ዘንድ በመሄድ ከእርሱ ስር በከፍተኛ የመኮንንነት ማዕርግ ማገልገል ጀመር። በዚያም በግብረ ገብነቱና በእውነተኛ ፍርዱ በወታደሮቹ ሁሉ ከፍተኛ መከበርን አተረፈ። ቆስጠንጢኖስ የአባቱ እንደራሴ ሆኖ ጥቂት እንደቆየ አባቱ ሞተ። የአባቱ ባለሟሎችና ሕዝቡ በአንድ ድምጽ ተስማምተው በአባቱ ዙፋን ላይ በሮም ምዕራብ ክፍል ገላትያ አነገሡት። በዚሁ ዓመት የአውጎስጦስ መክስምያኖስ ልጅ ማክሴንዲዮስ በሮም የአባቱ የነበረውን ሥልጣን ያዘ።

ቆስጠንጢኖስ የእናቱን ትምህርትና አደራ አስታውሶ በግዛቱ ለነበሩ ክርስቲያኖች ነፃነት አወጀ። በሮም ለሚገኘው ለማክሴንዲዮስ ተመሳሳይ ዐዋጅ እንዲያውጅ ደብዳቤ ፃፈለት። ማክሴንዲዮስ ግን ጣኦት አማላኪ ስለነበር በዚህ አልተደሰተም። ይሁን እንጂ በፍራቻ ተውጦ ላይ ላዩን ትዕዛዙን ያከበረ እያስመሰለ በክርስቲያኖች ላይ መከራ አፀናባቸው። ይህንንም ጉዳይ የሮም ባላባቶች ለቆስጠንጢኖስ ደብዳቤ በመፃፍ እንዲያድናቸው ተማፀኑት። ቆስጠንጢኖስም ማክሴንዲዮስን ለመውጋት ዘመቻ ላይ እንዳለ በቀትር ሰማይ ላይ ብሩህ መስቀል ተመለከተ። በዮናኒ ቋንቋ በዚህ ምልክት ድል ታደርጋለህ የሚል ፅሑፍ ነበረበት። ይህንንም መስቀል በወታደሩ ጦር፣ ልብሱና ጋሻው ላይ እንዲሆን አዘዘ። እርሱም በዘውዱ ላይ መስቀል አሰርቶ አደረገ። በመስቀሉ ኃይል ድልን ተጎናፀፈ። ንጉሥ ማክሴንዲስ በጦርነቱ ላይ ስለሞተ ቆስጠንጢኖስ የማክሴንዲዮስን ግዛት ጠቅልሎ በመያዝ አውጎስጦስ ተባለ።

ማክሴንዲስ ከሞተ በኃላ በ313 ዓ.ም ሊኪኒዮስ ተቃራኒው ማክሲሚኖስድያስን አሸንፎ ምስራቁን የሮም ግዛት ለብቻው ያዘ፤ ወድያውም የቆስጠንጢኖስን እህት አገባና ዝምድና መሰረተ። ከዲዮቅልጥያኖስ ጀምሮ ለአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችው ሮም በሁለት ምስራቁ በሊኪኒዮስ ምዕራቡ ደግሞ በቆስጠንጢኖስ ትገዛ ጀመር። ቆስጠንጢኖስም የክርስቲያኖችን ነፃነትና መብት የሚያስከብር ውል ከሊኪኒዮስ ጋር በሚላኖ ተፈራረመ። ይህም የሚላኖ ውል በመባል ይታወቃል። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ሊኪኒዮስ ውሉን በማፍረሱ የተነሳ ወደ ጦርነት አምርተው በውጊያው ቆስጠንጢኖስ አሸንፎ የምስራቁን ግዛት ጠቅሎ በመያዝ ለአርባ ዓመታት ያህል ከአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችው የሮም ግዛት በአንድ በቆስጠንጢኖስ ሥልጣን ስር ሆነች። ቆስጠንጢኖስ የመንግሥቱን ሥልጣን አንደ አድርጎ በያዘ ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ ይፈፀም የነበረው ግፍ ተቀነሰ።

- ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ለቅድስት ቤተክርስቲያን በቁሳሮች ያጣችውን መብት ያስከበረላት ሲሆን ከመብቶቹም መካከል፦
  1. ቤተ ክርስቲያን ከግብር ነፃ እንድትሆን፣

2. ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ገቢ ሁሉ ድርሻ እንዲኖራት፣
3. በግዛቱ ውስጥ ዕለተ እሁድ የክርስቲያኖች የበዓል ቀን እንድትሆን፣
4. ክርስቲያኖች ንብረታቸውን ለቤተ ክርስቲያን ማውረስ ቤተክርስቲያንም የመውረስ መበት እንዲኖራት፣
5. በክርስቲያኖች መካከል በሚፈጠሩ አንዳንድ አለመግባባቶችና ወንጀል ነክ ላልሆኑ ጉዳዮች ኤጲስ ቆጶሳት የመዳኘት ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚሉ ይገኙባቸዋል።

የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት ቅድስት ዕሌኒ በ325 ዓ.ም የጌታን መስቀል ለበርካታ ዓመታት ከተቀበረበት አስወጥታለች።

- **<u>ቆስጠንጢኖስ /283-337 ዓ.ም./(ቴዲ)</u>**

በ283 ዓ.ም. /ናይሳን/ በምትባል ቦታ ከአረማዊ አባቱ ከኮንስታንዲዮስና ከክርስቲያን እናቱ ከዕሌኒ ተወለደ። እናቱ አይሁዳዊ ክርስቲያን ስትሆን አባቱ አረማዊ /አሕዛብ/ ነበር ታዲያ እንደምን ተገናኝተው ቆስጠንጢኖስን ወለዱ ቢሉ፦

- ክርስትና ገና ስላልተስፋፋ በዚያ ዘመን አንዳንድ ሰዎች ይህን የመሰለ ጋብቻ ይፈጽሙ ነበር።
- ከባሏ ተርቢኖስ ጋር ተጣልታ ተሰዳ ነበርና በስደት እያለች ቆስጠንጢኖስን ወለደች።

በ305 ዓ.ም. አባቱ ከምሥራቅ ጠርቶ የራሱ እንደራሴ አድርጎ ሾመው አባቱም ጥቂት ቆይቶ ሞተ ያን ጊዜ 18 ዓመቱ ነበር። ጥቅምት 28 ቀን 305 ዓ.ም. የመክስምያኖስ ልጅ ማክሴንድዮስ በሮም ነገሠ። ቆስጠንጢኖስም የማክሴንዲዮስን ሴት ልጅ በማግባት ዝምድናውን አጠናከረ። የሁለቱ መስማማት ግን ባጭሩ ተቀጨ ምክንያቱም የማክሴንዲዮስ አባት ወደ ቆስጠንጢኖስ ተሰዶ እዚያም በእስር ቤት ሳለም ይሞታል። /በ310 ዓ.ም./ በዚህ ምክንያት ሁለቱ ይጣላሉ።

በምሥራቅ ደግሞ ጋሊዮስ በግንቦት ወር በ311 ዓ.ም. ሞተ ሥልጣኑም በሊኪኒዮስ አውግስጦስና ማክሲሚኖስ ዲያስቄሳር በመባል ወረሱት። በሁለቱ መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ ስለዚህ ማክሲሚኖስ ዱያስክማክሲንዲዮስ ፣ ሊኪኒዮስ ደግሞ ከቆስጠንጢኖስ ተወዳጀ።

በ312 ዓ.ም. ቆስጠንጢኖስ በማክሴንዲዮስ ዘመተ በመስቀል ምልክትነት ድል ነሳው። በ313 ሊኪኒዮስ ተቃራኒውን ማክሲሚኖስ ድያስን አባሮ ምሥራቁን ግዛት ተቆጣጠረ። ሊኪኒዮስ የቆስጠንጢኖስን እህት አግብቶ ዝምድናውን አጠነከረ። በሚላንም ሕግ አጸደቀ።እነርሱም፣

- በሮም ግዛት የሚገኙ ክርስቲያኖች እንደ ማንኛውም ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸው በሚያዘው ቀኖናና ሕግ አምልኮታቸውን ለመግለጥ ይችላል።
- ባለፉት ዘመናት ይሠራበት የነበረው ክርስቲያኖችን የሚቃወም የሚያወግዝ ሕግ ከዛሬ ጀምሮ የተሻረ ነው።
- ክርስቲያኖች የአምልኮ ቦታ መሥሪያ ቢያስፈልጋቸው በነጻ ይሰጣቸዋል።
- ያለአግባብ ለተወሰዱባቸው ንብረቶች ካሣ የመጠየቅ መብት አላቸው የሚሉ ናቸው።

የሁለቱ ነገሥታት ውል ግን አሁንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጣሰ እስከ መዋጋት አደረሳቸው። በውጊያው ቆስጠንጢኖስ አሸንፎ በ321 ዓ.ም. የድጋሚ ውል ከሊኪኒዮስ ጋር ተፈራረመ። ሊኪኒዮስ ግን በድጋሚ በ312 ዓ.ም. የፈረመውን የሚላኖንን ውል አፍርሶ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ጀመረ።ቆስጠንጢኖስም ውሉን ያፈረሰ ሊኪኒዮስን በ323 ዓ.ም. ገጥሞ ድል ነሳው። ነገር ግን የእህቱ ባል ነበርና ሳይገድል አግልሎ በድሎት አኖረው። ነገር ግን በቆስጠንጢኖስ ላይ ሲያሴር በመገኘቱ በ324 ዓ.ም. የሞት ቅጣት ተቀጣ። ለአርባ ዘመን ያህል ለአራት ተከፍላ የነበረች የሮም መንግሥት አንድ ሆነች። በግዛቷም የነበሩ ክርስቲያኖች የእምነት ነጻነታቸውን አገኙ።

- **<u>ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስቲያን የሰጣቸው መብቶች</u>**

በ313 እና በ315 በወጣው መንግሥታዊ መግለጫ መሠረት ቤተክርስቲያን ከግብር ነጻ ሆነች።

- ከመንግሥታት ገቢ ሁሉ ለቤተክርስቲያንም የተወሰነ ድርሻ አላት /አሥራት በኩራት/

- ከጌታ ትንሣኤ ጀምሮ በክርስቲያኖች ዘንድ ትከበር የነበረችውን ዕለተ ሰንበትን በ321 ዓ.ም. የክርስቲያኖች የበዓል ቀን እንድትሆንና በግዛቱ ውስጥም ሥራ እንዳይሠራባት አወጀ፡
- የሚሞቱ ምዕመናንን ንብረት እንደፈቃዳቸው / እንደ ኑዛዜአቸው/ ለቤተክርስቲያን የማውረስ መብት ተሰጣት፡፡
- በ321 ዓ.ም. በክርስቲያኖች መካከል ለሚነሱ ወንጀል ነክ ባልሆኑ ጉዳዮች ወይም ጥሎች ለኤጲስ ቆጶሳት የዳኝነት ሥልጣን ተሰጣቸው፡፡

ቆስጠንጢኖስ እነዚህን ሕጎች በመንግሥቱ ሕገ መንግሥት ውስጥ እንዲሠፍሩና ክርስትና የመንግሥቱ ሃይማኖት እንዲሆን አወጀ፡፡ ለሞት በቀረበም ጊዜ በኒቆሚዲያ ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስ እጅ በይፋ ተጠመቀ፡፡ በመጨረሻም ዘመኑ የተጠመቀው ስለ ሁለት ምክንያቶች ነው፡፡
ተወልዶ ያደገውና የነገሠውም በአሕዛብ ላይ ነበርና ተቃውሞ እንዳይነሳ፣

የመጀመሪያ ክርስቲያኖች ማለትም እስከ 5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የነበሩት በጥምቀት ኃጢአት እንደምትሠረይና ዳግም ግን ኃጢአት ቢሰሩ በጥምቀት አይሠረይም የሚል እምነት ስለነበራቸው ጥምቀታቸውን ካረጁና ካፈጁ በተለይም በሞት ጣር ላይ እያሉ ያደርጉት ነበርና እርሱም ስለዚህ ምክንያት ነው፡፡(2 ምክንያቶች)**(ቴዲ)**

ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስቲያን ብዙ ውለታን ውሏል፡፡ እናቱ ዕሌኒ በ327 ዓ.ም. የጌታን መስቀል ከተቀበረበት አውጥታለች፣ በ328 ዓ.ም ዐረፈች፡፡ ቆስጠንጢኖስም ሥልጣን በያዘ በ31 ዓመቱ፣ በተወለደ 54 ዓመቱ የበዓለ ጰራቅሊጦስ ዕለት እሑድ ቀን ግንቦት 22 በ337 ዓ.ም. ዐርፏል፡፡

<u>ነፃነቱ ያስገኛቸው በጎና ክፉ ውጤቶች</u> ፡-

ለቤተክርስቲያን የተገኙ ውጤቶች የምንላቸው፡-

1. ለ3 መቶ ዓመታት ያሳለፈችው መከራ ተቋጨ
2. አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ፡፡ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በአዲሲቱ ከተማው በቁስጥንጥንያ ያሳነጸው ቤተክርስቲያን አንዱ ነው፡፡
3. በገሀድ የሚደረግ የጣዖት መስዋዕት ቀረ፡፡ ከሰው ስብእና የወረዱ አስጸያፊ መሥዋዕቶች ከቤተ ጣዖታቱ ባዶ መሆን ጋር ቀሩ፡፡
4. ከቤተ ጣዖት ወደ ቤተ ክርስቲያን፡- በከተማና በቅርብ ቦታዎች የነበሩ አብያተ ጣዖታት አብያተ ክርስቲያናት ሆኑ፡፡
5. ድጎማ፡- በግዛቱ ለነበሩት ጣዖታት ይሰጥ የነበረው የመንግሥት ድጎማ ለቤተክርስቲያንና ለአገልጋዮችዋ ሆነ፡፡
6. ለካህናት ልዩ መብት ተሠጠ፡፡ የዜጎች የሥራ ግዴታዎች ፣ግብር . . . ለካህናት ቀረ፡፡ በካህናት ላይ ክስ ቢኖር በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ፍርድ ቤቶች መታት ጀመረ፡፡ ይህመ አገልጋዮች ከሀገራቱ ሕግ በላይ እንዲሆኑ አስቻለ፡፡
7. ሰንበት መከበር ጀመረች፡- የዕረፍትና የአምልኮ ቀን እንድትሆን ቆስጠንጢኖስ ሲያውጅ ለወታደሮቹ በሰንበት ዕረፍት ሠጠ፡፡ ዕለቲቱ የበለጠ በበዓልነት እንድትከበርበትም ሕዝባዊ ጨዋታዎች በሰንበት ተፈቀዱ፡፡

<u>ለመንግሥት እና ለሕዝብ የተገኙ መልካም ውጤቶች</u>

1. ስቅላት ቀረ፡- ሮማዊ ያልሆኑ የሚገደሉበት የስቅላት ቅጣት ቀርቶ መስቀል የሰላምና ድል ምልክት ሆነ፡፡
2. የአካል ጉዳተኞች ግድያ ቀረ፡- ከአረማዊነት የተወሰደው አካል ጉዳተኞችን በገደቢስነት እየፈረጁ መግደል ቆመ፡፡
3. የባሪያ ንግድ ተሻሻለ ፡- ባሪያን እንደ እንስሳ ቆጥሮ ማሰቃየትና ግድያ ቀርቶ ሰብአዊ ክብር እንዲጠበቅለት ተደረገ፡፡

4. የግላዲያተሮች ግፍኛ ጨዋታ ተከለከለ፡- ሰውና አራዊትን እያታገሉ በዘግናኝ ሞት መዝናት ተከለከለ፡፡

<u>አሳዛኝ ክስተቶች</u>

ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት እውቅና ማግኘትዋን ተከትሎ ክርስቲያኖች የበለጠ በአገልግሎታቸው እና በሕይወታቸው ሲበረቱ አብዛኛው ሕዝብ ክርስቲያን ሆነ በቤተ መንግሥት እና በባለ ጸጎች አካባቢ ለ ቤተክርስቲያን አባቶች የተሰጠው ክብርም የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የነበሩና ጥቅም ፈላጊዎችም በማስመሰል ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ አጋጣሚ ከፈተላቸው፡፡

እነዚህም የአሕዛብ ጣዖታት ልማድን የዓለምን የሐሰት ፍልስፍናና ለክርስቲያን ያልተገባ ሕይወትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው ገቡ፡፡ ይህም ትህትና የቅድስና ሕይወት ለክርስትና ዋጋ መክፈል... ፡፡ በፍቅረ ንዋይ በክፉ ምኞት በሥልጣን ግብግብ በአካባቢያዊነት እና በንቀት እንዲተኩ አደረገ፡፡ ስለዚህም አለመግባባቶች ወደ ነገሥታት ፍርድ ወንበር ቀላል ጉዳዮች ወደለየለት ልዩነት እንዲያድጉ ሲያደርግ ቆይቶ ቤተ ክርስቲያንን የከፋፈለ አደጋ ለመሆን በቃ፡፡ ከእነዚህ መከፋፈሎች በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የታዩት የሚከተሉት ልዩነቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

1. የመላጥዮስ ሐሳብ፡- በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን የካዱና ለጣዖት ያጤሱ ንስሓ ቢገቡም መቀበል የለብንም በሚል ከተፍፃሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስና ከተከታዮቹ ጋር የፈጠረው ክርክር መወጋገዝ አስከትሎ ነበር፡፡
2. የዶናቲስቶች ያልገባ አክራሪነው፡- በካርቴጁ ዶናቲስት መሪነት ጥንቃቄንና ቅድስናን በቤተክርስቲያን ለመጠበቅ ተነስተው በሐሰተኛ መረጃዎች ምዕመናኑን ግራ ማጋባትና ክርስቲያኖችን ማሳደድ ጀመሩ በኋላም ቅዱስ ቁርባን የሚለወጠው ካህኑ ቅድስና ካለው ብቻ ነው ብለው በማስተማራቸው የተወገዙ እና ለአንድ ክፍለ ዘመን የቆየ መለያየት የፈጠሩ ነበሩ፡፡
3. ጵርስቅላውያን፡- ጵርስቅላና ተከታዮቹ ጥንቆላንና ፍልስፍናን ከክርስትና ጋር ቀላቅለው ያስተማሩ አስከፊ ሁከት የፈጠሩም ነበሩ፡፡
4. አርዮሳውያን ፡- በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአርዮስ የተጀመረ አዲስ ትምህርት ነው፡፡ አርዮስ በግሪካውያን ፍልስፍና (በተለይም በፕሌቶ) ትምህርት ሁለት አማልት (ትልቅ እና ትንሽ) የሚለውን በመጽሐፍ ቅዱስ ሽፋን ያስተምርም ነበር፡፡ በዚህ ትምህርቱም የክርስቶስን አምላክነት ክዶ ፍጡር ነው አለ፡፡ በድምጹ ማማርና ለሕዝቡ በቀረበ አቀራረቡ በአጭር ጊዜ ተከታዮች አፈራ፡፡ ተፈፃሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ከስህተቱ እንዲመለስ ቢመክረውም አልተስማማም፡፡ ከመላጥዮሳውያን ጋር በመተባበሩ ቢወገዝም ተፍፃሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስን የተካው አኪላስ ከግዝቱ ፈታው፡፡ አኪላስ በመንበረ ማርቆስ በተሾ በ6ኛው ወር ሞተና (312 ዓ.ም) እለ እስክንድሮስ ተተካ ፡እለ እስክንድሮስ አርዮስ ከስህተቱ እንዲታረም ቢመክረውም አልሰማም ይባስ ብሎም እለ እስክንድሮስን በሰባልዮሳዊነት (እግዚአብሔር አንድ ገጽ ነው በማለት በሚያስተምረው) ሊከሰው ሞከረ፡፡ እለ እስክንድሮስ የአርዮስን ክህደት 100 ጳጳሳትን ይዞ ይህን ትምህርት ቢያወግዘውም በትምህርቱ የተሳሳቱ ‹‹ አባቶችን›› እና ተከታዮችን ይዞ በስህተቱ ቀጠለበት፡፡

እነዚህና የመሳሰሉት ክህደቶችና መፋፈሎችን ለመግታትም አካባቢያዊ (local) እና ዓለም አቀፋ (universal) ጉባኤያት ተካሂደዋል፡፡ የሮም መንግሥት ክርስቲያን መንግሥት ስለሆነም ነገሥታቱ በሕግና በአስተዳደር ለመፍታት ሞክረዋል ብዙ ጊዜም ተሣስተዋል፡፡ አባቶችም መጻህፍት በመጻፍ ፤በማስተማር እና በመንፈሳዊ ተጋድሎ በጾምና በጸሎት ለመፍታት ደክመዋል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር